# አልተሳሳትንምን?

"በታቦት ላይ ለሚነሡ ጥያቄዎች የማያዳግም ምላሽ" ተብሎ
የቀረበው የመምህር ምሕረተ አብ አሰፋ ክፍል ፩ ቪሲዲ
ስብከት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲመዘን

ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
የመጀመሪያ ዕትም ጥር 2003 ዓ.ም.

ስለ መጽሐፉ አስተያየት ወይም ለማሠራጨት ጥያቄ ቢኖርዎ

በሚከተሉት አድራሻዎች ይጠቀሙ

0911 96 11 67
23956 ኮድ 1000
Email: agizet@yahoo.com

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡፡

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሣሣኝ፣ ያስጀመረኝና ያስፈጸመኝ አምላክ ይመስገን፡፡ የመምህር ምሕረተ አብ አሰፋን ቪሲዲ በመስጠት እንድመለከተውና ምላሽ እንድሰጥበት ምክንያት የሆነችውን እኅት እምወድሽ ታከለን እግዚአብሔር ይባርካት፡፡ መጽሐፉን አንብበው ገንቢ አስተያየቶቻቸውን የሰጡኝን ወገኖች ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር ያክብርልኝ፡፡ መጽሐፉ ለኅትመት እንዲበቃ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉልኝንም እግዚአብሔር የእነርሱ የሆነውን ሁሉ አትረፍርፎ ይባርክ፡፡

## አበርክቶ

ይህ መጽሐፍ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚወዱ ሁሉ መታሰቢያ ይሁን!!

## ማስታወሻ

በሽፋኑ ላይ የሚታየው የብሉይ ኪዳን ታቦት ሥዕል ከ http://www.themanyfacesofspaces.com, 15/11/2010 የተወሰደ ሲሆን፥ የኢትዮጵያ ታቦታት ፎቶ ደግሞ ከ http://www.ethipiatourandtravel.com, 15/11/2010 ላይ የተወሰደ ነው፡፡

## ማውጫ


አርእስት — ገጽ

መቅድም ........ 5
መግቢያ ........ 8

ምዕራፍ አንድ፥ ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ ........ 9
1.1. ታቦት ምንድን ነው? ........ 9
1.2. ጽላት ምንድን ነው? ........ 10
1.3. የታቦት መኖሪያ ........ 11
1.4. ጽላቱ ወይም ታቦቱ የማን ነው? ........ 12
1.5. የታቦት አገልግሎት ........ 12
1.6. ካህናተ ኦሪት ታቦቱን የተሸከሙባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች ........ 13
1.7. በዐዲስ ኪዳን ታቦት አለን? ........ 16

ምዕራፍ ሁለት፥ ታቦታት በኢትዮጵያ ........ 20
2.1. የቃል ኪዳኑ ታቦት በአሁኑ ጊዜ የት ይገኛል? ........ 20
2.1.1. የብሉይ ኪዳን አዋልድ መጻሕፍት ምስክርነት ........ 20
2.1.2. ክብረ ነገሥትና ምስክርነቱ ........ 23
2.1.3. የቃል ኪዳኑ ታቦት በዛጉዌዎች አፈ ታሪክ ........ 30
2.1.4. የቃል ኪዳኑን ታቦት አድራሻ የፈለጉ ምን አሉ? ........ 32
2.2. ታቦታት በኢትዮጵያ ........ 34
2.3. ታቦትና መሠዊያ ምንና ምን ነበሩ? ........ 40
2.4. በቃል ኪዳኑና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል ያሉ ልዩነቶች ........ 45

ምዕራፍ ሦስት፥ የአልተሳሳትንም ጉልሕ ስሕተቶች ........ 47
3.1. ስለ ታቦት አመጣጥ ........ 48
3.2. ስለ ታቦትና ጣዖት ........ 51
3.3. ስለ ታቦት መባዛት ........ 53
3.4. ታቦትን ስለ መንካት - አለ መንካት ........ 75
3.5. ወደ ታቦት ስለማይቀረብበት ምክንያት ........ 59
3.6. ታቦታት ኦሪታውያን ያሰኛሉን? ........ 63
3.7. ታቦታት የሚሰጧቸው ጥቅሞች አሉን? ........ 69
3.8. ለታቦት ይሰገዳልን? ........ 75
3.9. ታቦታት ለምን ይሰረቃሉ? ........ 79
3.10. ስለ ታቦት ዐዲስ ኪዳን ምን ይላል? ........ 83
ማጠቃለያ ........ 93
ዋቢ ጽሑፎች ........ 97




## መቅድም

ይሁዲነት የክርስትና ጥላ ተደርጎ ሊወሰድ ቢችልም፥ ራሱን የቻለና ከክርስትና የተለየ ሃይማኖት ነው። የክርስትና መሥራች በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ በሐዋርያቱ ትምህርት ውስጥ፥ ክርስትና ራሱን የቻለ ዐዲስ መንገድ እንጂ የይሁዲነት ተቀጥላ ሆኖ የቀረበበት ሁኔታ የለም። በአገራችን የሚታየውን አንዳንድ ሁኔታ ከተመለከትን ግን፥ ክርስትና ራሱን የቻለ ሌላ መንገድ ሳይሆን ከይሁዲነት ጋር የተቀላቀለ ቅይጥ ሃይማኖት ሆኖ ነው የሚታየው። ኢትዮጵያ አስቀድሞ ኦሪትን በኋላም ክርስትናን ተቀብላለች የሚለው የብዙዎች ዕሳቤም፥ ስለ ኢትዮጵያ ክርስትና ብዙዎች ከዚህ ውጪ እንዳያስቡ አድርጓቸዋል ማለት ይቻላል።

ኦሪት የተሰጠው ለእስራኤል ብቻ በመሆኑ፥ ቀሪው የዓለም ሕዝብ (አሕዛብ) በኦሪት ላይ የይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ ሕጋዊም ሞራላዊም መብት የለውም። በአገራችን እንደሚታየው ከእስራኤላውያን ጋር ተደባልቆ በመኖርና በሌሎችም ምክንያቶች፥ ኦሪታዊ ወይም እስራኤላዊ ዕሴቶችን መውረስና የራስ ባህል አድርጎ መጠቀም ተፈጥሮአዊ ሂደት ሊሆን ይችላል። ጉዳዩ መታየት ያለበት ግን ከባህል አንጻር እንጂ ከክርስትና አንጻር አይደለም። ምክንያቱም ይሁዲነት ከክርስትና የተለየ ሌላ መንገድ ነበረ፤ ክርስትናም ከይሁዲነት የተለየ ሌላ መንገድ ነው።

በዓለም ላይ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታቦት እንደሌለ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ግን ታቦት የተባለ ንዋይ ቅዱስ (የተለየ ዕቃ) አለ። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሊቀርብላቸው የማይችለውን የኢትዮጵያን ታቦታት፥ አገራዊ ምንጫቸውን ከመግለጽ ይልቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አሰደግፎና መጽሐፍ ቅዱሳውያን አስመስሎ ማቅረብ ተለምዷል፤ ነገር ግን ትክክል አይደለም።

መምህር ምሕረተ አብ "አልተሳሳትንም" በሚል ርእስ ያቀረቡት ትምህርት በዚህ መሠረት ላይ የቆመ ነው። የመምህሩ ስብከት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የሚያስተምረውን በሚገባ ያላስተዋሉ ምእመናንን ሊያደናግርና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊመስል ይችላል። ስለዚህ እንዲህ ያለው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ሊታረም ይገባል። ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውንና ስለ

ኢትዮጵያ ታቦታት ያለውን እውነታ ለይቶ ማሳየትም አስፈላጊ ነው። የዚህን መጽሐፍ ርእስ በመምህሩ የስብከት ርእስ ላይ "ን"ን ጭኖና የጥያቄ ምልክት አክሎ "አልተሳሳትንምን?" ብሎ መሠየም ያስፈገለውም ስለዚህ ነው።

በአገራችን በሃይማኖት ነክ ጽሑፎች ላይ መተቻቸት ዐዲስ ነገር አይደለም። የሌሎቹን ትተን በክርስትና ስም በሚጠሩ ሃይማኖቶች መካከል አንዱ ለጻፈው ሌላው ምላሽ የሰጠባቸው መጻሕፍት አሉ። በ17ኛው ምእት ዓመት ወደ አገራችን የገቡትና ኢየሱሳውያን የተባሉት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች በዐማርኛ በጽሑፍ ያሠራጩ ለነበረው ትምህርታቸው፥ "ከአፍርንጅ የምንለይበት" በሚል ርእስ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በጊዜው ምላሽ ሰጥተው እንደ ነበር መረጃዎች ይጠቊማሉ።[1] ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ "ተግሣጽና ምክር" በሚል ርእስ በ1942 ዓ.ም. ላሳተሙት መጽሐፍ፥ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በ1949 ዓ.ም. "ኰኵሐ ሃይማኖት" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ የሰጡት ምላሽ፥ ካቶሊካዊው አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት በ1951 ዓ.ም. "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ባሕርያት አካላዊ ተዋሕዶ የምታምነው ትምህርት" በሚል ርእስ ለጻፉት መጽሐፍ፥ አለቃ አያሌው ታምሩ በ1953 ዓ.ም. "መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" በሚል ርእስ እና መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በ1954 ዓ.ም. "መድሎተ አሚን" በሚል ርእስ የሰጧቸው መጽሓፋዊ ምላሾች ይጠቀሳሉ። በዚህም ዘመን ተመሳሳይ ሥራዎች ቀጥለዋል። በተለያዩ አብያተ እምነት ውስጥ ያሉ ብቻም ሳይሆኑ በአንድ ቤተ እምነት ውስጥ ባሉ ወገኖች መካከልም በጽሑፍ ሥራዎች ላይ የመተቻቸት ሁኔታ አለ።

በመጀመሪያ የተጻፉትም ሆኑ ምላሾቹ ለአንባቢ ፍርድ የሚተዉ ቢሆንም፥ በሁለቱም ወገኖች እንዲህ ዐይነት ጽሑፎች መቅረባቸው በራሱ መልካም ነገር ነው። አንባቢው በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን የአስተምህሮና የባህል አንድነትና ልዩነት መገንዘብ ያስችለዋል። ከራሱ ሃይማኖታዊ ተቋም ባሻገር ለክርስትና ሊኖረው ስለሚገባ አመለካከት በቂ ግንዛቤንም ያስጨብጠዋል። እነዚህን ጠቃሚ ነገሮች ለማግኘት ግን፥ ትችቶቹ በማስረጃ የተደገፉ፣ ከተራ አሉባልታና ከስድብ የጸዱ፣ እንዲሁም ከግለ ሰብ ይልቅ በአስተሳሰብ ላይ ያተኰሩ ቢሆኑ ተመራጭ፥ ተገቢም ነው።

[1] አምሳሉ (ዶ/ር) (1976፣ 84)።





ይህ ጽሑፋዊ ምላሽ የተዘጋጀበት ዋና ምክንያት፥ ለመምህር ምሕረተ አብ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ምላሽ ለመስጠት ቢሆንም፥ በዚህ ብቻ ተወስኖ እንዲቀርብ አልተፈለገም። አንባቢ በቃል ኪዳኑ ታቦት እና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል ያሉትን መሠረታውያን ልዩነቶች እንዲረዳ ለማድረግም ታስቦ ነው የተዘጋጀው። ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስንና ልዩ ልዩ የታሪክ ሠነዶችን ለማመሳከር ጥረት ተደርጓል። ስለ እግዚአብሔር ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ሁሉ ለኢትዮጵያ ታቦታት በመጥቀስ እየተሳለፉ ያሉ ትምህርቶችን መሠረታዊ ስሕተት ለማሳየትም ተሞክሯል። በመሆኑም አንባቢው ጥሩ ግንዛቤ እንደሚጨብጥ አዘጋጁ ተስፋ ያደርጋል።

## መግቢያ

በሦስት ምዕራፎች የተከፈለው ይህ መጽሐፍ፥ በመጀመሪያው ምዕራፍ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን በመዳሰስ ግንዛቤን ያስጨብጣል። በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ፥ ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት አመጣጥና አገልግሎት በተለያዩ ማስረጃዎች የተደገፈ ግምገማ ያቀርባል። በመጨረሻው ምዕራፍ መምህር ምሕረተ አብ ላቀረቧቸው ዐሥር ጥያቄዎችና መልሶች መጽሐፍ ቅዱስን ከተጨባጩ እውነታ ጋር ያገናዘቡ ምላሾች ይሰጣሉ።

ምዕራፍ ሦስት ሰፊውን የመጽሐፉን ክፍል የሚሸፍን እንደ መሆኑ፥ ለአቀራረቡ መልክ እንዲኖረውና ለአንባቢም ምቹ እንዲሆን በማሰብ፥ የመምህር ምሕረተ አብን ጥያቄና የአዘጋጁን መልስ መሠረት በማድረግ፥ ለያንዳንዱ ጥያቄና መልስ ርእስ ተሰጥቶታል።

በዚህ መጽሐፍ ለቀረቡ ሐሳቦች በዋቢነት የተጠቀሱ የጽሑፍ ሰነዶች፥ በተጠቀሱበት ስፍራ ላይ በተራ ቍጥር በግርጌ ማስታወሻ ላይ የሰፈሩ ሲሆን፥ የጽሑፉ ባለቤት (የደራሲው ስም)፣ እንዲሁም በቅንፍ ውስጥ መጽሐፉ የታተመበት ዓመተ ምሕረትና ጥቅሱ ወይም ሐሳቡ የተወሰደበት ገጽ ተጠቅሰዋል። የአንድ መጽሐፍ ደራሲ፣ መጽሐፉ የታተመበት ዓመተ ምሕረትና ገጹ ከተጠቀሰ በኋላ በቀጣዩ ተራ ቍጥር "ዝኒ ከማሁ" የሚል ግእዛዊ ሐረግ ከሰፈረ፥ ይህም ጥቅስ ወይም ሐሳብ የተወሰደው ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ ነው ማለት ነው (ይህን ማለት ያስፈለገው ለአንዳንድ አንባብያን ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ነው)። በተጨማሪም አንዳንድ ማብራሪያ ላስፈለጋቸው ሐሳቦች በግርጌ ማስታወሻ ላይ ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል።

በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በአብዛኛው የተወሰዱት የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ በ1953 ዓ.ም. ካሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፥ ከሌሎች ዕትሞች በተጠቀሰበት ስፍራ ለምሳሌ፦ ከዐዲሱ መደበኛ ትርጒም ከተወሰደ "ዐ.መ.ት." ተብሎ ይጠቀሳል። ከ1980 ዓም እና ከ2000 ዓ.ም. ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሰበት ቦታም በዓመተ ምሕረቱ ተለይቶ ይጠቀሳል።

መልካም ንባብ!





# ምዕራፍ አንድ
# ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ

### 1.1. ታቦት ምንድን ነው?

ታቦት የሚለው ቃል በሰዋሰዋዊ ፍቺው የተለያዩ ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል፤ እንደየአገባቡ፡ መርከብ፣ ሣጥን፣ ሙዳየ ምጽዋት፣ ሙዳየ ምዉት (መቃብር) ተብሎ ይተረጐማል። ምስጢሩ ግን ቤታና ማኅደር ከመሆን አያልፍም።[2]

በዚህ ክፍል የምናየው ታቦት፥ እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ወደ ተስፋዪቱ ምድር እየተጓዙ ሳለና ወደ ሲና ተራራ ከደረሱ በኋላ (ዘፀ. 19፥1-2) እንዲሠራ የታዘዘውን ታቦት (የጽላት ቤት) ይሆናል። የዚህ ታቦት ታሪክ እዚህ (በሲና ተራራ) ላይ ይጀምራል። ከዚህ በፊት በሰማይም ሆነ በምድር ታቦት ስለ መኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም።

ታቦት ከግራር ዕንጨት ተሠርቶ ውስጣዊና ውጫዊ ክፍሉ በወርቅ የተለበጠ፥ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል (125 ሳንቲ ሜትር)፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳንቲ ሜትር)፣ ቁመቱ አንድ ክንድ ተኩል (75 ሳንቲ ሜትር) ሆኖ በሣጥን መልክ የተሠራ[3] የተቀደሰ ዕቃ (ንዋይ ቅዱስ) ነበር። አራት ካህናት ሊሸከሙት በሚችሉት ሁኔታ እንዲሠራ ስለ ታዘዘ፥ አራት የወርቅ ቀለበቶች ተደርገውለታል። በቀለበቶቹ ውስጥ የሚውሉና ከግራር ዕንጨት ተሠርተው በወርቅ የተለበጡ ሁለት መሸከሚያዎች (መሎጊያዎች) ነበሩት። በታቦቱ ልክ የተዘጋጀና የስርየት መከደኛ ሆኖ የሚያገለግል ክዳንም ተበጅቶለታል። በክዳኑ ላይ በተቀጠቀጠ ወርቅ የተሠሩ ሁለት ኪሩቤል ነበሩ። እነርሱም ትይዩ ሆነው በአንድ ላይ የተሠሩ ሲሆን፥ ወደ ላይ በተዘረጉት ክንፎቻቸው የስርየት መከደኛውን እንዲሸፍኑ ሆነው ተሠርተዋል (ዘፀ. 25፥10-20)።

ታቦቱ በዚህ ንድፍ መሠረት እንዲሠራ ያዘዘው እግዚአብሔር ነው። ለታቦቱ ብቻ ሳይሆን የመገናኛውን ድንኳንና በውስጡ የነበሩትን ልዩ ልዩ ንዋያተ ቅድሳት (የተቀደሱ ዕቃዎች) እንዲሠሩ፦ ብልኀት፣ ጥበብ፣ ማስተዋል፣ ዕውቀትና የእግዚአብሔር መንፈስ የሞላበትና ከይሁዳ ነገድ

[2] ኪዳነ ወልድ (1948፣ 892)።
[3] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣ 128)።

የሆነ ባሰልኤልና ከዳን ነገድ የሆነ ኤልያብ ተመርጠዋል (ዘፀ. 31፥1-11፤ 35፥30-35፤ 36፥1)። እግዚአብሔር በሰጠው ልኬትና ባዘዘው ጥሬ ዕቃ ባሰልኤል ታቦቱን ሠራ (ዘፀ. 37፥1-9)።

በኦሪት ዘመን የተሠራውና በእስራኤል ታሪክ የነበረው ታቦት ይኸው ባሰልኤል የሠራውና ሁለት ጽላት የያዘው አንድ ታቦት ብቻ ነበር። የተሰጠው ለእስራኤል ብቻ፥ አገልግሎቱም ለእስራኤል ብቻ እንጂ ለሌሎች አሕዛብ የሚተርፍ አልነበረም፤ "ቃሉን ለያዕቆብ፥ ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል። ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፤ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም" (መዝ. 147፥8-9) ተብሎ ተጽፏልና። "የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተከናንቦ ሙሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጽበት ዙፋን ነበር።"[4] እስራኤላውያንም ቢሆኑ፥ ከዚህ ታቦት ውጪ በዚሁ ታቦት አምሳል ወይም በሌላ መልክ ሌሎች ታቦታትን እንዲሠሩ እግዚአብሔር አላዘዘም። ሕዝቡም በያሉበት አካባቢ ታቦት እንዲኖር ፈልገው ያቀረቡት የ"ታቦት ይቀረጽልን" ጥያቄ የለም። ባሰልኤል ብልኀትም የእግዚአብሔር መንፈስም የሞላበት ሰው ቢሆንም፥ እነዚህን ሀብታት ተጠቅሞ ታቦታትን ወደ ማባዛት ተግባር አልገባም።

## 1.2. ጽላት ምንድን ነው?

ጽላት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው ቃል ኪዳን የተጻፈባቸው ሰሌዳዎች ናቸው። በዐማርኛ አንዱ ሰሌዳ ጽላት ይባል እንጂ፥ በግእዙ ጽላት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቍጥርን ያመለክታል፤ አንዱ ሰሌዳ ደግሞ ጽሌ ነው የሚባለው። ጽሌ ወይም ጽላት በሚለው ስም ሌሎች ነገሮችም የሚጠሩ መሆኑ ቢታወቅም፥[5] ዋናውና በዚህ ክፍል የምንመለከተው ዐሠርቱ ቃላት የተጻፉባቸውን ሰሌዳዎች ይሆናል።

በመጀመሪያዎቹ ጽላት የሰው ተሳትፎ አልነበረም። "ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፤ ጽሕፈቱም በጽላቶች ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበረ" (ዘፀ. 32፥16)። "እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው" (ዘፀ.

[4] ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) (1978፣ 109)።
[5] ኪዳነ ወልድ (1948፣ 755)።





31፥18)። ይሁን እንጂ ሙሴ ከተራራ ሳይወርድ መዘግየቱን ምክንያት አድርጎ ሕዝቡ በአሮን መሪነት የጥጃ ምስል አቁሞ እያመለከ በመመልከቱ፥ ሙሴ ተቈጥቶ ጽላቱን ከእጁ ጥሎ ሰበራቸው (ዘፀ. 32፥19)። "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደ ፊተኞች አድርገህ ጥረብ፤ በሰበርኻቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ" (ዘፀ. 34፥1) በማለት ጽላቱ እንደ ገና እንዲዘጋጁ አደረገ። በዚህም ሙሴ ጽላቱን በመጥረብ ሲሳተፍ የቀደሞዎቹን ቃላት የጻፈው ግን አሁንም እግዚአብሔር ነበር (ዘፀ. 34፥28፤ ዘዳ. 10፥1-4)። የተጻፈው ዐሠርቱ ቃላት ብቻ ናቸው እንጂ ሌላ የተጻፈ ጽሑፍም ሆነ የተቀረጸ ምስል ወይም ሥዕል ፈጽሞ አልነበረም (ዘዳ. 5፥22፤ 10፥4)።

የጽላቱን ቍጥር ስንመለከት ለእስራኤል የተሰጡት ጽላት ሁለት ብቻ ነበሩ። በእነርሱ አምሳል ሌሎች ጽላት እንዲቀረጹና እንዲባዙ አልታዘዘም። ባይታዘዝም እንኳ ሰው እኔ ከሙሴ አላንስም ብሎ ጽላት ልጥረብ ቢል፥ እግዚአብሔር ካልጻፈበት ጽላቱ እንዴት ጽላት ሊሆን ይችላል?

## 1.3 የታቦት መኖሪያ

በደብተራ ኦሪት (በማደሪያው ድንኳን) ውስጥ የታቦቱ መቀመጫ ስፍራ "ቅድስተ ቅዱሳን" ተብሎ የሚጠራው ውስጠኛው ክፍል ነበር (ዘፀ. 26፥33-34፤ ዕብ. 9፥3-4)። ወደዚህ ስፍራ የኦሪቱ ሊቀ ካህናት በዓመት አንድ ጊዜ በማስተሰረያ ቀን ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ኀጢአት ለማስተሰረይ ደም ይዞ ይገባ ነበር (ዕብ. 9፥7)። ከዚህ ውጪ መግባት አልተፈቀደለትም ነበር። ለሙሴም፥ "እኔ በስርየቱ መክደኛ ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ሁል ጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው" የሚል ማስጠንቀቂያ ተላልፏል (ዘሌ. 16፥2)። የቃል ኪዳኑ ታቦት አንድ ቋሚ መቅደስ እስኪሠራለት ድረስ በድንኳን ውስጥ ይሄድ ነበር (2ሳሙ. 7፥5-6)። መቅደስ ከተሠራለት በኋላ ግን በአንድ ስፍራ ተቀምጧል። ባቢሎናውያን የይሁዳን ሰዎችና የቤተ መቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት ማርከውና ዘርፈው ሲወስዱ ቤተ መቅደሱን አቃጥለውታል። ታቦቱ ግን የት እንደ ደረሰ አልታወቀም። በተዘረፉት የተቀደሱ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ታቦቱ አልተጠቀሰም (2ነገ. 25፥8-17)። ሰባው የምርኮ ዘመን ተፈጽሞ ሚጠት

(ከምርኮ መመለስ) ቢታወጀ ጊዜ የተዘረፉት የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች እንዲመለሱ ሲደረግ፥ አሁንም በዕቃዎቹ ዝርዝር ውስጥ ታቦቱ የለም (ዕዝ. 1፥7-11)።

## 1.4 ጽላቱ ወይም ታቦቱ የማን ነው? (በማን ስም ተጠራ?)

ጽላቱም ሆነ ታቦቱ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የሰጠው ቃል ኪዳንና ምስክር፥ የክብሩ መገለጫም ዙፋን በመሆኑ የተጠራው በእግዚአብሔር ስም ነው። መጽሐፍ ቅዱስም በኪሩቤል ላይ በተቀመጠ በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም "የእግዚአብሔር ታቦት" ተብሎ የተጠራ መሆኑን ይመሰክራል (2ሳሙ. 6፥2፡3፤ ኢያ. 7፥6፤ 1ሳሙ. 3፥3፤ 4፥11፡21-22)። ወይም ደግሞ ከላይ የተገለጹትንና "ቃል ኪዳን"፣ "ኪዳን"፣ "ምስክር" የተባሉትን ነገሮች ሊገልጽ በሚችልበት አጠራር፡-

- "የቃል ኪዳኑ ታቦት" (ዘኁ. 14፥44፤ ዘዳ. 10፥8፤ 31፥26፤ ኢያ. 3፥6፤ መሳ. 20፥27-28፤ 1ሳሙ. 4፥4፡5)፤
- "የኪዳኑ ታቦት" (ዘኁ. 10፥33፤ ዕብ. 9፥4፤ ራእ. 11፥19)፤
- "የምስክሩ ታቦት" (ዘፀ. 25፥21፤ 26፥33-34፤ 30፥6፡26፤ 40፥21፤ ኢያ. 4፥15-16) እየተባለ ተጠርቷል። ከእነዚህና እነዚህን ከመሳሰለው በቀር፥ ታቦቱ (ጽላቱ) የተጠራበት ሌላ ስም የለም። መታሰቢያ ሆነው የተሰጡትም ፍጡር መልአክ ወይም ሰውም ፈጽሞ የለም።

## 1.5 የታቦት አገልግሎት

ታቦት የሁለቱ ጽላት ማኖሪያና ከእስራኤል መሪዎች ጋር የእግዚአብሔር መገናኛ ሆኖ አገልግሏል።[6] ታቦት የጽላት ማኖሪያ ነበረ (ዘፀ. 25፥16፡21፤ 40፥20፤ ዘዳ. 10፥1-5፤ 1ነገ. 8፥9፤ 2ዜና. 5፥10)። በዕብራውያን መልእክት እንደ ተጻፈው ደግሞ፥ ከጽላቱ በተጨማሪ "መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር" በታቦቱ ውስጥ ነበሩ (ዕብ. 9፥4)።

እግዚአብሔር ስለ ታቦቱ አሠራር አጠቃላይ ንድፉን ለሙሴ ከነገረው በኋላ፥ "የስርየት መክደኛውን በታቦቱ አናት ላይ አስቀምጠው፤ እኔ የምሰጥህን ምስክሩንም በታቦቱ ውስጥ አስቀምጥ። በምስክሩ ታቦት ላይ ባሉት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል፣ በስርየት መክደኛው ላይ በዚያ እኔ ከአንተ ጋር እገናኛለሁ። ለእስራኤላውያን የሚሆኑትን ትእዛዞቼንም እሰጥሃለሁ" (ዘፀ. 25፥21-22 ዐ.መ.ት.) ባለው መሠረት፥ ታቦት

[6] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፥ 128)።





የእግዚአብሔርና የሙሴ መገናኛና መነጋገሪያ ነበር (ዘፀ. 30፥6፤ ዘኁ. 7፥89)። ሙሴ ከሞተ በኋላም የአሮን ካህናት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበትና የሚነጋገሩበት መሆኑ ቀጥሏል (መሳ. 20፥28)።

የቃል ኪዳኑ ታቦት እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ እነዚህን አገልግሎቶች እየሰጠ ዘልቋል። ከዚያ በኋላ ግን ታቦትም ሆነ አገልግሎቱ ከምርኮ በተመለሰውና በአገሩ እንደ ገና መኖር በጀመረው እስራኤላዊ ትውልድ ታሪክ ውስጥ አልታየም። ለምን?

ቀድሞውንም ቢሆን ታቦት እንዲሠራ የታዘዘው፥ እግዚአብሔር ለዘላለም በእርሱ አማካይነት ከመሪዎቻቸው ጋር እንዲገናኝበትና እንዲነጋገርበት አልነበረም፤ ሐዲስ ኪዳን እውን እስኪሆንና እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ ሊናገርበት በወደደው መንገድ ለሕዝቡ እስኪናገር ድረስ እንዲያገለግል ነው። "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" (ዕብ. 1፥1-2) ተብሏል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከተናገረባቸው ብዙ መንገዶች መካከል አንዱ ታቦት ነበር ማለት እንችላለን። በመሆኑም በልጁ የሚናገርበት ዘመን ሲመጣ በታቦት መናገር ማብቃቱ የሚጠበቅ ነበር። ነገር ግን ጊዜው ሳይደርስ በዚያው በብሉይ ኪዳን ዘመን (ከባቢሎን ምርኮ በኋላ) የታቦት አገልግሎት እንዴት ሊያበቃ ቻለ?

እግዚአብሔር የታቦቱ አገልግሎት የሚያበቃበትንና በሌላ የሚተካበትን፥ ከሕዝቡ ጋርም ሌላ ዐዲስ ኪዳን የሚገባበትን ምክንያት ሲናገር፥ በጽላት ተጽፎ በታቦቱ ውስጥ የተቀመጠውን ቃል ኪዳን (2ዜና. 6፥11) ተቀባዮቹ እስራኤላውያን አፍርሰዉት ስለ ተገኙ ነው ይላል (ኤር. 31፥31-33)። በመሆኑም ይህ ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ ሲደርስ፥ ማለትም ከባቢሎን ምርኮ ተመልሰው በአገራቸው መኖርና መብዛት ሲጀምሩ፥ "በዚያ ዘመን፡- የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ብለው ከእንግዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፤ አያስቡትምም፤ አይሹትምም፤ ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም" (ኤር. 3፥16) ተባለ።

## 1.6 ካህናት ታቦቱን የተሸከሙባቸው ጊዜያትና ምክንያቶች

ታቦት የተሠራው (አሮት) ካህናት በትከሻቸው ለመሸከም እንዲያመቻቸው ተደርጎ ነበር (ዘፀ. 37፥5፤ 1ዜና. 15፥15)። መሸከም

ያስፈለገውም ለሌላ ሳይሆን እስራኤል በምድረ በዳ ተጓዦች ስለ ነበሩ ነው። ማደሪያው ድንኳን የሆነውም ከሰፍራ ወደ ሰፍራ ሲጓዙ፥ ከተነሡበት ሰፍራ እንዲነቀልና ባረፉበት ቦታ እንዲተከል ለማድረግ ነበር። ድንኳኑን ለመንቀልና ለመትከል፥ ታቦቱንም ለመሸከም የተመረጠው የሌዊ ነገድ ሲሆን (ዘዳ. 10፥8፤ 31፥9፡25፤ ኢያ. 3፥8፡17፤ 4፥9-10፤ 6፥6፤ 8፥33፤ 1ዜና. 15፥2)፥ ከእነርሱ ውጪ ወደ ታቦቱ ለመቅረብ የተፈቀደለት ማንም አልነበረም። በመሆኑም በዳዊት ዘመን በድፍረት ታቦቱን ለመያዝ የሞከረው ዖዛ ተቀሥፏል (2ሳሙ. 6፥6-7)።

ሙሴ ጽላቱን የተቀበለውና ታቦቱም የተሠራው እስራኤል በጉዞ ላይ እያሉ መሆኑን ከፍ ብለን ለማየት ሞክረናል። ወደ ተስፋዪቱ ምድር ለመጓዝ ከሰፈሩበት ቦታ ሲነሡ፥ ትእዛዙና መመሪያው ተጠብቆ ካህናት ታቦቱን በትከሻቸው ይሸከሙና ጉዞው ይቀጥላል (ዘኍ. 10፥30-36፤ 1ዜና. 15፥15)። "ሙሴም ታቦቱ በተጓዘ ጊዜ፦ አቤቱ፥ ተነሣ፥ ጠላቶችህም ይበተኑ፥ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ ይል ነበር። ባረፈም ጊዜ፦ አቤቱ ወደ እስራኤል አእላፍ አእላፋት ተመለስ ይል ነበር" (ዘኍ. 10፥35-36)።

በጉዞ ላይ እያሉ፥ ካህናት ታቦቱን ተሸክመው የተለያዩ ነገሮችን እንዲያደርጉ ሲታዘዙና የታዘዙትን ሲፈጽሙ ተአምራት ይከናወን ነበር። የእስራኤል ልጆች ሰጢም ከተባለው ሰፍራ ተነሥተው ወደ ዮርዳኖስ ከመጡ በኋላ፥ ሳይሻገሩ ለሕዝቡ "የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናት ተሸክመዉት ባያችሁ ጊዜ ከሰፈራችሁ ተነሥታችሁ ተከተሉት" የሚል መመሪያ ተሰጣቸው። ወደ ታቦቱም እንዳይቀርቡና በተወሰነላቸው ርቀት ብቻ ተከትለዉት እንዲጓዙ ታዘዙ። ካህናቱም እንደ ታዘዙት ታቦቱን ተሸክመዉት በሕዝቡ ፊት በማለፍ እጅግ ሞልቶ በነበረው በዮርዳኖስ ውሃ ዳር እግሮቻቸው ሲጠልቁ፥ ከላይ ይወርድ የነበረው ውሃ ቆመ። ካህናቱም በደረቅ መሬት ላይ መቆም ቻሉ። ሕዝቡ ሁሉ በደረቅ መሬት ተሻገሩ (ኢያ. 3፥1-17)።

ከዚህ በኋላ የእስራኤል ልጆች ኢያሪኮን ለመውረስ ሰባት ቀን ከተማዪቱን እንዲዞሩ ሲታዘዙ፥ ካህናቱም የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ዐብረው ነበሩ። በመጨረሻውም ቀን ሕዝቡ ሲጮኹ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ሲነፉና ሕዝቡ እንደ ገና ታላቅ ጩኸት ሲጮኹ ቅጥሩ ፈረሰ (ኢያ. 6፥1-20)።





በዔሊ ዘመን ደግሞ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ገጥመው ድል በተመቱ ጊዜ፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘው እንደ ገና ተሰልፈው ነበር። ሆኖም ታቦቱ ለምርኮ፥ እነርሱም ለሽንፈት ተዳረጉ እንጂ ድል ማድረግ አልቻሉም፤ ታቦቱን ይዘው ቢዘምቱም እግዚአብሔር ዐብሯቸው አልወጣምና (1ሳሙ. 4፥1-22)። ይሁን እንጂ የፍልስጥኤማውያን አምላክ ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ተዋርዶ፥ የእግዚአብሔርም እጅ ታቦቱን በማረኩት ፍልስጥኤማውያን ላይ ከብዶ ነበር። ከዚህ የተነሣ፥ "እጁ (የእግዚአብሔር) በእኛና በአምላካችን በዳጎን ላይ ጠንክራለችና የእስራኤል አምላክ ታቦት ከእኛ ዘንድ አይቀመጥ አሉ" (1ሳሙ. 5፥6-7)። ታቦቱንም ወደ አገሩ መለሱት።

አቤሴሎም አባቱን ንጉሥ ዳዊትን ከዙፋኑ እንዲሰደድ ባደረገው ጊዜ፥ ካህናቱ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ተሸክመው ወደ ዳዊት መጥተው ነበር። ዳዊት ግን ታቦቱን እንዲመልሱት አዝዞ ወደ ሰፍራው መልሰዉታል (2ሳሙ. 15፥24-29)።

እስካሁን ከተመለከትናቸው ሁኔታዎች እንደምንገነዘበው፥ ካህናቱ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት፥ በእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ የተሸከሙበት ጊዜ አለ። በራሳቸው ፈቃድም የተሸከሙበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር እንዲሸከሙ ባደረገባቸው ጊዜያት ሁሉ ድንቅና ታምራት ሆኗል። በገዛ ፈቃዳቸው ተሸክመውት በወጡ ጊዜ ግን ሽንፈትና ምርኮ ነበር የገጠማቸው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ኖሮ ካላዘዛቸው፥ ወይም እነርሱን የተለየ ነገር ካልገጠማቸው በቀር፥ ታቦቱን ከማደሪያው አውጥተው የሚሸከሙበት ቋሚ ክብረ በዓል አልነበረም። "እግዚአብሔር ጽላቱን የሰጠበት፥ ሙሴ ጽላቱን የተቀበለበት ቀን" ተብሎ እንኳ ለታቦት የመታሰቢያ በዓል አልተሠራም። እስራኤላውያን በሚያከብሯቸው በዓላትም ቢሆን ታቦት እንዲነግሥ የተሰጠ ትእዛዝ የለም (ዘሌ 23፥1-44)። እነርሱም በበዓሎቻቸው ላይ ታቦት ሲያነግሡ አልታየም።

ርግጥ የእግዚአብሔርን ታቦት የማረኩት ፍስጥኤማውያን ወደ አገሩ ከመለሱት በኋላ፥ በመጀመሪያ በአሚናዳብ ቤት በኋላም በአቢዳራ ቤት የተቀመጠውንና በሳኦል ዘመን ያልፈለጉትን (1ዜና. 13፥3) የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ ሲያመጡት የደስታ በዓል አድርገው ነበር (2ሳሙ. 6፥1-19)። ሰሎሞንም ቤተ መቅደሰ ሠርቶ ታቦቱን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ባስገባ ጊዜ እንዲሁ በዓል ተደርጓል

(1ነገ. 8፥1-66)። ይህ ሁሉ ግን ለቃል ኪዳኑ ታቦት የመኖሪያ ለውጥ መደረጉን ተከትሎ አንድ ጊዜ የተከናወነ ሥርዐት እንጂ፥ ቋሚ የሆነ ዓመታዊ የንግሥ በዓል አልነበረም።

የቃል ኪዳኑን ታቦት በየጊዜው ተሸክሞ ማንገሥ እንዳልታዘዘ ግልጽ ነው። የታቦቱ መኖሪያ ወደ ሆነው ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ በዓመት አንድ ጊዜ፥ ያውም ሊቀ ካህናቱ ብቻ ደም ይዞ ከሚገባ በቀር ሁል ጊዜ እንዳይገባ መከልከሉም ለዚህ ፍንጭ ሊሰጠን ይችላል (ዘፀ. 26፥33፤ ዘሌ. 16፥2፤ 1ነገ. 6፥31)። ስለዚህ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እስኪቀመጥ ድረስም ሆነ ከዚያ በኋላ፥ ዐርፎ እንዲቀመጥ ከማድረግ በቀር ታቦቱን መሸከም አላስፈለጋቸውም (1ዜና. 6፥31፤ 2ዜና. 35፥3)።

## 1.7 በዐዲስ ኪዳን ታቦት አለን?

መጽሐፍ ቅዱስ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የቃል ኪዳኑን ታቦት አስመልክቶ ስለ ቀድሞው ታሪኩ ከማውሣት በቀር፥ ከምርኮውም በኋላ በአገልግሎት ላይ እንዳለ አድርጎ ያቀረበበት ሁኔታ የለም። ከምርኮ የተመለሱትም ሕዝብ «ታቦታችንስ?» ሲሉ ጥያቄ አላቀረቡም። በዐዲስ ኪዳን ዘመንም ታቦት የተወሣው በ«ነበር» ነው (ዕብ. 9፥4)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በተመላለሰበትና ባስተማረበት ጊዜ ስለ ታቦት አላወሣም። በተለያዩ ጥያቄዎች ሲፈትኑት የነበሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያንም ሆኑ ሕዝቡ ታቦትን የተመለከተ ጥያቄ አላቀረቡም። ሐዋርያትም በመልእክቶቻቸው የታቦት የአገልግሎት ዘመን ማብቃቱንና በሐዲስ ኪዳን ስለ ታቦት የምንናገርበት ሁኔታ እለ መኖሩን አብራርተዋል (2ቆሮ. 3፥6-11፤ ዕብ. 9፥1-5)።

በራእየ ዮሐንስ ግን በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ መከፈቱና የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ መታየቱ ተጽፏል (ራእ. 11፥19)። ብዙዎችም ታቦት በሐዲስ ኪዳን አልቀረም፤ አለ ለማለት በዋናነት ይህን ክፍል ይጠቅሱታል። ለዚህ ጥቅስ በሊቃውንት የተሰጠው ትርጒም ትክክለኛነት መታየት ያለበት መሆኑ ባያጠያይቅም፥ እንደ ብሉይ ኪዳን ያለው ታቦት በዐዲስ ኪዳንም መኖሩን የሚያረጋግጥ ግን አይደለም። በቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ለዚህ ክፍል የተሰጠው ትርጓሜ፥ «ሕጉን ጠብቃ የምትኖር ምእመን መንግሥተ ሰማይን ወርሳ ክብራ ታየች»[7] የሚል ነው። በዚህ ትርጒም መሠረት ምእመናን ታቦት ተብለዋል ማለት ነው። የኤን.አይ.ቪ. መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ደግሞ፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት፥ "በሕዝቡ መካከል የእግዚአብሔርን ዙፋን ወይም መገኘት ያመለክታል። በዐዲስ ኪዳን ደግሞ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ መሆኑን ያሳያል"[8] በማለት ማብራሪያ ይሰጣል። ሆኖም ክፍሉ በራእይ የተገለጠ ጒዳይ እንደ መሆኑ፥ የቀደመው ታቦት ይሁን ወይም ትእምርታዊነት ያለው ሌላ ታቦት፥ ዛሬ ማንም በርግጠኛነት ሊናገር አይችልም።





በዐዲስ ኪዳን ታቦት ስለ መኖር አለ መኖሩ ማረጋገጫ ከምናገኝባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል አንዱና ዋነኛው፥ እግዚአብሔር በቀደመው ቃል ኪዳን ምትክ ከሕዝቡ ጋር ዐዲስ ቃል ኪዳን እንደሚገባ የተናገረበት የትንቢት ክፍል ነው።

> እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር ዐዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር። ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፤ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፤ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር። ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። (ኤር. 31፥31-34)

ከዚህ ጥቅስ በተለይ፥

- ☛ ዐዲሱ ቃል ኪዳን ቀድሞ እንደ ገባው ዐይነት ቃል ኪዳን አለመሆኑን፤
- ☛ የቀድሞው ቃል ኪዳን በድንጋይ ጽላት የተጻፈ ሲሆን፥ ዐዲሱ ቃል ኪዳን ግን በምእመናን ልብ የሚጻፍ መሆኑን እንገነዘባለን።

---

[7] መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ (1989፤ 423) የራእየ ዮሐንስ 11፥19ን ትርጓሜ ይመልከቱ።

[8] "It symbolized the throne or presence of God among his people. In the NT it symbolizes God's faithfulness in keeping covenant with his people." (The NIV Study Bible 1995, 1938).

በመሆኑም በዐዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥ በድንጋይ የተጻፈ ቃል ኪዳን የለም፤ በዚህ መንገድ የተጻፈ ቃል ኪዳን የተቀበለ ወገንም የለም፡፡ ከቀደምት አበው አንዱ የሆነው ዮሐንስ አፈ ወርቅ፥ የዕብራውያንን መልእክት ባብራራበት ድርሳኑ፥ ብፁዕ ጳውሎስ ዐዲሲቱ ሕግ (ወንጌል) ከአሮጌዪቱ ሕግ (ኦሪት) እንደምትሻል ካስረዳባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ፥ በዐዲስ ኪዳን በታቦት ውስጥ ተቀምጦ የሚጠበቅ የኦሪት ትእዛዝ አለመኖሩ እንደ ሆነ ጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም "ወሐዋርያትሰ ኢነሥኡ ምንተኒ ወኢተወፈዩ ዘተጽሕፈ በረቅ፥ አላ ተወከፉ በሰሌዳ ልበሙ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ - ሐዋርያት በብራና የተጻፈ ሕግ አልተቀበሉም፤ የመንፈስ ቅዱስን ሀብት በልቡናቸው ሰሌዳነት ተቀበሉ እንጂ"[9] ብሏል፡፡

ዐዲሱ ቃል ኪዳን ለተቀበሉት የተሻለና ሊፈጽሙትም የሚችሉት እንደ ሆነ ግልጽ ነው፡፡ የቀድሞው በድንጋይ ጽላት ላይ ተጽፎ በታቦት ውስጥ የሚቀመጥ ነበር፡፡ ታቦቱም ሕዝቡ ሊቀርቡ በማይችሉበትና ሊቀ ካህናቱም ቢሆን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የማስተስረያ ደም ይዞ በሚገባበት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነበር የሚኖረው፡፡ በመሆኑም ሕጉ በብዙ መንገድ ከሕዝቡ ሕይወት ርቆ ይገኝ ነበር፡፡ ዐዲሱ ቃል ኪዳን ግን በምእመናን ልብ ውስጥ ስለሚጻፍ ለሕይወታቸው የቀረበና ለመፈጸምም የሚቻል ነው፡፡ እግዚአብሔርም ስለዚህ ሁኔታ ሲናገር እንዲህ ብሏል፤ "ዐዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ፤ ዐዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የደንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ፡፡ መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ በትእዛዜም እስሄዳችኋለሁ፤ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ፤ ታደርጉትማላችሁ" (ሕዝ. 36፥26-27)፡፡

ሰው ውሳጣዊ ዐይኖቹ ተገልጠው የወንጌልን እውነት ሲያስተውል፥ በዐዲሱ ቃል ኪዳን በክርስቶስ ደም ከኀጢአቱ ነጽቶና ተቀድሶ፥ ሕጉ በልቡ ከመጻፉና የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ከመኖሩ የተነሣ ሕጉንና ትእዛዙን መፈጸም ይችላል፡፡ ከዚህ ውጪ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚጠብቅበትና እርሱን ደስ የሚያሰኝበት መንገድ ፈጽሞ የለም (ዘካ. 4፥6፤ ዮሐ. 15፥5፤ ሮሜ 8፥9-14፤ ገላ. 5፥16፡18፤ ቲቶ 2፥11-14፤ ዕብ. 4፥16፤ 11፥6)፡፡

በዐዲስ ኪዳን ሕገ አምላክ የሚጻፍበት ጽላት የምእመናን ልብ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይናገራል፡፡ "እናንተም በሕያው

[9] ድርሳን ዘዮሐንስ አፈወርቅ (1987፣ 173-173፡277)፡፡





እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው» (2ቆሮ. 3፥3)፡፡ ምእመናን ልባቸው ጽላት ሲባል መላ ሰውነታቸው ደግሞ ቤተ መቅደስ እና የእግዚአብሔር ማደሪያ (ታቦት) ተብሏል (ዮሐ. 1፥14፤ 1ቆሮ. 3፥9፡16-17፤ 6፥19፤ 2ቆሮ. 6፥16[10]፤ ኤፌ. 2፥20-22)፡፡

ለነገሩ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን መቅደስ ይሥሩልኝ ሲል፥ ዐድራለሁ ያለው ግን በሕዝቡ መካከል እንደ ሆነ መዘንጋት የለበትም፡፡ "በመካከላቸውም ዐድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ" (ዘፀ. 25፥8) እንዲል፡፡ ሰሎሞንም ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ሲጸልይ፥ "እነሆ፥ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት ምንኛ ያንስ?" (1ነገ. 8፥27) ብሎ ነበር፡፡ ከእርሱ በኋላ በተነሣው በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነትም እግዚአብሔር ሕዝቡን ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቆ ነበር፤ እንዲህ ሲል፦ "ሰማይ ዙፋኔ ነው፥ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዐይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድን ነው? እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና፤ እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው፡፡" እርሱ ለማደር የሚፈልግበትን ስፍራ ምንነት ሲገልጽም፥ "ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ" ይላል (ኢሳ. 66፥1-2)፡፡ ሐዋርያትም እግዚአብሔር ሰው በሠራው ሕንጻ ውስጥ ሳይሆን፥ ራሱ በሠራው ሕንጻ (በሰው) ውስጥ ብቻ እንደሚያድር አስተምረዋል (ሐሥ. 7፥48-49፤ 17፥24-25)

በርግጥም ከዘላለም የነበረው ቃል ሥጋ ሆኖ ሲመጣ "በእኛ ዐደረ" (ዮሐ. 1፥14) ተብሏል፡፡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መባላችንም፥ "በእነርሱ እኖራለሁ፤ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ" (2ቆሮ. 6፥16) ተብሎ በተነገረው ትንቢት መሠረት መሆኑን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አረጋግጠዋል፡፡ ወደ ፊት በሚገለጠው መንግሥተ እግዚአብሔር ውስጥም "የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱ ጋር ያድራል፤ እነርሱ ሕዝቡ ይሆናሉ፤ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤» (ራእ. 21፥3) ተብሎ ነው የተነገረው፡፡

[10] ዐማርኛው «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ» የሚለውን ግእዙ «ታቦተ እግዚአብሔር» ይለዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ታቦታት በኢትዮጵያ

በክፍል አንድ እንደ ተመለከትነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ጽላት የተሰጠውና ማደሪያውን ታቦት እንዲሠራ የታዘዘው የእስራኤል ሕዝብ ብቻ ነው:: ከዚያ ውጪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽላት የተቀበለም ሆነ ታቦት እንዲሠራ የታዘዘ ሕዝብ በምድር ላይ ፈጽሞ የለም:: እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት ታዲያ የት ደረሰ? የኢትዮጵያ ታቦታትስ ከየት መጡ? በኢትዮጵያ ታቦት የተባለው ስሌዳ አሁን ባለው ሁኔታ እንዲዘጋጅ ያዘዘውስ ማነው? የሚሉትንና ተያያዥ ጥያቄዎችን በማንሣት፥ በዚህ ምዕራፍ ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት አንዳንድ ነጥቦችን እንመለከታለን::

### 2.1. የቃል ኪዳኑ ታቦት በአሁኑ ጊዜ የት ይገኛል?

ባለፈው ክፍል ለማሳየት እንደ ተሞከረው ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚናገረው ነገር የለም:: ሌሎች መረጃዎች ግን የቃል ኪዳኑ ታቦት ያለበትን ስፍራ በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦችን ይሰነዝራሉ::

#### 2.1.1. የብሉይ አዋልድ መጻሕፍት ምስክርነት፤

የቃል ኪዳኑ ታቦት የት ደረሰ? ለሚለው መልስ የለሽ ጥያቄ "የብሉይ አዋልድ" ወይም "የብሉይ ኪዳን ተጨማሪ መጻሕፍት (ዲዩትሮካኖኒካል)" ከሚባሉት መጻሕፍት መካከል መልስ ለመስጠት የሚሞክሩ አሉ::

*መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል* እንዲህ ይላል፤ "ቤተ መቅደሳችን እንደ ፈረሰ፥ መሠዊያችን እንደ ተሰባበረ አታዩምን? ግናያቱ እንደ ጠፋ፥ ምስጋናችን እንደ ቀረ፥ ዘመራ ዘውዳችን እንደ ወደቀ፥ የመቅረዛችን መብራት እንደ ጠፋ፥ የቃል ኪዳናችን ታቦት እንደ ተማረከች፥ ንዋየ ቅድሳታችን እንዳደፈ ... አታዩምን?" (ዕዝራ ሱቱኤል 9፥21፡22 /የ2000 ዓ.ም. ዕትም/)::

*መጽሐፈ ዕዝራ ካልእ* ደግሞ ታቦቱ የደረሰበትን ስፍራ እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ "የእግዚአብሔርንም ንዋየ ቅድሳት ትልቁንም ትንሹንም ሁሉ፥





የእግዚአብሔርንም ታቦት፥ የንጉሡንም ቤት ዕቃ ሁሉ ዘርፈው ወደ ባቢሎን ወሰዱ" (1፥54 የ2000 ዓ.ም. ዕትም)::

ሁለቱም መጻሕፍት የቃል ኪዳኑ ታቦት በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ተማርኮ ወይም ተዘርፎ ወደ ባቢሎን መወሰዱን ነው የሚተርኩት:: ከዚህ በፊት ለማሳየት እንደ ተሞከረው ግን፥ ታቦቱ ወደ ባቢሎን አለ መሄዱ የተረጋገጠ ስለ ሆነ ይህ ትረካ እውነትነት የለውም::[11]

ተረፈ ኤርምያስ ከእነዚህ በተቃራኒው ታቦቱ ወደ ባቢሎን አለ መማረኩንና ምድር እንድትውጠው መደረጉን በመናገር፥ የተለየ ምስክርነትን ይሰጣል:: "ባሮክና ኤርምያስም ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፤ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጧት፤ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው" ይላል (8፥13 የ1980 ዕትም):: በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት ንዋያተ ቅድሳት መካከል አንዱ ታቦት ነበረ:: ስለዚህ በተረፈ ኤርምያስ ትረካ መሠረት ባሮክና ኤርምያስ ለምድር ከሰጧትና ምድርም ተቀብላ ከዋጠቻቸው ዕቃዎች መካከል አንዱ ታቦቱ ነበር ማለት ነው:: ይህ ትረካ ስለ ቤተ መቅደሱና በውስጡ ስለ ነበሩት ንዋያተ ቅድሳት መጨረሻ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር የሚስማማ አይደለም (2ዜና. 36፥17-21)::

እነዚህን ከላይ የቀረቡትን ሦስት የብሉይ አዋልድ ምስክርነቶችን ቤተ ክርስቲያናችን እንዴት ታያቸዋለች? የዕዝራ ሱቱኤልን ምስክርነት በሚመለከት፥ "ዕዝራ ሱቱኤል ቤተ መቅደስ መዘረፉን ለማመልከት ሲል፣ ታቦተ ጽዮን ተማረከች አለ እንጂ፣ ታቦተ ጽዮን ተማርካ ወደ ባቢሎን አልሄደችም"[12] ሲል የኢኦተቤክ የሊቃውንት ጉባኤ የታቦቱን መማረክ ያስተባብላል:: ይሁን እንጂ ዕዝራ ሱቱኤል ተማረከ ያለው ታቦቱን ብቻ አይደለም፤ በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚገኙትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ ነው:: ታዲያ አባባሉ የቤተ መቅደሱን መዘረፍ ለማመልከት ነው የሚል ትርጉም እንዴት ሊሰጠውና በዚሁ ብቻ ሊታለፍ ይችላል? ታቦቷ አልተማረከችም ማለትስ በምን ማስረጃ የተደገፈ አስተያየት ነው? ምናልባት ወደ ባቢሎን ተማረከች የሚለው ነገር ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች የሚለውን ትረካ የሚያሳብል ሆኖ ስለ ተገኘ ይሆን ወደ

[11] ስለዚህ ጉዳይ በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 11 ላይ «የታቦት መኖሪያ» በሚለው ርእስ ሥር የተጻፈውን ይመለከቷል::

[12] ሁቁ ኢያስሕቀከሙ (1996፣ 63)::

ባቢሎን አልተማረከችም የተባለው? የሊቃውንት ጉባኤ ይህን በግልጽ ማብራራት ይጠበቅበታል።

የሊቃውንት ጉባኤው "ታቦቱ ወደ ባቢሎን ተማረከ" ከሚለው ይልቅ፥ "ኤርምያስ ምድር እንድትሰውረው አደረገ" የሚለውን የተረፈ ኤርምያስን ሐሳብ የደገፈ ይመስላል። ምክንያቱም፥ "ኢየሩሳሌም በተወረረች ጊዜ፣ ኤርምያስ ቤተ መቅደሱን ከነሙሉ ዕቃው፣ ንዋየ ቅድሳቱን ምድር እንድትሰውረው አደረገ (ተረ. ኤር. 8፥13) ይላል"[13] በማለት ወደዚህ ጥቅስ አዘንብሏል። የተረፈ ኤርምያስን ሐሳብ ለማጉላበትም ይመስላል፥ ያለ አንዳች ማስተባበያ ተጨማሪ ሐተታና ጥቅስ አስፍሯል፤ እንዲህ በማለት፥

> ታቦተ ጽዮንን፣ ኤርምያስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ባልታወቀ ስፍራ እንደ ሰወራት በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ (2ኛ መቃቢስ ም.፤ ቊ.4) ላይ ይናገራል። ኤርምያስም እግዚአብሔር የምሕረቱን ፊት እስኪመልስና ሕዝቡንም እስከሚሰበስብ ድረስ፣ ጽላቱዋ እንዳትገኝ በእግዚአብሔር ቃል አዳኝቶአል።[14]

የሊቃውንት ጉባኤው ወደዚህ ሐሳብ ካጋደለ፥ ታቦቱ እንዲሰወር ተደርጓል የሚለው አመለካከት በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀባይ አግኝቷል ማለት ነው። እንዲህ ከሆነም ከኤርምያስ ብዙ ምእት ዓመታት ቀደም ብሎ በሰሎሞን ጊዜ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለው አስተሳሰብ በጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ ይሆናል። ይሁን እንጂ የሊቃውንት ጉባኤው ይህን የተረፈ ኤርምያስን ሐሳብ ሳያስተባብል እንዳለ ተቀብሎ፥ "ሌዋውያን፣ በሊቀ ካህናቱ በአዛርያስ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፣ ከላይ እንደ ተገለጸው በእርግጥ ሕገ ኦሪትንና ጽላተ ሙሴን ይዘው መጥተዋል (መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ም. ፤፡3-4፤ ይመለከቷል)"[15] ወደ ማለት ተሸጋግሯል።

እዚህ ላይ የቃል ኪዳኑ ታቦት አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ከተባለ፥ ኤርምያስ እንዳትገኝ አድርጎ የሰወራት የትኛዋን ታቦት ነው የሚል ጥያቄን ያስነሣል። መቼም በእስራኤል ታሪክ አንድ ታቦት ብቻ

---

[13] ዝኒ ከማሁ።
[14] ዝኒ ከማሁ።
[15] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 64)።





ስለ ነበር ያንኑ ታቦት ነው እንዳይባል፥ ታቦቱ ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ተብሏል። ሌላ ነው እንዳይባልም በእስራኤል ታሪክ ሌላ ታቦት አልነበረም። ማስረጃ ተብሎ የተጠቀሰው መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ 1፥3-4፤ የሚናገረው ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መምጣቱ አይደለም፤ በኢዮስያስ ዘመን ስለ ሆነው ነገር ነው። የሊቃውንት ጉባኤው ግን ኢዮስያስ፥ ሰሎሞን ባሠራው መቅደስ ውስጥ አኑሩት ያለው የቃል ኪዳኑ ታቦት፥ "እግዚአብሔር ለሙሴ ሌላ ጽላት እንዲቀርጽ በፈቀደለት መሠረት የተቀረጸ ጽላት እንደ ሆነ የታመነ ነው"ይላል።[16]

ይህ አስተያየት ሙሴ ተቈጥቶ በሰበራቸው ምትክ፥ ሌሎችን ጠርቦ ወደ እግዚአብሔር ካቀረባቸውና እግዚአብሔርም በጣቶቹ ከጻፈባቸው ሁለት የድንጋይ ጽላት በተጨማሪ፥ ተፈቅዶለት የቀረጸው ሌላ ጽላት ያለ አስመስሎ ነው ያቀረበው። ከዚያ የመጀመሪያዎቹ ጽላቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። ተፈቅዶለት የጠረበው ደግሞ በኢዮስያስ ዘመን በመቅደሱ ውስጥ ነበረ ወደሚል ድምዳሜ ነው የሚወስደው። ሙሴ ግን ከመጀመሪያዎቹ ጽላት በቀር የጠረባቸውና እግዚአብሔር የጻፈባቸው ሌሎች ጽላቶች ፈጽሞ የሉም። ስለዚህ አስተያየቱ በመረጃ ያልተደገፈ ነው። ዞሮ ዞሮ ግን አስተያየቱ ወደ ክብረ ነገሥት ትረካ ነው የሚወስደው።

በአጠቃላይ እነዚህን የብሉይ አዋልድ መጻሕፍት የምትቀበለው ቤተ ክርስቲያናችን፥ ከታቦቱ ጋር የተገናኘውን የመጻሕፍቱን ትረካ ብዙም ትኩረት የሰጠችው አይመስልም። ከእነርሱ ይልቅ ለክብረ ነገሥት ትረካ ነው ቦታ የሰጠችው ማለት ይቻላል።

### 2.1.2. ክብረ ነገሥትና ምስክርነቱ

ክብረ ነገሥት የተባለውና እርሱን ምንጭ አድርገው የተጻፉ አያሌ መጻሕፍት የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣና በአክሱም እንደሚገኝ ይተርካሉ። ለመሆኑ ክብረ ነገሥት ለምን ዐላማ ተጻፈ? ማንስ ጻፈው?

---

[16] ዝኒ ከማሁ።

ክብረ ነገሥት ከ912-1270 ዓ.ም. ድረስ ሰሎሞናውያን ያልሆኑ የዛጔዌ ዘሮች ነግሠው ስለ ነበር፥ መንግሥቱን ለሰሎሞናውያን ለማስመለስ ሲባል የተጻፈ መጽሐፍ መሆኑ የታሪክ አደባባይ ምስጢር ነው።

> ይህ መጽሐፍ የተደረሰው በአገር ውስጥ ሲሆን፥ የተደረሰበትም ዐላማ እላይ እንደ ተጠቀሰው የሰሎሞናውያንን ሥርወ መንግሥት ከዳዊት ጋር ለማያያዝና ከዚህም የተነሣ ከክርስቶስም ጋር ያላቸውን [የ]ሥጋ ዝምድና ለማሳየት ነው። ይህ ፖለቲካዊ ዐላማ የነበረው መጽሐፍ ምንም እንኳ አብዛኛውን ተረት የመሰለና ከእውነት የራቀ ወሬ የያዘ መጽሐፍ ቢሆንም እስከ ቅርቡ ዘመናችን ድረስ ዋጋ የሚሰጠው መጽሐፍ ነበር።[17]

ክብረ ነገሥት ስለ ራሱ እንደሚመሰክረው ደግሞ ዘመኑን ራቅ አድርጎ በንጉሥ ሰሎሞን ጊዜ መጻፉን ይተርካል። "በተጨማሪም ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት፣ ደማትዮስ ዘሮም ወይም ዘአንጾኪያ እና 318 አበው የመጽሐፉ አስረጂ ገጸተ ባሕርያት ሆነው ቀርበዋል። እነዚህ ሰዎች የዐዲስ ኪዳን አባቶች መሆናቸው ይታወቃል።"[18] ቀደም ብሎ ከቅብጢ ወደ ዐረብኛ፥ በኋላም ከዐረብኛም ወደ ግእዝ ንቡረ እድ ይሥሐቅ በተባሉ ሰው እንደ ተተረጐመ ይናገራል። ይሁን እንጂ በውስጡ እስከ ዐፄ ዐምደ ጽዮን (በ14ኛው ምእት ዓመት) ድረስ ያሉትን አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ነገሥታትን ስለሚጠቅስ ተጻፈ እንጂ ተተረጐመ የሚለውን አጠራጣሪ ያደርገዋል።

"በክርስትና ሃይማኖት ላይ መንፈሳዊና ሞራላዊ ሥልጣን ባላቸው … አባቶች ስም መጻሕፍትንና ቀኖናዎችን መጻፍ ዐዲስ ነገር አይደለም።"[19] ከዚህ ዐለፍ ሲል ደግሞ "ከሰማይ ወረደ" ወይም "መልአክ አጻፈው" ወደ ማለት ይደረሳል። ተክለ ጻድቅ፥ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፤

> የዛሬም ዘመን ሕዝብ ይልቁንም የዚያን ጊዜ ሕዝብ የሚያውቀውና ወገኑ ያዘጋጀውን መጽሐፍ አክብሮ አድንቆ መቀበል ያዳግተዋል። ስለዚህ ሌሎች አረማውያንም እስላሞችም እንደሚያደርጉት ብዙ

[17] አምሳሉ (ዶ/ር) (1976፣ 38)።

[18] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 8)።

[19] ዝኒ ከማሁ።





> የክርስቲያን ጸሐፊዎች ገድልም ድርሳንም ጽፈው ከሰማይ ወረደ ወይም መልአክ አጻፈው እማለት ደርሰዋል። … ስለዚህ እነንቡረ እድ ይሥሐቅ ከሰማይ ወረደ ማለት እንዳይበዛ ሕዝቡና ካህናቱ ከሚያከብሩት ከማርቆስ ወንበር ወጣ ብለው በዘዴ ሕዝቡ እንዲቀበል አድርገውት እንደ ሆነ አይታወቅም።[20]

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተመዘገቡ የተለያዩ ሥርዐቶችንና ልማዶችን እናገኛለን። ርግጥ እነዚህ ሥርዐቶችና ልማዶች የግድ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ይሁኑ ማለት አይቻል ይሆናል፤ ነገር ግን ሥርዐቶቹንና ልማዶቹን ስማቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ሰዎች እንደ ጀመሩት አድርጎ ማቅረቡ ነው ችግሩ። ይህን የሚያደርጉትም ከላይ እንደ ተገለጸው የጸፉትን ድርሰት ሰዎች እንዳያናንቁባቸውና ተቀባይነትን እንዲያገኙላቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

እንዲህ ያለው አቀራረብ ግን ቢያንስ ሁለት ጉዳቶች አሉት። የመጀመሪያው ጉዳት ከእግዚአብሔር ያልሆነን ነገር ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ አድርጎ ማቅረብና ሕዝብን ማሳሳት ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ፥ በተለያየ መስክ ጥናት ማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች ቢኖሩ፥ ነገሩ መቼ ተጀመረ? ማንስ ጀመረው? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች እውነተኛ ምላሽ እንዳያገኙ ዕንቅፋት ይፈጥራል፤ የተሳሳተ የጥናት ውጤት ላይም ያደርሳል።

ክብረ ነገሥት መንፈሳዊ ተደርጎ ይወሰድ እንጂ ዋና ዐላማው ፖለቲካ መሆኑ አያጠራጥርም። ሃይማኖታውያን ጉዳዮችን ለፖለቲካ መሣሪያነት የተጠቀመበትና ለዚህም ሲባል እውነታዎችን በማዛባት ያቀረበበት ሁኔታ በብዛት ይስተዋላል። በተለይ ስለ ታቦት የተጻፈው ድርሰት ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው።

መጽሐፉ እግዚአብሔር ታቦተ ሕግን ከፍጥረት ሁሉ በፊት እንደ ሠራት አድርጎ ያቀርባል።[21] እንዲያውም፥ "የእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ለሆነችው ለጽዮን ግን አስቀድሞ ሰማይን ሠራ"[22] ይላል። በመቀጠልም ለኖኅ እንዲህ ማለቱን ጽፏል።

[20] 1966፣ 47)።

[21] ክብረ ነገሥት (1994፣ 1፡6)።

[22] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 9)።

> በራሴና ለመማለጃና ለሰዎች መድኀኒት በፈጠርኳት፣ በኋላም ለዘርህ በማወርዳት፣ በምድር ላይ የልጆችህን መሥዋዕት በምቀበልባት የቃል ኪዳን ታቦት ሆና ለዘላለሙ ከእነርሱ ጋር በምትኖር ቢቃል ኪዳኔ ታቦት በጽዮን እምላለሁ፡፡ ደመናም በመጣ ጊዜ እንዳይፈሩና የጥፋት ውሃ እንዳይመስላቸው ከጽዮን አዳራሽ የሕግ ታቦቴን የሚጋርዳትን የቃል ኪዳኔን ቀስት አወርዳለሁ፡፡ ይህም ቀስተ ደመና ነው፡፡[23]

ለኖኅ ምልክት ተደርጎ የተሰጠውን ቀስተ ደመናንና ታቦትን ምን አገናኛቸው? እንኳ በሰማይ በምድርም ቀስተ ደመና ታቦቱን ስለ መጋረዱ የተጻፈ ነገር የለም፡፡ አስቀድሞ ሙሴ የማደሪያውን ድንኳንና በውስጡ የሚገኙትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ፥ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ሠርቶ በፈጸመ ጊዜ ድንኳኑን ከድኖ የነበረው፥ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የሆነው ደመና ነው እንጂ፥ ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውሃ ላለማጥፋት ምልክት ሆኖ የተሰጠው ቀስተ ደመና አልነበረም (ዘፀ. 40፥35-37)፡፡ ሰሎሞን በሠራው መቅደስ ውስጥ ካህናት ማገልገል እስኪሳናቸው ድረስ ሞልቶ የነበረው ደመናም ተመሳሳይ ነበር እንጂ ቀስተ ደመና አልነበረም፡፡

ለአብርሃም ደግሞ፥ "... የቃል ኪዳኔንም ታቦት ከአንተ በኋላ በሰባት ትውልድ በምድር ላይ አወርዳታለሁ፡፡ ከዘርህም ጋር ትመላለሳለች፡፡ ለዘመድህም መድኀኒት ትሆናለች"[24] በማለት መናገሩን አስፍሯል፡፡ ይሁን እንጂ ለሙሴ የሚሠራበትን አምሳል መስጠቱንና እርሱም ከማይነቅዝ ዕንጨት ታቦቱን መሥራቱን ይተርካል፡፡[25] በዚህም እግዚአብሔር ለኖኅና ለአብርሃም "ከሰማይ ወደ ምድር አወርዳታለሁ" አለ የተባለው ተፈጻሚ ሆኖ አይታይም፡፡

ክብረ ነገሥት ቀድሞውንም በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈና ያልታወቀ ዐዲስ ታሪክ ፈጥሮ አቀረበ እንጂ የፈጠረው ታሪክ ተፈጻሚ ሆኖ ማሳየት አልቻለም፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ታቦታት የዚያን ዘመን ኪሥተት ሳይሆኑ፥ ሥርዐቱ በሰማይ የተጀመረ እንደ ሆነ ለማሳየትና ሰው ልዩ አክብሮት እንዲሰጠው ለማድረግ የተፈጠረ መላ ይመስላል፡፡

---

[23] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 5)፡፡
[24] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 8)፡፡
[25] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 9)፡፡





ከዚህ ሁሉ በኋላ ባስልኤል የሠራውና ክብረ ነገሥት "ታቦተ ጽዮን" እያለ በሴት አንቀጽ (ጾታ) የሚጠራት ታቦት፥ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣችና በአክሱም እንደምትገኝ ይተርካል፡፡ ትረካው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰሎሞንና ስለ ንግሥተ ሳባ ግንኙነት (1ነገ. 10፥1-13፤ 2ዜና. 9፥1-12) ያስፈረውን ታሪክ ጫፍ በመያዝና በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተመዘገቡ አፈ ታሪኮችን በማከል የቀረበ ነው፡፡

እንደ ትረካው ከሆነ ንግሥተ ሳባ ሰሎሞንን ለመጐብኘት በሄደች ጊዜ ከእርሱ ፀንሳ ተመለሰች፡፡ ወንድ ልጅም ወለደች፡፡ እርሱም ቀዳማዊ ምኒልክ የተባለው ነው፡፡ 22 ዓመት ሲሆነውም አባቱን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ በዚያም ከሰሎሞን ጋር ተገናኝቶ "እኛና ከእኛ በታች ያሉት የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች በዘመናችን ሁሉ እንሰግድላት ዘንድ ከእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ከልብሷ ጫፍ ስጠን አለው፡፡"[26] ሰሎሞንም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ እንዳይሄድና ከእርሱ በኋላ በእስራኤል ላይ እንዲነግሥ ለመነው፡፡ ምኒልክ ግን ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ ሰሎሞን ምኒልክን እንግሦ ካህኑ ሳዶቅ የእግዚአብሔርን ፍርድና አገዛዝ እንዲያስተምረው አዘዘ፡፡ ከዚያም የእስራኤል መኳንንት ልጆች ዐብረዉት እንዲሄዱና አለቃ ሆነው በቀኝና በግራው እንዲቀመጡ አደረገ፡፡ ያስተምሩ ዘንድም ካህናትን ለመላክ ወሰነ፡፡

ከምኒልክ ጋር ዐብረው እንዲሄዱ የታዘዙት የመኳንንትና የካህናት ልጆችም፥ ሀገራቸውን፣ ዘመዶቻቸውንና የሀገራቸውን ሰዎች፣ ይልቁንም ታቦተ ጽዮንን ትተው የሚሄዱ በመሆናቸው ማዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ከዚያ የካህኑ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስ ባቀረበው ሐሳብ መሠረት ታቦተ ጽዮንን ደብቀው ለመውሰድ ይማማላሉ፡፡ ወደ እግዚአብሔርም ቤት በሄዱ ጊዜ ከውጪ እስከ ውስጥ በሮቹ ተከፋፍተው፥ ታቦተ ጽዮን "እንደ ቅጽበተ ዐይን ተነሣች፡፡" ቢታቦተ ጽዮን ልክ ዕንጨቶችን አገጣጥመው በቦታዋ በማስቀመጥ በጽዮን ልብስ ሸፈኗቸው፡፡ ተሰነባብተው ሲሄዱም ታቦተ ጽዮንን "ከአልባሌ ዕቃዎች ጋር በቆሻሻ ልብሶች በሰረገላ ላይ" ጭነው ወደ ኢትዮጵያ ይዘዋት መጡ፡፡

ታቦተ ጽዮን በስርቆት መወሰዷ በታወቀ ጊዜም፥ በሀገረ እስራኤል ከፍተኛ ልቅሶና ዋይታ እንደ ሆነና ታቦታቸውን ለማስመለስ

---

[26] ዝኒ ከማሁ ገጽ 30፡፡

ተከትለዋቸው እንደ ነበር ተተርኳል። ሆኖም የእነ ምኒልክ ጉዞ በመልአኩ ሚካኤል መሪነት ተአምራዊ በሆነ መንገድ፥ እነርሱና ጓዛቸው በአጠቃላይ ከምድር አንድ ስንዝር ከፍ ብለው በመንሳፈፍ ይጓዙ ስለ ነበር ሊደርሱባቸው አልቻሉም። ንጉሥ ሰሎሞንም ከእስራኤል ሊቃውንት ጋር ወደ ቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ገብቶ አለቀሰ። ቀጥሎም እንዲህ አለ።

> ከብራቸው ፈረሰ እግዚአብሔርም ተዋቸው ብለው ያልተገረዙት ወገኖች በላያችን ላይ እንዳይመኩ ተውት፤ ከእንግዲህ በኋላ ለሌሎች ወገኖች አትግለጹት። እነዚህን የተጠጋጉና የተያያዙ ጠፍጣፋ ገቢታዎች ግን አሁኑኑ እንቀድሳቸው። በወርቅም እንለብጣቸው። በእመቤታችን በጽዮን ምሳሌም እንሸልማቸው። በውስጧም የሕጉን መጽሐፍ እናስቀምጥ።[27]

ይህ ትረካ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ከሚናገረው ፍጹም ተቃራኒ ነው። በርካታ የእውነታ ተፋልሶ ይታይበታል። በመጽሐፉ የተዘረዘሩትን ብዙ ሕጸጾች ትተን በቀረበው ጭምቅ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱትን እንኳ ብንመለከት፡-

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት በአንድም ስፍራ በሴት አንቀጽ እና "ታቦተ ጽዮን"፤ "እመቤታችን ታቦተ ጽዮን" "ጽዮን" በሚሉ ስሞች ፈጽሞ አልተጠራም። ክብረ ነገሥት ግን በብዛት የሚጠቀመው እነዚህን ስሞች ነው።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ሲቀመጥ፥ በስርየት መከደኛ ከሚከደን በቀር፥ መጐናጸፊያ የሚሆን ልብስ የለውም። እስራኤል በምድረ በዳ ተጓዦች በነበሩ ጊዜ ለመጓዝ ሲነሡ ግን፥ "አሮንና ልጆቹ ገብተው የሚሸፍነውን መጋረጃ ያውርዱ፥ የምስክሩንም ታቦት ይጠቅልሉበት፤ በላዩም የአቆስጣውን ቍርበት መሸፈኛ ያድርጉበት፥ ከእርሱም በላይ ሁለንተናው ሰማያዊ የሆነ መጐናጸፊያ ይዘርጉበት" (ዘኍ. 4፥5-6) ተብሏል። የክብረ ነገሥት ታቦተ ጽዮን ግን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ በልብስ የምትሸፋፈን ናት።

[27] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 16-64)።





ሰሎሞንም ለልጁ ለምኒልክ "የጽዮንን ልብስ አምልክበት"[28] ብሎ እንደ ሰጠው ተጠቅሷል።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኪዳኑ ታቦት ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት የሚፈቀድለት ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር። እርሱም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንጂ በፈለገው ጊዜ ሁሉ እንዲገባ መብት አልተሰጠውም። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱ ሲመረቅ በእግዚአብሔር ፊት የጸለየው በእግዚአብሔር መሠዊያ ፊት ሆኖ ነው (1ነገ. 8፥22)። እርሱም የሚገኘው ከቅድስተ ቅዱሳን ውጪ በመቅደስ ውስጥ ነበረ (1ነገ. 7፥48-49)። ክብረ ነገሥት ግን የሌዊ ወገን ያልሆኑት ሰሎሞንና የእስራኤል ሊቃውንትም የቃል ኪዳኑ ታቦት ስፍራ ወደ ሆነው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ገቡ ይላል።

- ካህኑ ሳዶቅ በዳዊትና ሰሎሞን በነገሠባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ያገለገለ ካህን መሆኑ ይታወቃል (2ሳሙ. 8፥17፤ 1ነገ. 2፥35)። በኋላ ላይ ግን ከተሾሙት አለቆች መካከል ልጁ ካህኑ አዛርያስ አንዱ ነበር (1ነገ. 4፥1-2)። ስለዚህ አዛርያስ ከምኒልክ ጋር ዐብሮ ሊሄድ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። ክብረ ነገሥት እንደ ጻፈውም ከምኒልክ ጋር እንዲሄዱ የተደረጉት የካህናትና የመኳንንት ልጆች ናቸው እንጂ አለቆች አይደሉምና፥ አዛርያስ ወደ ኢትዮጵያ መጣ የሚለው አጠያያቂ ይሆናል።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ እንደምናነበው ታቦቱን ደብቆ ለመውሰድ ቀርቶ በድፍረት ለመንካት እንኳ የማይቻል ነው። አዛርያስ አደረገ በተባለው የስርቆት ተግባር ከእግዚአብሔር ዘንድ በሕልም የተደገፈ ምሪትና ተኣምር ሊደረግለት ቀርቶ በዖዛ ላይ የደረሰው ቅሥፈት በእርሱም ላይ በመጣበት ነበር።

- ሰሎሞን የታቦቱን መወሰድ ተመልክቶ፥ ምስጢሩ እንዲደበቅ አደረገ መባሉና፥ ወሳጆቹ በታቦቱ ምትክ ያስቀመጧቸውን ጠፍጣፋ ገበታዎች (ፎርጅድ ታቦት) «እንቀድሳቸው። በወርቅም እንለብጣቸው። በእመቤታችን በጽዮን ምሳሌም እንሸልማቸው። በውስጧም የሕጉን መጽሐፍ እናስቀምጥ» አለ መባሉ አንድም የእግዚአብሔር ሐሳብ

[28] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 49)።

የለበትም፡፡ ሰሎሞንም እንዲህ አድርጎ ቢሆን ኖሮ ጣዖት እንደ ሠራና ሕዝቡን እንዳሳተ በተቈጠረ ነበር፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በእርሱ ትእዛዝ በተሠራው በቃል ኪዳኑ ታቦት ኀያልነቱንና ታላቅነቱን ሲገልጽ ነበር፡፡ በክብረ ነገሥት እንደ ተተረከው ግን በሰሎሞን ጊዜ በታቦቱ ላይ ከላይ የተገለጸውን የመሰለ ተግባር ሲፈጸም እግዚአብሔር ዝም ማለቱ፥ ወይም የድርጊቱ ተባባሪ ተደርጎ መቅረቡ በእግዚአብሔር ላይ መዋሸት ይሆናል፡፡

## 2.1.3. የቃል ኪዳኑ ታቦት በዛጉዌዎች አፈ ታሪክ፤

በዛጉዌዎች በኩል ስለ ክብረ ነገሥት የሚታመነው በሰሎሞናውያን ዘንድ ከሚታመነው የተለየ ነው፡፡ እንደ እነርሱ እምነት ክብረ ነገሥት፥ "የላስታ-ዋግ (የዛጉዌ) ሥርወ መንግሥት ዝርያዎች፣ ሰሎሞናውያኑ ሕጋዊ ሰነድ እንዲሆናቸው ባሰፈለሰፉት ክብረ ነገሥት አማካይነት፣ ከሥልጣነ መንግሥት በራፍ ለአንድዬና [ለአንዴና] ለመጨረሻ ጊዜ ድርሽ እንዳይሉ የጠነሰሱት ሤራ ነው፡፡"[29] በተጨማሪም "ልቦለድ መጽሐፍ"[30] ነው፡፡ ምንም እንኳ ክብረ ነገሥት ከመቃብረ ማርቆስ መገኘቱ በመጽሐፉ ውስጥ ቢጠቀሰም፥ "በፀረ ላስታ ዋግ (ዛጉዌ) ሥርወ መንግሥት ቀጥተኛ ተሳትፎ የእስከንድርያ መንበረ ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ከእነርሱ ጋር ይኖር የነበሩ[ረ] ሰሎሞናዊ ነኝ በማለት ዙፋን ይመኝ የነበረው አካል ደጋፊዎች የሆኑ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት እጅ"[31] እንደ ነበረበት ይገመታል፡፡

በሌላ በኩል ግን እንደ ሰሎሞናውያኑ ሁሉ ዛጉዌያውያንም የዳዊት ዘር መሆናቸውን የሚገልጽ አፈ ታሪክ አላቸው፡፡ አፈ ታሪኩ የተዘጋጀውም እነርሱ ያልተገባቸውን መንግሥት ከሰሎሞናውያን በሕገ ወጥ መንገድ መውሰዳቸውን የሚያትተውን የክብረ ነገሥትን ሐሳብ ለማስተባበል እንደ ሆነ ይነገራል፡፡ ይኸውም ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን ሄዳ ከእርሱ ፀንሳ በተመለሰች ጊዜ፥ ደንገጡሯ ወይም የቅርብ አሿዋጇ ከሰሎሞን እንደ ፀነሰችና ዛጌ የተባለ ወንድ ልጅ እንደ ወለደች፥ እርሱም የአገዎች ቅድመ-ቅድመ አያት እንደ ሆነ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ምኒልክ በ22 ዓመቱ ወደ

[29] አያሌው (ዶ/ር)(አልቦ ዓ.ም. ፣ 205)፡፡
[30] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 204)፡፡
[31] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 205)፡፡





ሰሎሞን በሄደ ጊዜ ዛጌም ዐብሮት እንደ ሄደና ሲመለሱ ታቦተ ጽዮንንና ታቦተ ሚካኤልን ይዘው እንደ ተመለሱ ይተርካል፡፡[32]

ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ በጻፈው የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ላይ ደግሞ፥ በዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ውስጥ ስለ ነበረው ንጉሥ ላሊበላ፥ አንድ የአርመን ተወላጅ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ እንዲህ ሲል መጻፉን ተከለ ጻድቅ ጠቅሰዋል፡፡

> የሐበሻው ንጉሥ ከዳዊት ዘር የመጣ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሙሴ ከዚያ አገር ንጉሥ (ኢትዮጵያን?) በተጋባ ጊዜ ከሁለቱ ዘር የወረደ ነው ይባላል፡፡ … ዐሠርቱ ቃላትን እግዚአብሔር በእጁ የጻፈበት ሁለት የቃል ኪዳኑ ድንጋዮች (ጽላተ ሙሴ) በአበሾች እጅ አለ፡፡ እሱም በቤተ መቅደስ በምሥዋዑ ላይ በወርቅ በተለበደ እንደ ቁም ሣጥን ባለ ላይ ተቀምጧል፡፡ ለልደት፣ ለኤጲፋንያ (ለጥምቀት)፣ ለፋሲካ፣ ለመስቀል በዓል በዓመት አራት ጊዜ ወጥቶ ከቤተ ክርስቲያኑ እስከ ቤተ መንግሥቱ ድረስ በታላቅ ከብር ድባብ ተይዞለት ይሄድና (ዑደት ይደረግና) ቅዳሴ ይቀደሳል፡፡[33]

ይህም ትረካ ታቦቱ በዛጉዌዎች ዘንድ እንዳለ አድርጎ የሚያቀርብ ይመስላል፡፡

ይሁን እንጂ "የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ታሪክ" ጸሐፊ ዶ/ር አያሌው ሲሳይ፥ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ጽላትን በተመለከተ ያቀረበው ሐሳብ በትክክል ያልተቀመጠ ነው ይላሉ፡፡ አክለውም፥ "በአፈ ታሪክ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣች የሚነገርላትና በእግዚአብሔር እጅ ዐሠርቱ ቃላተ አሪት የተጻፉባት ጽላተ ሙሴ አለች የሚባለው በአክሱም ብቻ ነው፡፡ ጸሐፊው ግን ስለ ማንኛውም ተራ /ቅጅ/ ጽላት የሚናገር ይመስላል፡፡ ዑደት ተደርጎ ተመልሶ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ ይላልና"[34] ብለዋል፡፡

[32] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 8)፡፡
[33] (1951፣ 417)፡፡
[34] አያሌው (ዶ/ር)(አልቦ ዓ.ም. ፣ 176)

ሆኖም በአንድ በኩል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አቡሳሊህ፥ ከላይ የተጠቀሰው፣ ከታቦቱ ውጭ ያለውና፥ "ንጉሡ ከሙሴና ከአበሻ ንጉሥ ልጅ ጋብቻ የወረደ ዘር ነው" የሚለው የራሱ የፈጠራ አባባል እንደ ሆነ ሲገልጹ፥ በሌላ በኩል ደግሞ "ምናልባት ለአቡሳሊህ አንድ አፈ-ታሪክ ዐዋቂ ኢትዮጵያዊ ሹክ ብሎት ሊሆን ይችላል"[35] የሚል ግምታቸውን አስቀምጠዋል፡፡

ሹክ ባዩ አፈ ታሪክ ዐዋቂ የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት አቀንቃኝ መሆኑን መገመት አይከብድም፡፡ ሆኖም ለሰሎሞናውያኑ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማስገኘት ሲባል፥ ጽላተ ሙሴ በዛጉዌያውያን እጅ እንዳለ አድርጎ ያቀርባል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ምናልባት በሰሎሞናውያንና በዛጉዌያውያን መካከል የአፈ ታሪክ ሽሚያ ኖሮ ከዚያ አንጻር የቀረበ ትረካ ሊሆን ይችላል፡፡

በይትባረከ መጽሐፈ ገድል የተጻፈውን ጠቅሰው እንዳሰፈሩትም፥ የንጉሥ ላሊበላ ልጅ ይትባረክ በአጎቱ ልጅ በነአኩቶ ለአብ ላይ አንድ ሰው አቀረበ በተባለው ክስ ውስጥ፥ "ቀደም ሲል መንግሥትህን ወሰደብህ አሁን ግን ታቦትህን ጽዮንን ይዞ ከዋሻ ውስጥ ተደብቆልሃል"[36] በማለት ታቦተ ጽዮንን የጠቀሰ ይመስላል፡፡ ይህም ታቦቷ በዛጉዌያውያን ዘንድ እንደ ነበረች ይታመን ነበር ወደሚል አመለካከት ይወስዳል፡፡

በሁለቱም ወገኖች ዘንድ የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ እንዳለ ተተርኳል፡፡ በክፍል አንድ እንደ ተመለከትነው ግን፥ ከ971-931 ከክርስቶስ በፊት በነገሠው በሰሎሞን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጣ የተባለው ታቦት፥ ከሰሎሞን በኋላ ከ639-609 ከክርስቶስ በፊት[37] በነገሠው በኢዮስያስ ዘመን (ከ332 ዓመታት በኋላ) ታቦቱን በቤተ መቅደሱ ውስጥ አኑሩት ተብሎአልና፥ ከዚህ አንጻር ወደ ኢትዮጵያ መጣ የሚለው ትረካ ከአፈ ታሪክነት የሚያልፍ አይመስልም፡፡

## 2.1.4. የቃል ኪዳኑን ታቦት አድራሻ የፈለጉ ምን አሉ?

የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል የሚለውን ትረካ መነሻ በማድረግ ብዙዎች የትረካውን ትክክለኛነት ለማረጋጋጥ ጥረት

[35] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 176)፡፡
[36] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 225)፡፡
[37] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣117፣170)፡፡





ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የሚናገረውን ይዘው የከብረ ነገሥትን ትረካ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገቡታል፡፡ ሌሎች ደግሞ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ እስካሁን ድረስ የቃል ኪዳኑ ታቦት በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅደስ ውስጥ የሌለ በመሆኑ፥ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለውን እምነት ለማረጋገጥ ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በፍለጋቸው የደረሱበትን ውጤት ለንባብ ያበቁ ለምሳሌ፡- ግርሃም ሐንኮክ እና ሮበርት ኮርኑክ የተባሉ የውጪ ዜጎች ይገኙበታል፡፡[38]

"ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ" ተብሎ በተተረጐመው መጽሐፍ ላይ እንደ ተገለጸው፥ ግርሃም ሀንኮክ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለውን ትረካ የተቀበሉ ይመስላል፡፡ ነገር ግን በ3ኛው የእስራኤል ንጉሥ በሰሎሞን ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ መጣ በሚለው የከብረ ነገሥት ትረካ አይስማሙም፡፡ ከሰሎሞን በኋላ እስከ ሕዝቅያስ ባሉት ዘመናት ታቦቱ በኢየሩሳሌም መቅደስ ውስጥ እንደ ነበረ አረጋግጠዋል፡፡ ከሕዝቅያስ በኋላ በነገሡት በምናሴና በአሞጽ የንግሥና ዓመታት • ውስጥ፣ በተለይም ምናሴ ጣዖት አምላኪ መሆኑን የተቃወሙትን በርካታ አይሁድ ሲጨፈጭፍ፥ የተረፉት አይሁድና ካህናቱ ታቦቱን ይዘው ወደ ግብጽ ተሰደዋል ይላሉ፡፡ ከ200 ዓመታት በኋላም ወደ ኢትዮጵያ ይዘዉት መጥተዋል የሚል ሌላ መላ ምት አስቀምጠዋል፡፡[39]

ሆኖም ይህ መላ ምት እውነት መሆኑ የተረጋገጠ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በምናሴ ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት ከምድረ ኢየሩሳሌም ተወስዶ ቢሆን ኖሮ፥ ከምናሴ ልጅ ከአሞጽ ቀጥሎ የነገሠው ኢዮስያስ ተሐድሶን ካደረገ በኋላ፥ ሌዋውያኑን "ቅዱሱን ታቦት የእስራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በሠራው ቤት ውስጥ አኑሩት" (2ዜና. 35፥3) ሲል ባላዘዘም ነበር፡፡ ትእዛዙ በቅርቡ (በምድረ እስራኤል) ላሉት ሌዋውያን የተሰጠ እንጂ ርቀው ለሄዱት (በምድረ ግብጽ ላሉት) ሌዋውያን የቀረበ አይመስልም፡፡

[38] የግርሃም ሐንኮክ መጽሐፍ "The Sign And The Seal" ሲሆን፣ በጌታቸው ተሰፋዬ "ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ" ተብሎ ወደ ዐማርኛ ተመልሷል፡፡ የሮበርት ኮርኑክ መጽሐፍ ደግሞ "Relic Quest" ይሰኛል፡፡ በማህሉ ጥላሁን "ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን?" ተብሎ ወደ ዐማርኛ ተመልሷል፡፡
[39] ሐንኮክ (1995፣ 184-187 ፡245)፡፡

ግርሃም ሐንኮክ ታቦቱ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል የሚለውን ትረካ መሠረት አድርገው፥ ታቦቱ ተቀምጦባቸው ነበር የተባሉትን ቦታዎች ሁሉ ለመጐብኘት ጥረት አድርገዋል:: በየስፍራው በኀላፊነት ላይ ያሉ የቤተ ክህነት ሰዎችን ለማነጋገርም ሞክረዋል:: ከሁሉም የሰሙት የታቦቱን ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ቢሆንም፥ ለማረጋገጥ ያደረጉት ሙከራ ግን ብዙ የተሳካ አልነበረም ማለት ይቻላል:: በተለይም ታቦቱ አሁን ይገኝበታል በሚባለው በአክሱም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው የታቦቱ ጠባቂ የሆኑትን አባ ገብረ ሚካኤልን አነጋግረዋቸዋል:: ወደ ቤተ መቅደሱ ለመግባትና ታቦቱን ለማየት ፈቃድ ጠይቀዋቸውም ነበር:: ያገኙት ምላሽ ግን፥ "ልታየው አትችልም:: እንደምትለው ስለ ታሪካችን ካጠናህም ይህን ጠንቅቀህ ማወቅ ነበረብህ:: … ብዙዎች ተስፋ ያደርጋሉ:: ነገር ግን ከእኔ በስተቀር ማንም ወደ ቃል ኪዳኑ ታቦት መቅረብ አይችልም:: ንቡረ እዱም ቢሆኑ፤ ፓትርያርኩም:: ፈጽሞ የተከለከለ ነው::"[40]

እንዲህ የሆነበት ምክንያት ግልጽ አይደለም:: ፓትርያርኩም ሆኑ ንቡረ እዱ በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት መሠረት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው፥ ይልቁንም ፓትርያርኩ ሥልጣነ ክህነትን የሚሰጡ እንደ መሆናቸው ታቦቱ ተቀምጦበታል ወደሚባለው ክፍል ሊገቡ ያለ መቻላቸው ጕዳይ አጠያያቂ ነው::

ሮበርት ኮርኑክም በግርሃም ሐንኮክ ምርምር ላይ ተመሥርተው ያቀረቡት ጥናት፥ በምናሴ ዘመን ከኢየሩሳሌም በግብጽ ውስጥ ወደሚገኘው ኤሌፋንታይን ደሴት የተሰደዱት አይሁድ ታቦቱን ወደዚያው እንደ ወሰዱትና በኋላም ወደ ኢትዮጵያ እንዳመጡት የሚናገር ነው::[41] እንደ ግርሃም ሐንኮክ ሁሉ እርሳቸውም የታቦቱን በአክሱም መኖር ከሚመለከታቸው ኀላፊዎች ከመስማት በቀር የተለየ ማረጋገጫ ያገኙበት ሁኔታ የለም::

## 2.2. ታቦታት በኢትዮጵያ

የቃል ኪዳኑ ታቦትና የኢትዮጵያ ታቦታት ምንም ዐይነት ግንኙነት የሌላቸው መሆኑ ቢታወቅም፥ የኢትዮጵያን ታቦታት በብሉይ ኪዳን

[40] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 243)::
[41] ኮርኑክ (1999፣ 239-243)::





ዘመን ከነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር አያይዞ መናገር የተለመደ ሆኗል::

> የታቦት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ተጀምሮ የቀረ አይደለም:: ጽላተ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መጣች ሀገራችን ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ አምልኮተ እግዚአብሔርን አጽንታ ቈይታለች:: … የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ኦሪትን ከሥርዐተ ወንጌል አጣምራ የያዘች ስለ ሆነ በክርስትና ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን በክርስትና መንፈስ እየተረጐመች ትገለገልባቸዋለች::[42]

የሚለው አመለካከትም ይህንኑ ያስረዳል:: ይህም አስተሳሰብ የቃል ኪዳኑ ታቦትና የኢትዮጵያ ታቦታት አንድ ዐይነት ተደርገው እንዲቈጠሩ በር ከፍቷል:: በሌላም በኩል በአገራችን "ታቦት" ቀርጾ አምልኮ መፈጸም መቼ እንደ ተጀመረ በርግጠኛነት መናገር እንዳይቻል እክል ፈጥሯል::

ብሉይ ኪዳን የተሰጠው በሥጋ ከአብርሃም ዘር ለተወለዱት እስራኤላውያን ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው በሰጠው ተስፋ መሠረት በሲና ተራራ ላይ፥ ቃል ኪዳኑን በሙሴ በኩል አስታወቃቸው:: እነርሱም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቃል ኪዳን ለመቀበልና ለመጠበቅ ተስማሙ (ዘፀ. 19፥3-8):: ቃል ኪዳኑም በደም ተመረቀ (ዘፀ. 24፥3-8፤ ዕብ. 9፥18):: በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከእነርሱ በቀር ቃል ኪዳን የተጋባው ሌላ ሕዝብ የለም፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ "ቃሉን ለያዕቆብ ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል፤ ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፥ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም" (መዝ. 147፥8-9):: "አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው" (ሮሜ 3፥2) ተብሎ የተነገረላቸውም እነርሱ ብቻ ናቸው:: ኦሪታቸውም እንዲህ ይላል፤ "በዐይናችሁ ፊት ዛሬ እንደማኖራት እንደዚህች ሕግ ሁሉ ጽድቅ የሆነች ሥርዐትና ፍርድ ያለው ታላቅ ሕዝብ ማነው?" (ዘዳ. 4፥7-8)::

ከእነርሱ ጋር በተለያየ መንገድ ግንኙነት በመፍጠር የማንነታቸው መገለጫ የሆኑትን ነገሮች ሌሎች ሕዝቦች መውረስ ይችላሉ:: በኢኦተቤክ

[42] የኢኦተቤክ እምነት፥ ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት (1988፣ 62)፤ ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) (1974፣ 94)::

ዛሬ የሚታዩት ልዩ ልዩ ኦሪታውያን ሥርዐቶችና ልማዶችም በተለያዩ መንገዶች ከአይሁድ የተወረሱ ናቸው።[43] ይህ ግን የባህል መወራረስ ተብሎ ይወሰዳል እንጂ ብሉይ ኪዳንን መቀበል ተብሎ ሊገለጽ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም።

እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ብዙ ጊዜ የገለጸው በባልና ሚስት መካከል እንደሚደረግ ቃል ኪዳን ነው (ሆሴ. 2፥21-22፤ ኤር. 3፥14)። የባልና ሚስት ቃል ኪዳን ከባልና ሚስቱ ዐልፎ ሌሎች የሚታቀፉበት ቃል ኪዳን እንደማይሆን ርግጥ ነው።

ለመሆኑ ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን መቼ ተቀበለች? ማንስ ሰጣት? እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በገባው ብሉይ ኪዳንስ እንዴት ልትታቀፍ ትችላለች? ከላይ እንደ ተመለከትነው ይህ፥ ባልና ሚስት በመካከላቸው ስለሚኖረው የፍቅር ግንኙነት በገቡት ቃል ኪዳን ሌላው ወገን ለመታቀፍ እንደ"መሞከር አይቈጠርም ወይ?

ሌላው ነጥብ፥ ኦሪት ከነሙሉ ጓዙ የተሰጠው ለእስራኤል ብቻ በመሆኑ፥ ከዐሠርቱ ትእዛዛትና እነርሱን ከመሳሰሉት ሕገጋት በቀር ቤተ ክርስቲያን ከኦሪት በቀጥታ አምጥታ፥ ወይም በክርስትና መንፈስ ተርጕማ የምትገለገልባቸው የኦሪት ሥርዐታትና ንዋያተ ቅድሳት አይኖሩም።

- "ይሻር የነበረ" (2ቆሮ. 3፥11)
- "ደካማና የሚናቅ" (ገላ. 4፥9)
- "ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ" (ቈላ. 2፥17)፤
- "የምትደክም፥ የማትጠቅምም" (ዕብ. 7፥18-19)፤
- "ምሳሌና ጥላ" (ዕብ. 8፥5)፤
- "ነቀፋ ያለበት" (ዕብ. 8፥6)፤
- «አሮጌና ውራጅ» (ዕብ. 8÷13)

ወዘተ. እየተባለ ከተገለጸው ብሉይ ኪዳን፥ በክርስትና መንፈስ የሚተረጐም ምን የተሻለ ነገር ይገኛል? ብሉይ ኪዳን በዐዲስ ኪዳን ተፈጻሚ ከሚሆን በቀር ተሻጋሪ የኦሪት ሥርዐትም ሆነ የተቀደሰ ዕቃ በዐዲስ ኪዳን ውስጥ አይኖርም። ቤተ ክርስቲያንም ወንጌልን ብቻ እንጂ ኦሪትንና ወንጌልን በአንድ ላይ እንድታስኬድ የታዘዘችበት ሁኔታ ፈጽሞ

[43] ስለዚህ ጕዳይ ይበልጥ ለመገንዘብ «የተቀበረ መክሊት» የተሰኘውን መጽሐፍ ከገጽ 137-144 ያለውን ይመልከቱ።





የለም። አለ ከተባለ ግን ብሉይ ኪዳንን ያስረጀውን ዐዲስ ኪዳንን (ዕብ. 8፥13) አሻግሮ አለማየት፥ ወይም ዝቅ አድርጎ መመልከት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።[44]

አሁን በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙት ታቦታት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገራችን የገቡት ከግብጽ እንደ ሆነ፥ የደስታ ተክለ ወልድ ያማርኛ መዝገበ ቃላት ይናገራል። "ከግብጽ መጥተው የነበሩ የመዠመሪያዎቹ ታቦቶችም ታቦተ ማርያምና ታቦተ ሚካኤል ናቸው።"[45] በ4ኛው ምእት ዓመት ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፋው ፍሬምናጦስ ወይም ሰላማ ከሣቴ ብርሃን፥ በጊዜው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ከነበረው ከአትናቴዎስ ጵጵስናን ተሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ፥ የተለያዩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጡ ንዋያተ ቅድሳትን እንደ ሰጠውና ከእነዚህም መካከል አንዱ ታቦት እንደ ሆነ በስሙ የተደረሰው የገድል መጽሐፉ ይተርካል።[46] ይህ ሁሉ ግን ያው እንደ ተለመደው ኢትዮጵያዊው ታቦት ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ፥ ጕዳዩን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ለማያያዝ የተፈጠረ ልቦለድ ታሪክ መሆኑ አያጠራጥርም። ምክንያቱም "ይህ እንግዳ ነገርና በየትኛውም ባህል የማይታይ ሲሆን፤ ከአክሱም መንግሥት ወደ ክርስትና መለወጥ፣ ማለትም ከ331 እስከ 1959 ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለኢትዮጵያ ስትልክ የኖረችው የአሌክሳንድርያዋ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያንም እንኳ አትቀበለውም።"[47]

የመጀመሪያዎቹ ታቦታት ከግብጽ መጡ፥ ወይም አቡነ ሰላማ ታቦትን ወደ አገራችን አመጣ የሚለውን ሐሳብ ለመቀበል የሚያስቸግረው ግን፥ ግብጾች እንደ ኢትዮጵያው ያለ ታቦት የሌላቸው የመሆኑ ጕዳይ ነው። ታቦት በመጀመሪያ ከግብጽ መጥቶ ቢሆን ኖሮ ግብጾች ዛሬ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ያለውን ታቦት ይዘው በተገኙ ነበር። እነርሱ ቅዱስ ቍርባንን የሚፈትቱበት "ሉሕ" የተባለ ሰሌዳ አላቸው። እርሱም እንደ መሠዊያ እንጂ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ታቦት የሚታይ አይደለም። በተለያዩ ቅዱሳንና ሰማዕታት ስም ተሠይሞ፥ የበዓል ቀን ተለይቶለት ቀሳውስት ተሸክመውት የሚያነግሡትም አይደለም። እንደዚህ አድርገው

[44] በኦሪትና በወንጌል መካከል ያለውን ልዩነትና ንጽጽር ለማገናዘብ «ጥላና አካል» የተሰኘውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

[45] 1962፣ 1250)።

[46] ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998፣ 10-11)።

[47] ሐንኮክ (ገጽ 1995፣ 125)።

ቢገኙ እንኳ እነርሱም ስሕተተኞች መባላቸው አይቀርም ነበር። ስለዚህ እየሰጡ ካለው አገልግሎት አንጻር "ታቦት" እና "ሉሕ" በከፊል ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ጉልሕ ልዩነቶችም ይታዩባቸዋል። ሌሎቹም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት "አንዲሚንስዮን"፥ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "ሜንሳ" በማለት የሚጠሯቸው ንዋያተ ቅድሳት ለሥጋ ወደሙ መፈተቻነት የሚያገለግሉ ናቸው።[48]

አሁን ያለውን ታቦት መቅረጽና አገልግሎት ላይ ማዋል መቼ እንደ ተጀመረ በውል መናገር ባይቻልም፥ ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ወዲህ ይበልጥ የተስፋፋ ይመስላል። አባ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከተከሰሰባቸው ጉዳዮች አንዱ፥ ቢታቦት ላይ ልታቀርብ ሲገባህ "ቍርባንን በጠረጴዛ ላይ ታቀርባለህ" ተብሎ ነበር። እርሱም፥ "በመጽሐፍ ውስጥ በጠረጴዛ ላይ እንዳያዘጋጁ የሚከለክል ቃል ስላላገኘሁ ከዕንጨት በተሠራ ጠረጴዛ ላይ ቍርባንን እንዲያዘጋጁ ወንድሞቼን አማክሬያቸዋለሁ" በማለት ክሱን ተከላክሏል። ታቦት የሚቀረፀውም ከዕንጨት መሆኑን ጠቅሶ፥ ሌላው ግን ከወርቅ ወይም ከብር በተሠራ ታቦት ላይ ሊያዘጋጅ ቢወድ ተቃውሞ እንደሌለው ገልጧል። "ንጉሡም ይህስ መልካም ነው" ማለቱ ተዘግቧል።[49] ምናልባትም ይህን ያለው አሁን ያሉት ታቦታትና አገልግሎታቸው ገና እየተዋወቀ ያለበት ጊዜ ስለ ነበረ ሊሆን ይችላል።

ባንድ ቤተ ክርስቲያን አንድ ታቦት ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ ድርብ ታቦታት በደባልነት እንዲቀመጡ ትእዛዝ የወጣው በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ነው።[50] ይህም ሁኔታ ያ ዘመን በየቤተ ክርስቲያኑ የታቦታት ቍጥር እንዲጨምርና የታቦት አምልኮ እንዲስፋፋ ያደረገ ዘመን መሆኑን ይጠቍማል።

ታቦት የተባለው ሁለት ገጽ ያለው ዝርግ ሰሌዳ እንደ መሆኑ፥ በፊትና በጀርባው የተለያዩ ነገሮች ይቀረጹበታል፤ ይጻፉበታል። በአንደኛው ገጽ የተለያዩ ሐረጋትና ሥዕላት፣ እንዲሁም ምስጢራውያን የተባሉ የእግዚአብሔር ስሞች ይቀረጹበታል። "በሁለተኛ ገጽ መሠረታዊ ታሪክ ያለበት ጽሑፍ ይገኝበታል። ይኸውም ንጉሡ፣ ጳጳሱ፣ ጊዜው፣ ወይም

[48] ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) (1974፣ 95)።

[49] ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ (1996፣ 134-135)።

[50] ተክለ ጻድቅ (1966፣ 239)።





ምስለኔው፣ የጭቃ ሹሙና ገበዙ ይጠቀሱበታል። በዚሁም ታቦቱ የተተከለበትን፣ ቤተ ክርስቲያኑ የተቋቋመበትንና የተመረቀበትን ጊዜና ቦታ ባጭሩ የሚገልጽ ታሪክ ሆነ ማለት ነው።"[51] በተለይ በሰሌዳው ሁለተኛ ገጽ ላይ የሚጻፈው ይህ መረጃ፥ ሰሌዳው አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲተከል ከሊቀ ጳጳሱ የሚሰጥ የፈቃድ ማስረጃ እንደ ነበር ይጠቍማል።[52] በሂደት ግን እንደ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይቈጠር የነበረው ሰሌዳ፥ "ታቦት" ተብሎ አሁን ወደሚገኝበት ደረጃ ተሸጋግሯል ማለት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ስለ ታቦት የሚነገረውና የሚታመነው ሁሉ በየትኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንደ ተወሰነ ግልጽ አይደለም። ስለ ታቦት በእምነት መግለጫችንም ሆነ በዐምስቱ አዕማደ ምስጢር አስተምህሮአችን ውስጥ አልተወሳም። በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በተተረጐመው ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ግን ስለ አሠራሩ እንዲህ ተብሏል፤ "ወይኩን ታቦት በዘይፈልስ እመካን ውስተ መካን ከመ ዕብነ ደቂቀ እስራኤል ዘፈለሰ እመካን ውስተ መካን። - ታቦቱ ከቦታ ወደ ቦታ ይዛወር እንደ ነበረው እንደ እስራኤል ልጆች ታቦት ከቦታ ወደ ቦታ የሚዛወር ይሁን"[53] መቼም ከኢትዮጵያ በቀር ታቦት ያላት ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ የለችም። ፍትሐ ነገሥትን ባስተረጐመችን በግብጽ ቤተ ክርስቲያንም ሉሕ እንጂ ታቦት የለም። ታዲያ ስለ ታቦት በፍትሐ ነገሥት እንዴት ሊጻፍ ቻለ? የሚለው አነጋጋሪ ነው።

"በርግጥ የፍትሐ ነገሥት የግእዙ ትርጕም ከዐረብኛው ጋር ሲተያይና ሲነጻጸር ስሕተቶችና የአለመጣጣም ሁኔታዎች ያጋጥማሉ"[54] ስለ ተባለ፥ ምናልባት ከታቦቱ ጋር በተያያዘ ከላይ የተጠቀሰው ትእዛዝም የዚሁ ውጤት ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ይህ የታቦት አሠራር ደንብ፥ የኢትዮጵያን የታቦት ሥርዐት ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን የመጣ ለማስመሰል በሥርዋጽ የገባ ይሆናል።

የኢትዮጵያን ታቦታት የተመለከተ ትችትና ተቃውሞ በተነሣ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያናችን በኩል ምላሽ የሚሆኑ ማስተባበያዎች ይሰጣሉ። እነዚህም

[51] መሠረት (ዓ.ም. ያልተገለጸ፣ 12-13)።

[52] ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ቍጥር 15፣ ገጽ 16)።

[53] ፍትሐ ነገሥት (1990፣ 21)።

[54] ዲበኩሉ (ዶ/ር) (1986፣ 80)።

በአብዛኛው ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተነገሩትን መጽሐፍ ቅዱሳውያን ጥቅሶች ለኢትዮጵያ ታቦታት በመጥቀስ የሚቀርቡ ናቸው። በማስተባበያው ውስጥም ትችቱንና ተቃውሞውን የሚሰነዝሩት ወገኖች፥ በብሉይ ኪዳን የነበረውን የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደ ነቀፉ ተደርጎ ነው የሚቀርበው። እነርሱ ታቦት በብሉይ ኪዳን እንደ ነበረና ዛሬ እንደሌለ፥ አገልግሎቱም እንዳበቃ በመናገራቸው ተሳስተዋል ለማለት የሚቀርብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ግን አይኖርም።

በቤተ ክርስቲያናችን ስለ ታቦት ያለው ትምህርትና እምነት ግን ይህ ብቻ ነው ማለት አይደለም። በብሉይ ኪዳን የነበረው የቃል ኪዳን ታቦት ጥላና ምሳሌ እንደ መሆኑ፥ በዐዲስ ኪዳን እርሱን የተካው እካሉና አማናዊው ታቦት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነ ይታመናል። ከእርሱ በቀር የታቦትን ጥላነት የሚተካ አማናዊ ታቦት የለም። የምእመናን ልብ ግን ቃሉ የሚጻፍበት ጽላት ተብሎ ተገልጿል (ኤር. 31፥33፤ 2ቆሮ 3፥3)።

## 2.3. ታቦትና መሥዊያ ምንና ምን ናቸው?

በብሉይ ኪዳን ታቦትና መሥዊያ ሁለት የተለያዩ አገልግሎቶችን የሰጡ ሁለት የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ነበሩ። ታቦት የሰጠውን አገልግሎት በተመለከትንበት ክፍል፥[55] የተጠቀሱትን አገልግሎቶች ከመስጠት በቀር ታቦት መሥዊያ ተብሎ አልተጠራም፤ መሥዊያም ሆኖ አላገለገለም። ታቦትና መሥዊያ ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው፥ ስለ ሁለቱም አሠራር እግዚአብሔር ንድፉን በተናጠል ለሙሴ ከሰጠበት ክፍል ማረጋገጥ ይቻላል። ስለ ታቦቱ በኦሪት ዘፀአት 25፥10-22 ላይ ሲናገር፥ ስለ መሥዊያው ደግሞ ኦሪት ዘፀአት 27፥1-8 ላይ ይናገራል። በንድፉ መሠረትም ታቦቱ (ዘፀ. 37፥1-9) እና መሥዊያው (ዘፀ. 38፥1-70) ለየብቻ ተሠርተዋል። በማደሪያው ድንኳን ውስጥም በተለያዩ ቦታዎች እንዲቀመጡ ተደርገዋል (ዘፀ. 40፥20-21፡ 28-29)።

የኢትዮጵያ ታቦታት ግን ከቃል ኪዳኑ ታቦት ተለይተው መሥዊያ ተብለው ይጠራሉ።[56] መሥዊያ የሚለው ስያሜም ለታቦቱ ተለዋጭ ስም ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል። ታቦቱን መሥዊያ ያሰኘውም የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ስለሚፈተትበት ነው። ይሁን እንጂ ቀድሞ

[55] በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 12 ላይ የታቦት አገልግሎት የሚለውን ክፍል ይመለከቷል።
[56] ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) (1974፣ 94)።





መሥዊያ የሚባለው ታቦቱ ሳይሆን መንበሩ ነበር። መንበሩ አሁን የያዘውን ቅርጽ ከመያዙ በፊት አንበር የሌለው ጠረጴዛ እንደ ነበረና ጠረጴዛ ወይም ምሥዋዕ (መሥዊያ) እየተባለ እንደሚጠራ ቀደምት ድርሳናትን ጠቅሰው ሊቃውንት ይናገራሉ።[57]

መንበሩም ሆነ ታቦቱ መሥዊያ መባላቸው፥ እንደ መሥዊያ መወሰዳቸው፥ ቄሱን በቅዳሴ ጊዜ መሥዋዕት አቅራቢ፤ የክርስቶስን ሥጋና ደም ደግሞ መሥዋዕት ማሰኘታቸው አልቀረም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከሆነ ግን ኅብስቱንና ወይኑን መሥዋዕት ብለን የምንጠራበትም ሆነ መሥዋዕት አድርገን የምናቀርብበት አግባብ የለም።

በመሠረቱ መሥዋዕት የሚባለው ሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ለአምላኩ የሚሰጠው ወይም የሚያቀርበው ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መሥዋዕት ለሚለው ቃል የተሰጠው ትርጉም፥ "ሰው ለአምላኩ አንዳች ነገር ቢሰጥ ወይም ቢያቃጥል ያ ነገር መሥዋዕት ወይም ቍርባን ይባላል"[58] የሚል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘባት በዚያች ሌሊት "ሥጋዬ ነው" ያለውን ኅብስት "እንካችሁ፥ ብሉ"፥ "የዐዲስ ኪዳን ደሜ ነው" ያለውን ወይን ደግሞ "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ" ብሎ የሰጠው ለደቀ መዛሙርቱ ነው። ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አላቀረበውም (ማቴ. 26፥26-27)።

"ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" (ሉቃ. 22፥20) ባለው መሠረት፥ በኅብስትና በወይን የተሰጠውን የክርስቶስን ሥጋና ደም በመብላትና በመጠጣት፥ ጌታችን ዳግም እስኪመጣ ድረስ ሞቱንና ትንሣኤውን በመናገር መታሰቢያውን እንድናደርግ ታዝናል (1ቆሮ. 11፥23-26)። ስለዚህ ኅብስቱና ወይኑ መሥዋዕት ባለ መሆናቸው እነርሱ ለሚቀመጡበት ዝርግ ሰሌዳ መሥዊያ የሚለው ስያሜ ተስማሚ አይሆንም። ሆኖም ለሥጋ ወደሙ ክብር ለመስጠት እስከ ሆነ ድረስ፥ የተለየ መክበሪያ ዝርግ ሰሌዳም ሆነ ሌላ ነገር መዘጋጀቱና መለየቱ መልካም እንጂ መጥፎ አይደለም።

የዐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አንድ ጊዜ ያቀረበው ራሱን ብቻ ነው

[57] መሠረት ፣ ያልታተመ ገጽ 10-11።
[58] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣ 30)።

(ኤፌ. 5፥2፤ ዕብ. 7፥27፤ 9፥14፡26፤ 10፥10፡12)። ይህ መሥዋዕት አንድ ጊዜ የቀረበና የማይደጋገም ነው። ስለዚህ ለክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መታሰቢያ የሆኑትን ኅብስትና ወይን ከመካፈል (ሉቃ. 22፥17) በቀር እርሱ ባቀረበው አምሳል የምንሠዋው መሥዋዕት የለም። ይህን መሥዋዕት ዳግም እንዲያቀርብ የተሾመ ሊቀ ካህናትም የለም። ነገር ግን በክርስቶስ አምነው በደሙ የተቀደሱ ሁሉ የንጉሥ ካህናት በመሆናቸው (ራእ. 1፥6) ሌሎች መንፈሳውያን የሆኑ መሥዋዕቶችን እንዲሠዉ ታዘዋል (ሮሜ 12፥1-2፤ 15፥15-16፤ ፊል. 4፥18፤ ዕብ. 13፥15፡16)። እነዚህና የመሳሰሉት መሥዋዕቶች መንፈሳውያን እንደ መሆናቸው፥ መሠዊያቸውም መንፈሳዊ እንጂ ግዙፍ ወይም ቍሳዊ አይደለም።

ታቦትና መሠዊያ አንድ ናቸው ለማለት የሚያበቃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ አይገኝም። የዕብራውያኑ ጸሐፊ "መሠዊያ አለን" (ዕብ. 13፥10) ያለውን ቃል ለታቦት እንደ ጠቀሰው አድርገው የሚያስተምሩ ግን አሉ።[59] እያይዘውም ጌታችን ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቍጥር 23 እና ምዕራፍ 23 ቍጥር 19 ላይ መሠዊያን ጠቅሶ የተናገረው፥ የኦሪቱን መሠዊያ ብቻ ሳይሆን በዐዲስ ኪዳንም አለ ስለሚሉት ታቦት ጭምር እንደ ተነገረ አድርገው ያቀረቡበት ሁኔታ አለ።[60]

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው የብሉይ ኪዳንን ትምህርትና ታሪክ በሚገባ ለሚያውቁና ወንጌልን ከኦሪት ጋር ቀላቅለው ለማስኬድ ዝንባሌ ላሳዩ አይሁድ ክርስቲያኖች መሆኑ ይታወቃል። "መሠዊያ አለን" የተባለው ግን በዐዲስ ኪዳን መሠዊያ አለን ለማለት የተነገረ አይደለም፤ የቀደመውን ኦሪታዊውን መሠዊያ ጠቅሶ የተሻለውን የዐዲስ ኪዳን አገልግሎት ለማሳየት የተጠቀሰ ነው እንጂ። ይህንም ከዐውደ ምንባቡ መረዳት ይቻላል። "መሠዊያ አለን" የሚለው ጥቅስ የተመዘዘበትን አንቀጽ ከቍጥር 7 ጀምሮ ስንመለከት፥ ዕብራውያኑ የእግዚአብሔርን ቃል የነገሯቸውን ዋኖቻቸውን እንዲያስቡ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬና ለዘላለምም ያው መሆኑንና እንደማይለወጥ፣ ከዚህ በመነሣትም ልዩ ልዩ በሆኑ የስሕተት ትምህርቶች እንዳይወሰዱ ያስገነዝባቸዋል። በማስከተልም የኦሪትን መሠዊያና በዚያ የሚያገለግሉትን ካህናት የመሥዋዕት አቀራረብ በመግለጽ፥ "ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጪ መከራን ተቀበለ" (ቍጥር 12) በማለት

---

[59] ሄኖክ (ዲ/ን) (2001፣ 35)።

[60] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 45-46)።





ምሳሌውን ከእማናዊው፥ ጥላውን ከአካሉ ለይቶ የተሻለውንና የበለጠውን ያመለክታቸዋል።

ወንጌል የተሰበከና ኦሪት ከነጓዙ ስፍራውን የለቀቀለት ቢሆንም፥ ወደ ወንጌል ዘወር ያላሉና በኦሪት ሥርዐት ውስጥ ያሉ ነበሩና፥ ጊዜ ያለፈበትን መሥዋዕተ ኦሪት በመሠዊያው ላይ ማቅረባቸውን አልተዉም ነበር። በወንጌል ያመኑትና ወደ ኦሪት እያፈገፈጉ የነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች ሊያቀርቡት ስለሚገባው መሥዋዕት ምንነት ሲያስረዳቸው እንዲህ ይላቸዋል፤ "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት። ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።" (ቍጥር 15-16)።

መቼም ይህ መሥዋዕት በኦሪቱ መሠዊያ ላይ ሊቀርብ የማይችል መንፈሳዊ መሥዋዕት እንደ መሆኑ መሠዊያውም መንፈሳዊ ነው። ስለዚህ "መሠዊያ አለን" የሚለው በኦሪት ዘመን አገልግሎት ይሰጥ ስለ ነበረው የኦሪቱ መሠዊያ እንጂ ስለ ሌላ የተነገረ አይደለም። ቃሉ በዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ስለ ተጠቀሰ ብቻ ዐውደ ምንባቡን ሳያጤኑ ለዐዲስ ኪዳን እንደሚያገለግል አድርጎ ማቅረቡ ትልቅ ስሕተት ነው።

ጌታችን በቅዱስ ወንጌል ስለ መሠዊያው የተናገራቸውን ቃላት ስለ ታቦት እንደ ተናገራቸው ተደርጎ የተጠቀሰውም በተመሳሳይ የስሕተት መንገድ የተጠቀሰ ነው። እርሱ፥ "እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ" (ማቴ. 5፥23)። እንዲሁም፥ "ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መባ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ትላላችሁ። እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው?" (ማቴ. 23፥18-19) በማለት የተናገረው ስለ ኦሪቱ መሠዊያ እንደ ሆነ ግልጽ ነው።

እነዚህ ጥቅሶች ስለ ኦሪቱ መሠዊያ ብቻ ሳይሆን ስለ ሐዲስ ኪዳኑ መሠዊያ ስለ ታቦትም የተጻፉ ናቸው ብለው በርግጠኝነት የሚናገሩ ግን አሉ። ለዚህም፥ "ጌታ ዐዲስ በሚሠራት በሕገ ወንጌል ላይ እንዴት ስለምታልፈው የኦሪት መሥዋዕት ብቻ ይናገራል?" የሚል መሠረት የለሽ

መከራከሪያ ያቀርባሉ::[61] ይህ አስተሳሰብ ግን ጌታ ስለ መሠዊያው የጠቀሰበትን እውነተኛ ምክንያት ከዐውደ ምንባቡ ካለመገንዘብ የመጣ አስተሳሰብ ነው:: እስኪ የመጀመሪያውን ጥቅስ ለማሳያነት ቀጥሎ እንመልከተው::

ጥቅሱ የቀደመውንና "አትግደል" የሚለውን ሕግ ይበልጥ አጠንክሮ ያቀረበበትን ሁኔታ ያስረዳል:: ይኸውም መግደል ብቻ ሳይሆን በወንድም ላይ መቈጣትና ወንድምን መስደብ ፍርድን የሚያመጣ ኀጢአት መሆኑን ጌታ የገለጠበት ክፍል ነው:: አንድ ሰው ሌላውን ሰው ስላልገደለ ብቻ ራሱን እንደ ጻድቅ ቈጥሮና ወንድሙን አሳዝኖ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር መባ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም:: ስለዚህ አስቀድሞ ከወንድሙ ጋር መታረቅ ከዚያ መባውን ማቅረብ ይገባዋል::

ልብ መባል ያለበት ጕዳይ ቢኖር፥ ጌታ ይህን በተናገረበት ጊዜ ኦሪት ገና ያልተሻረች መሆኗን ነው:: ደግሞም መባ ሰው ለአምላኩ የሚያቀርበው ስጦታ በመሆኑ ዐይነቱ፣ አቀራረቡና መሠዊያው ቢለያይ እንጂ በወንጌል ዘመንም የሚኖር ነገር ነው:: ስለዚህ በልማዳዊ መንገድ መባን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፥ መባን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ቅድስናዊ ዝግጅት ማሟላትም እንደሚገባ ጌታ የሰጠው ትምህርት ያስገነዝባል::

ጌታ ይህን መልእክት እያቀረበ ያለው የኦሪቱ መሠዊያ ባለቤት ለሆነው አይሁዳዊ ትውልድ መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ስለዚህ በሙሴ በኩል የተሰጣቸውን የኦሪት ሥርዐትና ትምህርት እየጠቀሰ ማስተማሩ፥ ኦሪት በወንጌል ዘመንም አገልግሎቷን እንደምትቀጥል ማረጋገጫ ለመስጠት ሳይሆን፥ ሕዝቡ የሚኖርበትን ትምህርትና ሥርዐት መሠረት ያደረገ ትምህርት ለመስጠት ነው:: ነገሩን እንዲህ መመልከት ካልተቻለ ኦሪትንና ወንጌልን ለይቶ መመልከት ያዳግታል፤ በአተረጓጐም ላይም በስሕተት ውስጥ መውደቅ ይመጣል::

እንደ ተባለው መሠዊያው በዐዲስ ኪዳን በኢትዮጵያ ታቦታት የተተካ ቢሆን ኖሮ፥ ጌታ የቅዱስ ቍርባንን ሥርዐት በመጀመሪያ ባሳየ ጊዜ መሠዊያን ወይም ታቦትን በተጠቀመ ነበር:: ነገር ግን የፋሲካን ራት እንዲያዘጋጁ ለላካቸው ደቀ መዛሙርት ስለ መሠዊያ ወይም ስለ ታቦት የሰጣቸው ትእዛዝ አልነበረም:: እነርሱም ያለ መሠዊያ ወይም ያለ ታቦት

[61] ዝኒ ከማሁ (ገጽ 46)::





እንዴት ይሆናል ሲሉ አልተጠየቁም፤ ወይም አልተከራከሩም (ማቴ. 26፥17-29፤ ማር. 14፥12-25፤ ሉቃ. 22፥7-20):: ታዲያ መሠዊያው ታቦት ነው የሚለው ትምህርት ምንድን ነው? ቢሉ፥ የቀደሙ ሰዎች ታቦትን መሠዊያ ብለው ተጠቅመዉበታልና ስሕተትም ቢሆን ጥቅስ ፈልገን እናጽድቀው በሚል፥ ለውጥ ጠል ከሆኑ ወገኖች የተሠራጨ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው ከማለት በቀር ሌላ ምላሽ አይገኝለትም::

## 2.4. ቢቃል ኪዳኑና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል ያሉ ልዩነቶች

እስካሁን ለመመልከት እንደ ሞከርነው ቢቃል ኪዳኑ ታቦትና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል ከስም በቀር ልዩነት እንጂ ተመሳሳይነት አይታይም:: ምናልባትም የኢትዮጵያ ታቦታት ዝርግ ሰሌዳዎች በመሆናቸው፥ በቅርጽ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ሳይሆን ዐሥሩ ቃላት ከተጻፉባቸው ጽላት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው ቢባል ሊያስኬድ ይችላል:: ከዚህ ውጪ ግን የተለያዩ ናቸው:: ከሞላ ጐደል ልዩነቶቻቸው በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልከተዋል::

| የቃል ኪዳኑ ታቦትና ጽላት | የኢትዮጵያው ታቦት/ጽላት |
|---|---|
| ታቦቱ የጽላት ቤት ነው:: | ታቦትም ጽላትም የሚባለው ያው አንዱ ዝርግ ሰሌዳ ነው:: |
| ጽላቱ የተሠሩት ከድንጋይ ሲሆን፥ ታቦቱ ደግሞ ከግራር ዕንጨት ሆኖ በውስጥና በውጭ በወርቅ የተለበጠ ነው:: | ከዕብነ በረድ የተሠሩ ጽላቶች እንዳሉ ቢነገርም፥ በአብዛኛው ጽላት የሚሠራው ከዕንጨት ነው:: ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ በወርቅ የተለበጡ አይደሉም |
| የታቦቱ መጠን ተለክቶ የተሰጠ ሲሆን፤ ጽላቱን በተመለከተ ግን ስለ መጠኑ የተጻፈ ነገር የለም:: ሆኖም በፊቱና በጀርባው ዐሥሩን ቃላት ሊይዝ የሚችል ሆኖ | ጽላቱ፥ "ቁመቱ አንድ ክንድ ተሰንዝር፤ ጎኑ አንድ ክንድ፤ ውፍረቱ ሦስት ጣት"[62] ነው የሚል መለኪያ እንደ ተቀመጠ ይነገራል:: ይሁን እንጂ አንዱ |

[62] ደስታ (1962፣ 1250)::

| | |
|---|---|
| የተዘጋጀ እንደ ሆነ ግልጽ ነው:: | ታቦት/ጽላት ከሌላው ታቦት/ጽላት በቁመት፣ በወርድና በውፍረት ሊበልጥ ወይም ሊያንስ ይችላል:: |
| በጽላቱ ላይ የጻፈው እግዚአብሔር ነው:: | በጽላቱ ላይ የሣለው ወይም የጻፈው ሰው ነው:: |
| በጽላቱ ላይ የተጻፉት ዐሥርቱ ቃላት ብቻ ናቸው:: | ቢታቦቱ/በጽላቱ ላይ የእግዚአብሔር ኀቡእ/ምስጢራዊ/ ስም፣ ሥዕልና የሰዎች ስሞች /የጳጳስ፣ የንጉሥ፣... ነው የሚጻፈው እንጂ ዐሥርቱ ቃላት አይደሉም:: |
| በቍጥር 1 ታቦትና 2 ጽላት ብቻ ነበሩ:: | ስፍር ቍጥር የላቸውም:: |
| ታቦቱ አራት ካህናት በትከሻቸው የሚሸከሙት ሆኖ የተሠራ ነበር:: | አንድ ቄስ በራሱ ላይ እንዲሸከመው ሆኖ የተቀረጸ ነው:: |
| እግዚአብሔር የእስራኤልን መሪዎች የሚያነጋግርበት የክብር ዙፋን ነበር:: | ሥጋ ወደሙን መፈተቻ ወይም መሠዊያ ነው:: |
| የተጠራው በእግዚአብሔር ስም ነው:: እንዲሁም እርሱ በሰጠው ቃል ኪዳንና ምስክር ስም፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት፣ የኪዳኑ ታቦት፣ ወይም የምስክር ታቦት ተብሎ ተጠርቷል:: | በእግዚአብሔር ስም የተሰየሙ ታቦታት ያሉ ሲሆን፥ በቅዱሳን ሰዎችና መላእክት ስምም ይጠራሉ:: |
| በፍልስጥኤማውያን የተማረከበት ጊዜ ቢኖርም፥ ወደ አገሩ ሲመለስ እንደ ረከሰ ተቈጥሮ ዳግመኛ መቀደስ አላስፈለገውም:: | ታቦቱ ቢሰበር፣ ቢሰረቅ ወይም ቢማረክ እንደ ረከሰ ስለሚቈጠር ዳግመኛ መቀደስ እንዳለበት ተደንግጓል::[63] |

[63] ፍትሐ ነገሥት (1990፣ 21)::





# ምዕራፍ ሦስት

## የ"አልተሳሳትንም" ጉልሕ ስሕተቶች

ባለፉት ሁለት ምዕራፎች የቃል ኪዳኑን ታቦትና የኢትዮጵያን ታቦታት በንጽጽር ለማሳየት ተሞክሯል:: ሁለቱን ታቦታት አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስና የኢትዮጵያ ታቦታት ታሪክ የሚሉትን ለመዳሰስም ጥረት ተደርጓል:: ከዳሰሳውም የቃል ኪዳኑ ታቦትና የኢትዮጵያ ታቦታት ስያሜ ካልሆነ በቀር፥ የሚያመሳስላቸውም ሆነ አንድ የሚያደርጋቸው ጥቂት ነጥብ እንኳ አለመኖሩን መገንዘብ ተችሏል:: ከዚህ እውነታና ጭብጥ በመነሣት መምህር ምሕረተ አብ "አልተሳሳትንም" በሚል መፈክራዊ ርእስ የኢትዮጵያን ታቦታት ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በተነገሩት የእግዚአብሔር ቃላት ሸፍነውና "የእግዚአብሔር ታቦት" አስመስለው ሲያቀርቡ፥ የፈጸሟቸውን ጉልሕ ስሕተቶች ወደ መመርመር እንሸጋገራለን::

በቅድሚያ ግን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ለአንባቢው፥ መምህር ምሕረተ አብ በቪሲዲያቸው የጀርባ ሽፋን ላይ "ቢታቦት ላይ ለሚነሡ ጥያቄዎች የማያዳግም ምላሽ" የሚል የማይቀለበስ የሚመስል ፉከራዊ ድምዳሜ መስጠታቸውን ማስገንዘብ ይወዳል:: በተጨማሪም ከመምህር ምሕረተ አብ ምላሽ እየቀደሙ፥ 'ታቦታችንን የሚቃወሙ ሰዎች የሚያቀርቧቸው' ያሏቸውን ዐሥር ጥያቄዎች ቢድምፅ ብቻ የሚያሰሙት ሰው፥ ከጥያቄዎቹ በፊት በመግቢያ ንግግራቸው የሚከተለውን ማለታቸውን መግለጽ ይፈልጋል::

> እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች፥ ከሌሎች የምንለይበት ዐቢይ ምክንያት አንዱ የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘን በመገኘታችን ነው:: አንዳንዶች የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘን በመገኘታችን እንደ ስሕተተኛ ይቈጥሩናል:: እኛ ደግሞ ስሕተት የሌለበትን፥ ነገር ግን የሰዎችን ስሕተት የማሳየት ብቃት ያለውን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገን፥ ተሳስታችኋል ለሚሉን ወገኖች አለመሳሳታችንንና ትክክለኛ መሆናችንን ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን::

ብለዋል::

ርግጥ ነው! የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በዓለም ላይ ካሉ አብያተ ክርስቲያናትም ሆነ ታቦትን በብቸኝነት ከእግዚአብሔር ተቀብለው ከነበሩትና ዛሬ ግን ታቦት ከሌላቸው ከአይሁድም ልዩ የሚያደርጋት፥ በሌሎች ዘንድ የሌለውን እርሷ ብቻ ይዞ መገኘቷ ነው። ሆኖም በዚህ ነገር የተለየች መሆኗ፥ ከክርስትና ትምህርት አንጻር የሚያኰራና እንደ ጀብድ ሊወራ የሚገባው ሆኖ አይታይም፤ ታቦትን በመጀመሪያ የተቀበሉት አይሁድና ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ታቦት ሳይኖራቸው እንዴት እኛ ብቻ ታቦትን ይዘን ተገኘን? የሚል ጥያቄን የሚያጭር ነው እንጂ። ለዚህም ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምላሽ አይገኝለትም። ምናልባት መምህር ምሕረተ አብ እንዳደረጉት ለእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት የተጻፈውን ቃል፥ ለኢትዮጵያ ታቦታት በመጥቀስ፥ የነገሩትን ብቻ የሚቀበለውን የዋህ ምእመን ለጊዜው ማደናገር ይቻል ይሆናል። ከሁሉም በላይ ግን ኢትዮጵያውያን ራሳቸው የቀረጹትንና "ታቦት" ወይም "ጽላት" ብለው የሰየሙትን ንዋይ ቅዱስ፥ "የእግዚአብሔር ታቦት" ብሎ መጥራት ትልቅ ስሕተት ብቻ ሳይሆን ትልቅ ድፍረትም መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

እውን እርሳቸው እንዳሉት፥ "ስሕተት የሌለበትና የሰዎችን ስሕተት የማሳየት ብቃት ያለውን መጽሐፍ ቅዱስን " መሠረት አድርገው፥ ተሳስታችኋል ለሚሏቸው ወገኖች አለመሳሳታቸውንና ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችሉ ይሆን? በኢትዮጵያ ታቦታት ላይስ ለሚነሡ ጥያቄዎች የማያዳግም ምላሽ ሰጥተው ይሆን? ወይስ ሌሎች ጥያቄዎችን ፈጥረው የትምህርታቸው ገበና ይገለጥ ይሆን? ለሁሉም ጥያቄዎቹንና መልሶቻቸውን እንመርምር።

### 3.1 ስለ ታቦት አመጣጥ

"ታቦት ከየትና እንዴት መጣ?"

መምህር ምሕረተ አብ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፥ "በመጀመሪያ ደረጃ ሰው ማወቅ ያለበት ትልቁ ነጥብ ታቦት ከየት መጣ? የሚለውን ነጥብ ነው ይላሉ። እዚህ ላይ ስለ የትኛው ታቦት እንደሚናገሩ ግልጽ አይደለም። የሚናገሩት ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ከሆነ ግን፥ መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበና ሲሰበክም የሰማ ሁሉ የሚያውቀው እውነት ነውና ጥያቄው የማይመጥን ሆኖ ይታያል። በታቦት ላይ ጥያቄውን አነሡ የተባሉት ወገኖች ጥያቄም የቃል ኪዳኑ ታቦት ከየት መጣ? የሚል





እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ነገር ግን ጥያቄው የኢትዮጵያ ታቦታት ከየት መጡ? የሚል ሊሆን ይገባል፤ መሆንም አለበት።

የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት የሚናገሩ ጽሑፎችን የተቻለውን ያህል ለመመርመር ሞክሯል። ሆኖም ስለ ታቦት የጻፉ ብዙዎቹ የኢትዮጵያን ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር አመሳስለውና አገናኝተው ስለሚጽፉ፥ ጥቂት ጽሑፎች ከሚሰጧቸው ፍንጮች በመነሣት የተረዳውን ሐሳብ ከመሰንዘር በቀር ከየትና እንዴት እንደ መጡ ርግጡን ማወቅ አልቻለም። መምህር ምሕረተ አብም ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከር ይልቅ፥ የኢትዮጵያን ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ማገናኘትን ነው የመረጡት። (ምናልባት በክፍል 2 ሰብከታቸው ከየትመጣውን ይነግሩን ይሆን?)

በዚህ በመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ውስጥ ያነሡት ሌላው ነጥብ፥ ኦርቶዶክሳውያን ታቦትን ይዘን መገኘታችን ጣዖት አምላኪ አሰኝቶናል የሚል ይዘት ያለው ነው። ለዚህም፥ "እኛ ጣዖትን አምልከን አናውቅም፤ እግዚአብሔርም ጣዖትን ፈጽሞ ይቃወማል፤ እኛ የተከተልነውና በመንበራችን ያስቀመጥነው፣ አምልኮታችንን የምንፈጽምበት ታቦት የመጣው ከእግዚአብሔር ከራሱ … የሚገርም እኮ ነው! በጣቱ ጽፎ እግዚአብሔር ሰጠን" በማለት ዘፀ. 24፥12ን ማስረጃ ጠቅሰው የሚሰነዝረውን ትችት ያስተባብላሉ። ጥቅሱን እንብበው ሲያብራሩም፥ ታቦቱ የተሰጠው ለሙሴ እንደ ሆነ ገልጸው፥ "ስለዚህ እኛ ኦርቶዶክሳውያን እግዚአብሔር የሰጠንን ይዘን" ይሉና የአፍ ወለምታቸውን "እግዚአብሔር የሰጠውን ነገር ይዘን በመገኘታችን" በሚለው ቅቤ አሽተው ለማስተካከል ይሞክራሉ። ታቦት የተሰጠው ለእኛ ካልሆነና ለእስራኤላውያን ከሆነ፥ እግዚአብሔር ያልሰጠንን ይዘን መገኘታችን ጥያቄ ያስነሣብናል እንጂ አያስመሰግነንም፤ ምናልባት የባለቤትነት ጥያቄን ሊያስከትልብን ይችላል።

መምህሩ ግን ይህ ሁሉ ጥያቄ መነሣቱን ልብ ሳይሉ ራሳቸው ትክክለኛ እንደ ሆኑ በመቍጠር ለአድማጮቻቸው "ምን አላልንም" የሚለውን የሰብከታቸውን አዝማች ያወርዳሉ። አድማጮቻቸውም "አልተሳሳትንም" ብለው ይቀበሏቸዋል። ከዚያ፥ "በሙሴ አማካይነት ታቦትን የሰጠን እግዚአብሔር ነው" በማለት መልሳቸውን ይደመድማሉ።

መምህር ምሕረተ አብ፥ "እኛ ጣዖትን አምልከን አናውቅም" ያሉት ጉዳይ በሚገባ መፈተሽ ያለበት ቢሆንም፥ ጣዖት ሊመለክ እንደማይገባውና እግዚአብሔርም ጣዖትን አጥብቆ እንደሚቃወም የገለጹት ዐቋማቸው ትክክል ነው:: ዐቋማቸው በተግባር ካልታየና በተቃራኒው ከተገለጠ ግን እንዲህ ማለቱ ብቻውን የሚፈይደው ነገር የለም::[64]

በመቀጠል፥ "እኛ የተከተልነውና በመንበራችን ያስቀመጥነው፣ አምልኮታችንን የምንፈጽምበት ታቦት የመጣው ከእግዚአብሔር ከራሱ ... የሚገርም እኮ ነው! በጣቱ ጽፎ እግዚአብሔር ሰጠን" የተባለው ግን፥ በተሳሳቱ ገለጻዎችና በሐሰት ምስክርነት የተሞላ ነው:: ይህን ለማለት የሚያስደፍረው በተሰጠው ገለጻና ማስረጃ ተብሎ በተጠቀሰው የዘፀ. 24፥12 ጥቅስ መካከል የሰማይና የምድር ያህል ርቀት መታየቱ ነው::

ጥቅሱ፥ "እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ወደ እኔ ወደ ተራራው ውጣ፥ በዚያም ሁን፤ እነርሱን ታስተምር ዘንድ እኔ የጻፍሁትን ሕግና ትእዛዝ የድንጋይም ጽላት እሰጥሃለሁ አለው" ይላል:: በጥቅሱ መሠረት ሕግና ትእዛዙን፣ የድንጋዩንም ጽላት ሰጪው እግዚአብሔር፥ ተቀባዩ ደግሞ ሙሴ፥ የተቀበለውም እስራኤላውያንን ለማስተማር እንደ ሆነ ከንባቡ በግልጽ መረዳት ይቻላል:: ነገር ግን በምን መንገድ ቢተረጐም ነው ይህ ንባብ፦ ታቦትን መከተል፣ ታቦትን በመንበር ማስቀመጥና አምልኮትን በታቦት መፈጸም የሚሉትን ኢመጽሐፍ ቅዱሳውያን ፍቺዎች የሚሰጠው? በተለይም አምልኮትን በታቦት መፈጸም የሚለው ከየት የመጣ ልማድ ነው? ደግሞም ታቦት በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን ተሰጠ እንጂ፥ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን መቼና እንዴት ነው የተሰጠን? ከምንም በላይ ደግሞ መምህሩ፥ "የሚገርም እኮ ነው! በጣቱ ጽፎ እግዚአብሔር ሰጠን" ሲሉ ከማፈር ይልቅ "መገረማቸው" ያስገርማል:: የአፍ ወለምታቸውን ለጊዜው አሽተው ያስተካከሉት ቢመስልም በሚገባ እንዳልተጠገነና እንደ ተናጋ ግን ከዚህ ድምዳሜያቸው መገንዘብ ተችሏል::

**ኧረ! ለመሆኑ በኢአተቤክ መቅደስ ውስጥ በመንበር ላይ በተቀመጠው በየትኛው ታቦት ላይ ይሆን እግዚአብሔር በጣቱ የጻፈው? ይህ ማንንም ማሳመን የማይችል ነጭ ውሸት ነው::** እውነቱ ግን የኢትዮጵያ ታቦታት እግዚአብሔር በጣቶቹ የጻፈባቸው ሳይሆኑ፥ በቤተ ክህነት ትምህርት ውስጥ ያለፈ የቅርጻ ቅርጽ ባለሙያ የተጠበበበት የሰው እጅ ሥራ መሆኑ ነው::

መምህር! የሰው እጅ ሥራ የሆነውን ታቦት በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሰጠ አድርገው በማቅረብዎ አልተሳሳትሁም ይላሉ?

## 3.2. ስለ ታቦትና ጣዖት

**"ታቦትን ጣዖት ለሚሉ ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?"**

በንግዱ ዓለም ጥራትና ተፈላጊነት ባላቸው ምርቶች ስም ተመሳስለው የተሠሩ /ፎርጅድ/ ምርቶች ተጠቃሚውን የሚያሳስቱ፥ አምራቹንም ለኪሳራ የሚዳርጉ መሆናቸው ይታወቃል:: ስለ ሆነም ኅብረተ ሰቡ ተመሳስለው በተሠሩ ምርቶች እንዳይታለል፥ የእውነተኛውን ምርት ልዩ ምልክትና መገለጫዎቹን እንዲያውቅ ይደረጋል:: በዚህም እውነተኛውን ተመሳስሎ ከተሠራው ሐሰተኛ ምርት መለየት ይቻላል::

ታቦትን በሚመለከት በቃል ኪዳኑ ታቦትና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል የስም መመሳሰል አለ:: ይሁን እንጂ የቃል ኪዳኑ ታቦት ከኢትዮጵያ ታቦታት የሚለይባቸውን ምልክቶችና መገለጫዎች ስንመለከት፥ የኢትዮጵያ ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ተመሳስለው የተሠሩ ለማለት የሚያስደፍር ተመሳስሎ ባይኖራቸውም፥ ይህን ስፍራ እንስጣቸው ቢባል እንኳ፥ እንደ ቃል ኪዳኑ ታቦት ያሉ አለ መሆናቸውን በቀላሉ መለየት አያስቸግርም::[65]

መምህር ምሕረተ አብ ግን ይህን እውነት ከግምት አላስገቡም፤ ወይም ሆን ብለው ዐልፈዉታል:: ይኸውም ከላይ በርእሱ ለቀረበውና "ታቦትን ጣዖት ለሚሉ ወገኖች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?" ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፥ ጉዳዩን ከቃል ኪዳኑ ታቦትና እርሱን ከሰጠው ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኙታል:: "አንዳንዶች ጣዖትን ነው የምታመልኩት፤ ጣዖትን ነው የምትከተሉት ካሉን ተሳስተዋል፤ ጠቡ ከእግዚአብሔር ጋር ነው" ሲሉም ያስፈራራሉ:: አክለውም ታቦት ጣዖት ከተባለ ታቦትን የሰጠውን እግዚአብሔርን ጣዖትን ሰጠ ያሰኛል ይላሉ:: ይህ መከራከሪያ ላይ ላዩን ለተመለከተው እውነትነት ያለው ይመስላል::

[64] የኢትዮጵያው ታቦት ከጣዖት ጋር ተመሳስሎ ስለ ተነሣው ሐሳብ በ2ኛው ጥያቄ ውስጥ እንመለከታለን::

[65] በዚሁ መጽሐፍ በክፍል ሁለት «ቢቃል ኪዳኑና በኢትዮጵያው ታቦታት መካከል ያሉ ልዩነቶች» በሚለው ርእስ ሥር በሠንጠረዥ የቀረበውን ንጽጽር ይመለከቷል::

ነገር ግን የቃል ኪዳኑን ታቦት ጣዖት ነው ያለ አለ ወይ? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መመለስ አለበት፡፡ ታቦት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእስራኤላውያን የተሰጠ ነውና ማንም ክርስቲያን ይህን ታቦት ጣዖት ነው ሊል ፈጽሞ አይችልም፡፡ ነገር ግን በስም ብቻ ተመሳሰለው በተሠሩት በኢትዮጵያ ታቦታት ላይ የተባለው ትችት ከቀረበ፥ የሐሳቡን እውነት-ሐሰት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር መመልከቱ ወሳኝ ይሆናል፡፡

ለመሆኑ ጣዖትን ጣዖት የሚያደርገው ምንድን ነው? "ጣዖት [በዋናነት] ከዕንጨትና ከቀለጡ ማዕድናት የተሠራ የማምለኪያ ምስል"[66] ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ግዑዛንና ሕያዋን ፍጥረታትም፥ ከተፈጠሩበት ዐላማ ውጪ በአምላክነት ደረጃ ሲታዩ ጣዖት ይሆናሉ፡፡ ጣዖት የሚሆኑት ግን በተፈጥሮአቸው ጣዖታት ስለ ሆኑ አይደለም፤ በአምላክነት ደረጃ ያስቀመጣቸው ሰው እንደ አምላክ ሲመለከታቸው ነው እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ለአንድ የተወሰነ ተግባርና ዐላማ የሰጠው ነገርም፥ ተግባሩን ከፈጸመና ዐላማውን ካሳካ፥ ሰፍራውንም ከለቀቀ በኋላ የቀደመ ተግባሩን ይቀጥል፤ ወይም ሌላ ክብር ይሰጠውና ይመለክ ቢባል ወደ ጣዖትነት እየተሸጋገረ ነው፡፡ ምንም እንኳ በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ቢሆንም አቅጣጫውን ስቷልና ጣዖት መባሉ አይቀርም፡፡

ለዚህ የናሱን እባብ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ በማጕረምረማቸው ምክንያት በእባቦች የተነደፉት እስራኤላውያን፥ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላቸው በጠየቁት ጊዜ ጸለየላቸው፡፡ እግዚአብሔርም በእባቦች ለተነደፉቱ መድኀኒት ይሆን ዘንድ፥ የናስ እባብ እንዲሠራና በዐላማ ላይ እንዲሰቅል ሙሴን አዘዘው፡፡ ወደ ተሰቀለው የናስ እባብ የተመለከቱ ሁሉ ዳኑ፡፡ ይህ እንዲሆን የፈቀደው እግዚአብሔር ነው (ዘኍ. 21፥4-9)፡፡ የናሱ እባብ የተሠራውም ለዚህ ወቅት ብቻ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ የናሱ እባብ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የማዳን ሥራ ሲሠራ አይታይም፡፡ ይሁን እንጂ የታሪካቸው አንድ ክፍል በመሆኑ፥ ለታሪክ መዘከርነት ይዘዉት ተገኝተዋል፡፡ ይህም በራሱ ምንም ክፋት ላይኖረው ይችላል፡፡ ክፋቱ በዚህ መንገድ የተቀመጠውን የናሱን እባብ ወደ ማምለክ መሸጋገራቸው ነው፡፡ ከመቼ ጀምሮ እንደ ሆነ ባይታወቅም፥ እስከ ሕዝቅያስ ዘመን ድረስ ያጥኑለት የነበረውን የናሱን እባብ ንጉሡ ሕዝቅያስ ሰባብሮ አስወግዶታል (2ነገ. 18፥4)፡፡ ለጊዜው ችግር የተሰጠውንና በተፈጥሮው ጣዖት ያልነበረውን የናስ እባብ፥

[66] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1992፣ 254)፡፡





አገልግሎቱ ካበቃ በኋላ ለእርሱ ወደ ማጠን በመሸጋገራቸው እስራኤላውያን ጣዖት አደረጉት ማለት ነው፡፡

በዚሁ ዐይነት የታቦት አገልግሎት ካበቃበት ከባቢሎን ምርኮ በኋላ አገልግሎቱ ቀጥሏል ብሎ ማመን፣ ማስተማርና አምልኮትን መፈጸም፥ አምልኮተ ጣዖት እንጂ አምልኮተ እግዚአብሔር ሊሆን በፍጹም አይችልም፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦትም ቢሆን እንኳ፥ የአገልግሎት ዘመኑ ካበቃ በኋላ ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተሠራ ነው በሚል አምልኮትን ቢፈጽሙበት፥ ድርጊቱ አምልኮተ ጣዖት መሆኑ አይቀርም ነበር፡፡ [በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት በመጨረሻ የት እንደ ደረሰ አለመገለጹና እንዳይታወቅ መድረጉ፥ ሕዝበ እስራኤል በናሱ እባብ ያደረጉትን በታቦቱም እንዳይደግሙ በሚል እንደ ሆነ ማንም አያውቅም፡፡] ይልቁንም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ያልተሠሩትና የሰው እጅ ሥራ ብቻ የሆኑት የኢትዮጵያ ታቦታት፥ ከተሰጣቸው ስፍራና ከሚቀርብላቸው አምልኮት አንጻር ምን ሊባሉ ይሆን?

## 3.3. ስለ ታቦት መባዛት

**"እግዚአብሔር ለሙሴ አንድ የቃል ኪዳን ታቦት ከሰጠው አሁን በየገዳማቱና በየአድባራቱ ያሉ በርካታ ታቦታት ከየት መጡ?"**

ይህን ጥያቄ ለመጽሐፍ ቅዱስ ማቅረብ ቢቻል፥ "ደግሞ የምን የታቦት መባዛት አመጣችሁብኝ?" በሚል ጥያቄውን በጥያቄ እንደሚመልሰው ጥርጥር የለውም፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቀው አንድ የቃል ኪዳን ታቦትን ብቻ ነው፡፡ ከመምህር ምሕረተ አብ እየቀደሙ ጥያቄውን የሚያቀርቡት ሰው ግን፥ "እግዚአብሔር አንድ [ታቦት] ሰጥቶ እናንተ ብዙ ይዛችሁ በመገኘታችሁ ተሳስታችኋል ይሉናል፡፡ እኛ ግን አልተሳሳትንም እንላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንን እውነት መሠረት አድርገናልና" በማለት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ታቦት መባዛት እንደሚናገር በድፍረት ይጠቅሳሉ፡፡ መምህር ምሕረተ አብም፥ "ለዚህም መልሳችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው" ሲሉ ሐሳቡን ያጸድቁታል፡፡

ለዚህ የጠቀሱት ሙሴ በሕዝበ እስራኤል ኀጢአት ተቈጥቶ በሰበራቸው ሁለት ጽላት ምትክ፥ እንደ ፊተኞቹ አድርጎ ሁለት ጽላት ጠርቦ እንዲያመጣ እግዚአብሔር የተናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው (ዘፀ. 32፥1-20፤ 34፥1)፡፡ በተለይም ዘፀአት 34፥1 ላይ ያለውን ቃል እንበበው

በራሳቸው መንገድ ሲገልጹት፥ "ይህ ነገር ተሰብሮ መቅረት የለበትም። እንደበፊተኛው አድርገህ እንድታዘጋጅ ና ፎርሙላውን ልሰጥህ፤ መመሪያውን እንዴት አድርገህ እንደምትሠራ ልሰጥህ አለውና ይላል» በማለት ያላነበቡትን እየተረጐሙ ነው። ይገርማል! ዘፀአት 34፥1 እንዲህ የሚል ንባብ፣ መልእክትም ሆነ ሐሳብ ፈጽሞ የለውም።

ይህ ሁሉ የፈጠራ ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸውን የኢትዮጵያን ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል ነው። ስሕተትን በመጽሐፍ ቅዱስ ማስተካከል ሲገባ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለስሕተት መሸፈኛ አድርጎ ማቅረብ ሰውን እንጂ እግዚአብሔርን ደስ አያሰኝም። መምህር፥ "ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።" (ገላ. 1፥10) በሚለው የታማኝ አገልጋይ ዐቋም እስኪ ራስዎን ይፈትሹ!

ዘፀ. 34፥1 የሚለውስ እንዲህ ነው፤ "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፤ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደ ፊተኞች አድርገህ ጥረብ፤ በሰበርኻቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ።" በዚህ ቃል ውስጥ በግልጽ እንደሚነበበው ሙሴ የድንጋዮቹን ጽላቶች ጠርቦ አመጣ፤ እግዚአብሔር ደግሞ ቃሎቹን ጻፈባቸው። ከዚህ ውጪ በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ስለ ጽላት አሠራር ለሙሴ የሰጠው ቀመርም (ፎርሙላም) ሆነ መመሪያ የለም። መጀመሪያውኑ ና ላሳይህ በማለት ፈንታ ጥረብ ነው ያለው። ሙሴም ቢታዘዘው መሠረት ጽላቱን ጠርቦታል። የጻፈበት ግን እግዚአብሔር ነው። የተከናወነው ይህ ብቻ ከሆነ፥ መምህሩ "እንደበፊተኛው አድርገህ እንድታዘጋጅ ና ፎርሙላውን ልሰጥህ ... አለው" ያሉት ምን ትርጕም ሊኖረው ነው? ምክንያቱም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር የሄደው የጠረበውን ጽላት ይዞ እንጂ የጽላት አጠራረብን ጥበብ ለመማር አይደለም። ወይም የእግዚአብሔርን ድርሻ ወስዶ በጽላቱ ላይ ቃሎቹን እንዴት እንደሚጽፍ ለማየት አልነበረም። ስለዚህ መምህር፥ ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት ብዜት ጕዳይ ደጋፊ የሚሆን ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለማያገኙ፥ ቅዱስ ቃሉን ባያጣምሙና ታቦት የሚባዛበትን ምክንያት ከእነዚያው ከአዋልድ መጻሕፍት ቢፈልጉ ይሻላል።

ማስረጃ ይሆነኛል ብለው የጠቀሱት ቃል የሚናገረው፥ ሙሴ በሰበራቸው ሁለት ጽላት ምትክ እንደ ፊተኞቹ ያሉ ሌሎች ሁለት ጽላት መተካታቸውን ነው፤ በአገራችን እንደሚደረገው ጽላት እንዲባዙ





መፈቀዱን ፈጽሞ አያመለክትም።[67] እርስዎ እንዳሉት ቢሆን ኖሮ እነሙሴ በእስራኤል አውራጃዎች ሁሉ ብዙ አብያተ መቅደስን ባነጹ፥ በርካታ ጽላትም በቀረጹ ነበር። በእስራኤል ታሪክ ግን እንዲህ አልተደረገም። የነበራቸው አንድ ቤተ መቅደስና በአንድ ታቦት ውስጥ የተቀመጡ ሁለት የድንጋይ ጽላት ብቻ ናቸው።

መምህር፥ ርግጥ ያልተጻፈውን አብራርተው ሙሴ "ፎርሙላና መመሪያ ተሰጠው" በሚለው የሐሰት ማብራሪያ የተንደረደሩት፥ የኢትዮጵያን ታቦታት የሚቀርጹትን ሰዎች በሙሴ እግር የተተኩ ናቸው ለማለት እንደ ሆነ ግልጽ አድርገዋል፤ እንዲህ በማለት፥ "ስለዚህ [በ]ቤተ ክርስቲያናችንም በሙሴ እግር የተተኩ ብፁዓን አባቶች፥ እግዚአብሔር በእንዲህ ዐይነት መንገድ ሥሩ ባላቸው መሠረት፥ ጽላት እየቀረጹ፥ እግዚአብሔር ባዘዘው መመሪያ መሠረት ይህን እየሠሩ፥ በቤተ ክርስቲያን፣ በመቅደሱ፣ በመንበሩ ማስቀመጣቸው ስሕተት ሳይሆን ትክክል ነው።" የሚገርም ሌላ ውሸት ነው!!

በዚህ ገለጻዎ ውስጥ አንድም እውነት የለም። ነገር ግን ቢያንስ ሦስት ውሸቶችን ነቅሶ ማውጣት ይቻላል።

1. ሙሴንና የቤተ ክርስቲያናችንን ጳጳሳት የሚያገናኛቸውና የሚያተካካቸው ምንም ምክንያት የለም። ሙሴ በብሉይ ኪዳን የእስራኤል መሪ፥ ብፁዓን አባቶች ደግሞ በሐዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች ናቸው። በሙሴ እግር የተተኩት ከኢያሱ ጀምሮ ያሉ በእስራኤል ላይ የተሾሙ መሳፍንት፣ ነቢያትና ነገሥት ናቸው እንጂ በኢኦተቤክ ላይ የተሾሙ ጳጳሳት አይደሉም። ብፁዓን አባቶችም ቢሆኑ ራሳቸውን በሐዋርያት እግር እንደ ተተኩ እንጂ የሙሴ ምትክ እንደ ሆኑ አይቈጥሩም። ስለዚህ በሙሴ እግር ተተኩ የሚለው አያስኬድም።

2. ብፁዓን አባቶች ጽላት እንዲቀርጹ እግዚአብሔር አዘዛቸው የሚለውም ምንጭ አልባ የሐሰት ምስክርነት ነው። ሙሴ በሰበራቸው ሁለት ጽላት ምትክ አንደ ፊተኞቹ አድርጎ ሁለት ጽላቶችን ብቻ እንዲቀርጽ እግዚአብሔር ለአንዴም ለመጨረሻ ጊዜም ያዘዘው ሙሴን ብቻ ነው። ከእርሱ በኋላ ጽላት

[67] ስለዚህ ጕዳይ ይበልጥ ለመገንዘብ «የተቀበረ መክሊት» የተሰኘውን መጽሐፍ ገጽ 106 ላይ ያለውን ይመልከቱ።

የሚጠረብበት ምክንያት ስለሌለም ጽላት እንዲጠርብ የታዘዘ፥ እንኳ ኢትዮጵያዊ እስራኤላዊም የለም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ታቦታት/ጽላት እንዲቀረጹ እግዚአብሔር አዘዘ ብሎ ያልተጻፈ ከማንበብና ሕዝብን ከማሳሳት ይልቅ፥ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች አዘዙ፤ በፍትሐ ነገሥት ጽላት እንዲቀረጽ ደነገጉ[68] ቢባል ሊያስኬድ ይችላል።

3. ጽላት የሚቀርጹት ብፁዓን አባቶች ናቸው መባሉም ፍጹም ሐሰት ነው። ፍትሐ ነገሥት ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ በሚቻል መልኩ ጽላት እንዲቀረጽ ደንግጓል። ከዚህ ውጪ ስለሚቀርጹት ሰዎች ማንነት ያለው ነገር የለም። ርግጥ ሲቀርጹ አልሰማንም፥ አላየንም እንጂ፥ የቅርጻ ቅርጽ ሙያ ያላቸው ጳጳሳት ካሉ ጽላት ሊቀርጹ ይችላሉ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ታቦታት/ጽላት የሚቀረጹት የቤተ ክህነት ትምህርትና የቅርጻ ቅርጽ ሙያ ባላቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ነው። ከዚህ በቀር ጽላትን ለመቅረጽ የሚያስችል ሌላ መሰፈርት ያለ አይመስልም። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ጽላት የሚቀረጸው በጳጳሳት ነው ማለት ለምን አስፈለገ? ያው እንደ ተለመደው ሕዝቡ ታቦታቱን አቃልሎ እንዳይመለከታቸውና የተለየ ክብርና አምልኮ እንዲሰጣቸው ለማድረግ አይደለምን? ለነገሩ ጳጳስም ይቅረጸው ሌላ እግዚአብሔር ያላዘዘው በመሆኑ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም።

ነገር ግን እርስዎ ያሉት ሁሉ ይሁንና፥ **ብፁዓን አበው እንደ ሙሴ ጽላቱን ጠረቡ እንበል፤ ግን በእነዚህ ሁሉ ጽላቶች ላይ ማን ጻፈባቸው?** ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተነገረውን ሁሉ ለኢትዮጵያ ታቦታት ሰጥተው እንዳስተማሩት፥ እግዚአብሔር ነው የጻፈው ማለት እንኳ ሊነገር የማይታሰብ ነው። ዛሬ የሰማዎ ሁሉ የተቀበለዎ እንዳይመስልዎ፤ ያጨበጨበልዎ ምእመን ነገ እያነበበና እየተረዳ ሲመጣ፥ እርስዎንም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትዎንም መተዉ አይቀርም። የባሰው ግን ሕዝብን ከእግዚአብሔር መንገድ ማስወጣት በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅና ጽኑ ፍርድ የሚያመጣ ነው።

መምህር፥ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውና በተጨባጩ እውነት የፈረሰውን የሐሰት ምስክርነትዎን ብርድ እንዳይመታው ሠግተው ነው መሰል፥ "መምህር ዘበነ የተናገሩት" ብለው በጠቀሱት ማስረጃ ለመሸፈን

[68] ፍትሐ ነገሥት (1990፣ 21)።





ሞክረዋል። የጠቀሱትና "ውስጤ አለ እስካሁን" ያሉት የመምህር ዘበነ ምሳሌ በእርስዎ አገላለጽ እንዲህ የሚል ነው፤

> በመጀመሪያ ስንት መጽሐፍ ቅዱስ ነበር? ... አንድ አይደል! ... አስፈላጊ ስለ ሆነ በክርስቲያኖች ሁሉ እጅ እንዲገኝ፥ ተባዝቶ እንዲገኝ ተደረገ። እንደዚሁም አንዱ የቃል ኪዳን ታቦት፥ ታቦተ ሕጉ አስፈላጊ ስለ ሆነ፥ ካህናት፣ ምእመናን፣ አባቶች፣ አማንያን ባሉበት ቦታ፥ በገዳማትና በአድባራት ሁሉ እየተቀረጸ እንዲቀመጥ በመደረጉ ትክክል ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ታቦታትም እየተባዙ በየግለ ሰቡ ቤት ሁሉ ሊቀመጡ ይገባል እለ ማለትዎ መልካም ነው።

አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ እየተባዛ በሰዎች እጅ ውስጥ እንዲገባ መደረጉ አስፈላጊና ተገቢ የሆነ ቅዱስ ተግባር ነው። ቃሉ ለሰው የተሰጠበት ዐቢይ ምክንያት፥ ሰው አንብቦት እውነትን እንዲያውቅና ወደ ዘላለም ሕይወት ለመግባት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነውና። የቃል ኪዳኑ ታቦት ግን መጀመሪያውኑ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ተግባር ለመፈጸም የተሰጠ አይደለም። ስለዚህ እንዲባዛም ሆነ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ካልሆነ በቀር፥ በተለያዩ ሰፍራዎች እንዲቀመጥ አልታዘዘም። የኢትዮጵያው ዝርግ ሰሌዳ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ መባዛት ጋር መነጻጸር ሳያስፈልገው፥ ለሥጋ ወደሙ መከበሪያ በሆነው አገልግሎቱ ብቻ በየቤተ ክርስቲያኑ መገኘቱ በራሱ ስሕተት የለውም። ታቦት ተብሎ መጠራቱና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሊባዛ ይችላል መባሉ ነው ስሕተት የሚሆነው። ታዲያስ መምህር፥ አሁንም አልተሳሳትሁም እያሉ ነው?

## 3.4. ታቦትን ስለ መንካት-አለ መንካት

**"ጽላቱን ወይም ታቦቱን ማንም ሊነካው ይችላል ወይ?"**

የኢትዮጵያ ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንደሌላቸው በተደጋጋሚ ለማሳየት ተሞክሯል። መምህር ምሕረተ አብ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። የፈለጉትን ሊያገኙ እንደማይችሉ ቢያውቁትም፥ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተጻፈውን ሁሉ ለኢትዮጵያ ታቦታት በመጥቀስ ሁለቱን ሊያመሳስሏቸው ሞክረዋል። በዚህም ለጊዜው በቃል ኪዳኑ ታቦትና በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል

ያለውን ልዩነት ያላስተዋሉ ሰዎችን አስጨብጭበዋል፡፡ የሁለቱን ልዩነቶች ሲረዱና የኢትዮጵያ ታቦታት በተለጠፈላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስና ታሪክ መሠረት የሚጠበቅባቸውን መሆንና ማድረግ እንደማይችሉ ሲያስተውሉ ግን ጥያቄ ማንሣታቸው አይቀርም፡፡

መምህሩ፥ ታቦትን ስለ መንካት አለ መንካት በ1ዜና. 13፥9 ላይ የተጻፈውን የዖዛን ታሪክ በመጥቀስ፥ የእግዚአብሔርን ታቦት ማንም በዘፈቀደ ዘሎ ሊነካው እንደማይችል ተናግረዋል፡፡ በርግጥም የተናገሩት ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ከሆነ ትክክል ነው፡፡ "ወደ አውድማ ዳርም በደረሱ ጊዜ ላሞቹ ስረገላውን ሲስቡ የእግዚአብሔር ታቦት ዘንበል ብላለችና ታቦቷን ሊይዝ ዖዛ እጁን ዘረጋ፡፡ እግዚአብሔርም በዖዛ ላይ ተቈጣ፡፡ እጁንም ወደ እግዚአብሔር ታቦት ስለዘረጋ ቀሠፈው፤ በዚያም በእግዚአብሔር ፊት ሞተ" ተብሎ ተጽፏልና (1ዜና. 13፥9-10 የ2000 ዕትም)፡፡

የኢኦተቤክ ባሳተመችው የ2000 ዓ.ም. ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ፥ የእግዚአብሔር ታቦት በወንድም፥ በሴትም አንቀጽ ተጠርቷል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ክፍል እንደሚነበበውም በሴት አንቀጽ ነው የተጠራችው፡፡ በ1953 ዓ.ም. ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን በወንድ አንቀጽ ነው የተጠራው፡፡ ርግጥ ታቦቱ በራሱ ሕይወት የሌለው ግዑዝ ነገር በመሆኑ፥ በወንድ ወይም በሴት አንቀጽ መጠራቱ በራሱ ችግር ላይኖረው ይችላል፡፡ ነገር ግን በሴት አንቀጽ መጠራቷ (እንቺታው)፥ የእግዚአብሔርን ታቦት "ታቦተ ጽዮን" ወደ መባል ማሸጋገሩ ነው ችግሩ፡፡ ይህም ጽዮን ማርያም ነች በሚል ታቦቱ "የእግዚአብሔር ታቦት" መባሉ ይቀርና "ታቦተ ማርያም" ወደሚለው ስሕተት ያደርሳል፡፡ መምህር ምሕረተ አብም በዚህ መንገድ ላይ የቆሙ ይመስላል፡፡ ይኸውም ከላይ የተጠቀሰውን የ1ዜና. 13፥9 ክፍል ሲያነቡ ከየትኛው ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳነበቡ ባይገልጹም፥ የእግዚአብሔርን ታቦት "ታቦተ ጽዮን" በሚል ስም ነው የጠሩት፡፡ አዋልድ መጻሕፍት ካልሆኑ በስተቀር የቃል ኪዳኑን ታቦት "ታቦተ ጽዮን" የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ግን ፈጽሞ የለም፡፡

በስመ ታቦት፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት በማንኛውም ሰው ያለ መገሠሥ (ያለ መነካት) ክብር፥ ለኢትዮጵያ ታቦታት መጥቀሱ ብዙ አያዋጣም፡፡ ምክንያቱም በቃል ኪዳኑ ታቦት ይደረግ እንደ ነበረው፥ የኢትዮጵያን ታቦታት በመንካት የሚከተል አሉታዊ ውጤት አይታይም፡፡ መምህር ምሕረተ አብ ግን፥ "ታቦቱን እንንካ የማለት መብት አለን፤ መንካትም እንችላለን፤ ግን ድጋሚ መንካት አንችልም፤ ለምን እንሞታለንና" በማለት





ከቀሳውስት ውጪ ታቦቱን በድፍረት በሚነካው ላይ ስለሚከተለው ቅጣት ተናግረዋል፡፡ ይህን ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ተናግረውት ከሆነ ሐሰት ነው የሚል አይኖርም፤ በዖዛ ላይ የሆነውን ሁሉም ያውቃልና፡፡ ነገር ግን ይህ በኢትዮጵያ ታቦታት ላይ ሲሠራ ስለማይታይ፥ ማስፈራሪያቸው "ገበሬ አስደንግጥ" የሚባለው ዐይነት ጥቅስ ይሆናል፡፡

ከቀድሞ ጀምሮ ታቦታቱን የመንካት መብት በተሰጠው ቄስም ይሁን በሌላ ሰው የኢትዮጵያ ታቦታት ይሰረቃሉ፡፡ ከዚያ በውድ ዋጋ እየተሸጡ ከአገር የሚወጡበት አጋጣሚ እንደ ነበረና አሁንም እንዳለ ይነገራል፡፡ በዚህ መካከል የሰረቁት፣ ለመሸጥ የሚደልሉትና የሚገዙት በፖሊስ ቍጥጥር ሥር ሲውሉ፥ ጉዳዩ እስኪጣራና ለባለ ንብረቱ ደብር እስኪመለስ ድረስ ታቦታቱም በኤግዚቢትነት ይያዛሉ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን እንግዲህ ታቦቱ ከሰረቀው ሰው እስከ መርማሪው ፖሊስ ድረስ እርሱን የመንካት መብት በሌላቸው የተለያዩ ሰዎች እጅ ይገሠሣል፡፡ ይሁን እንጂ መጀመሪያውኑ ራሱን ከመሰረቅ ያላዳነው ታቦት፥ ማንንም ሲቀሥፍ አልታየም፤ ማንንም ሊያድን አይችልም፡፡

ያልሆነውን ሆነ፥ የማይደረገውን ተደረገ ከማለት የበለጠ ስሕተት አይኖርም፡፡ ስለዚህ መምህር አልተሳሳትንምን ትተው ተሳስተናልን ቢይዙ መልካም ነው፤ ስሕተትን መረዳት ለንስሓ ያበቃልና፡፡

### 3.5. ወደ ታቦት ስለማይቀረብበት ምክንያት

"ሁሉም ሰው እንደ ልቡ ሊቀርበውና ሊነካው የማይችለውን ታቦተ ሕግ ይዛችሁ በመገኘታችሁ ተሳስታችኋል፤ ለምን ሁሉም ሊነካው አልቻለም? ለሚሉ ወገኖችም የምንሰጠው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ አለ" ስለ ተባለው፤

እውን ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የሰማና ያነበበ ሰው ይህን ጥያቄ ያቀርባልን? በፍጹም አያቀርብም፡፡ ምክንያቱም እስራኤላውያን ተጓዦች በነበሩባቸው ዓመታት፥ ጉዞ ለመጀመር የማደሪያው ድንኳን ሲነቀልና ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ሲወጡ፥ ሕዝቡ በማደሪያው ድንኳን ዙሪያ ከሰፈረበት ጊዜያዊ ሰፈር ተነሥቶ እንዲከተል፥ በሕዝቡና ታቦቱን በተሸከሙት ካህናት መካከልም ሁለት ሺህ ክንድ (አንድ ሺህ ሜትር ወይም አንድ ኪሎ ሜትር) ርቀት እንዲኖር መታዘዙ ግልጽ ነው (ኢያ. 3፥1-4)፡፡ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር በተያያዘ ይህን ጥያቄ ያነሣ ወይም

የሚያነሣ ክርስቲያን አለ መኖሩ እየታወቀ ታዲያ፥ መምህር ምሕረተ አብ ጥያቄውን ሰዎች እንደሚያነሡት አስመስለው ለምን አቀረቡት?
ከላይ በ4ኛ ተራ ቍጥር እንደ ተመለከትነው፥ ይህም ነጥብ መምህሩ የኢትዮጵያን ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ለማመሳሰል የያዙት ጥረት አካል ሆኖ ይታያል። ለኢትዮጵያ ታቦታት ለሚደረገው ንግሣዊ በዓልና በበዓሉ ላይ ለሚታየው አምልኮታዊ ሥርዐት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሽፋን ለመስጠት ሲሉ፥ በሰዎች ስም በጥያቄ ጠቅልለው ያቀረቡት የራሳቸው ሐሳብም ነው የሚመስለው። ይሁንና የኢትዮጵያ ታቦታት እንዲህ ያለ ጥያቄ ቢቀርብባቸው ያንስባቸዋል እንጂ አይበዛባቸውም።

ዋናው ጥያቄ መሆን ያለበት ግን፥ የኢትዮጵያን ታቦታት "ሁሉም ሰው እንደ ልቡ ሊቀርበውና ሊነካው ... ለምን ... አልቻለም?" የሚለው አይደለም፤ ዋና መጠየቅ ያለበት ጕዳይ እስራኤላውያን ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ባላቸው ታሪክና ግንኙነት ያላደረጉትን የታቦት በዓለ ንግሥ፥ የኢኦተቤክ ለምን ታደርጋለች? የሚለው ነው። በመሠረቱ የአሪት ካህናት የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙበት ምክንያትና የኢኦተቤክ ካህናት (ቀሳውስት) የኢትዮጵያን ታቦታት የሚሸከሙባቸው ምክንያቶች ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው።[69] እነዚያ በዋናነት የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ተጓዦች ስለ ነበሩ ሲሆን፥ እነዚህ ደግሞ በንግሥ በዓል ስምና በሌሎችም ምክንያቶች ነው ታቦታቱን የሚሸከሟቸው።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው የመምህር ምሕረተ አብ ዋና ጕዳይ፥ ታቦት በተሸከሙ ካህናትና በሚያጅቡት ሕዝብ መካከል ርቀት ሊኖር ይገባል የሚለው አለ መሆኑ አያጠራጥርም። ይህ ለተነሣው ነጥብ ሽፋን የሚሆን ጥቅስ ሲፈለግ በአግረ መንገድ የተወሣ መሆኑ ግልጽ ነውና። ዋናው ነጥባቸውና የሐሳባቸው ማእከል ግን የኢኦተቤክ ምእመናን ታቦቱ ሲነግሥ፥ ሴቱ በእልልታ ወንዱ በሆታ ማጀባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ማሳየት ነው። ለዚህም መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 3፥3 ላይ ያለውን በመጥቀስ ሲያብራሩ ሐሳባቸው ምን እንደ ሆነ ግልጽ አድርገዋል።

ይህ ቃል የተነገረበትን ምክንያት በዐውደ ምንባቡ መሠረት በመነሻው ላይ ተመልክተናልና እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም። መምህሩ፥

[69] ካህናተ ኦሪት የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙባቸውን ጊዜያቶችና ምክንያቶች በሚመለከት በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 13 ላይ የተጻፈውን ያስታውሷል።





እስራኤል በጕዞ ላይ ሳሉ ካረፉበት ጊዜያዊ ሰፈር ተነሥተው ዮርዳኖስን ለመሻገር ሲጓዙ፥ ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገር በሚመለከት የተሰጠውን የኢያ. 3፥3ን መመሪያ በቀጥታ ከኢትዮጵያው የታቦት ንግሥ ሁኔታ ጋር ያገናኙታል። እንዲህ በማለት፥

> ሌዋውያን ካህናት ታቦቱን ተሸክመው ባያችሁ ጊዜ ከሰፈር ተነሥታችሁ ተከተሉት። ሱቅ ያላችሁ ሱቃችሁን ዝጉ፤ ፈረሰኛው ከፈረስ ይውረድ፤ የመንግሥት ሠራተኛው ለዚያን ዕለት ቢሮውን ይዝጋ፤ ገበሬው ሞፈር ቀንበሩን ይስቀል፤ ሹፌሩ መኪናውን ሞተር አጥፍቶ ከመኪናው ይውረድ፤ ሥራ ያለው ሁሉም ሰው ሥራውን ይተው፤ ተማሪም ከትምህርት ገበታው ላይ ያቺን ሰዓት ለእግዚአብሔር ይስጥ፤ ሁል ጊዜ አይደለም ያቺን ሰዓት። ከዚያ ካህናትን በዝማሬ፣ በሆታ፣ በእልልታ፣ በመለከትና በነጋሪት ድምፅ ተከተሏቸው። ... አቤት ደስ ሲል! ... ለካስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው!

[እግዚኦ ܼመሐረነ ክርስቶስ!] በርግጥ እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?

የኢትዮጵያ ታቦታት ከስሙ በተጨማሪ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ሊመሳሰሉባቸው ይችላሉ የተባሉ፥ በቃል ኪዳኑ ታቦት የታዩና የተከናወኑ ሌሎች ነገሮችን አመሳስሎ ለማሳየትና ለማከናወን የተሞከረባቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ። በመምህር ምሕረተ አብ ለኢያ. 3፥3 ጥቅስ የተሰጠው ማብራሪያም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ጥቅሱ እግዚአብሔር በማግሥቱ የዮርዳኖስን ወንዝ በመክፈል ድንቅን ስለሚያደርግ (3፥5) እስራኤል ከዮርዳኖስ ወዲህ ማዶ ከሰፈሩበት ተነሥተው ለጕዞ እንዲዘጋጁና፥ የአካሄዳቸውን ሁኔታ እንዲያውቁ የተሰጠ የአንድ ጊዜ መመሪያ ነው። መምህሩ ግን በኢትዮጵያ ለበዓለ ጥምቀት ለሚደረገው ታቦት የማጀብ ሥርዐት የተደነገገ ቋሚ ሕግ አድርገው ነው ያቀረቡት።

ኢያሱ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከሙትን ሌዋውያን ካህናት ባዩ ጊዜ ከሰፈራቸው ተነሥተው እንዲከተሉት ያዘዘው፥ በማደሪያው ድንኳን በየተመደበላቸው ሰፍራ[70] የሰፈሩትን ሕዝብ ነው። መምህሩ ደግሞ፥ በተለያየ ቦታና በተለያየ ሥራ ተሰማርተው የሚገኙት ሁሉ ሥራቸውን

[70] በማደሪያው ድንኳን ዙሪያ የእስራኤል ልጆች ስለሚሰፍሩበት አቀጣጫ በዘኍልቍ ምዕራፍ 2 ላይ የተጻፈውን ይመለከቷል።

ትተው የኢትዮጵያን ታቦታት እንዲያጅቡ ነው የሚጋብዙት፡፡ በመጨረሻም፥ "አቤት ደስ ሲል! ... ለካስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው!" በማለት ራሳቸውን በራሳቸው ያስገርማሉ፡፡

የእስራኤላውያን ብቻ የሆነውን የቃል ኪዳኑን ታቦት ያለፈ ታሪካዊ ድርጊት፥ አስመስለው እንዲደግሙት ኢትዮጵያውያንን የሚያነሣሣቸው ምን ታሪካዊም ሆነ ሞራላዊ ግዴታ ይኖራል? ይህን ታሪክ ለመዘከርስ ቢሆን የተጠቀሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍል ይበልጥ ስሜት የሚሰጠው ለእነ ማን ነው? ለእስራኤላውያን ወይስ ለኢትዮጵያውያን? ከቃሉ ውጪ በሆነ ሁኔታ የእስራኤልን ታሪክ በመታከክ አምልኮት እየተፈጸመባቸው ያሉትን የኢትዮጵያን ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስመስሎ ማቅረብስ እንዴት ይቻላል?

በዚህ ክፍል መምህሩ ከተናገሩት ሳይጠቀስ የማይታለፈው ታቦቱን "እሳተ መለኮት" ሲሉ መጥራታቸው ነው፡፡ መለኮት በሚለው ስም ለመጠራት መብቱ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ከእርሱ በቀር ማንም በዚህ ስም ሊጠራ አይችልም፡፡ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ፥ "መለኮት የሚል ስም እንዲህ ነው፤ ይህ ነው ይህን ይመስላል ተብሎ በማይነገርና በማይታወቅ ጠባይው የሚጠራበት የልዑል እግዚአብሔር ስም ነውና፥ ከልዑል እግዚአብሔር ውጪ የሚታይ ይሁን የማይታይ ማን ወይ ምን በሚል ጥያቄ የሚፈለግ እንዳች ነገር በዚህ ስም ሊጠራበት አይችልም፡፡"[71] ይላሉ፡፡ መምህር ምሕረተ አብ ግን ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ተናግሮም ተሰምቶም የማያውቀውን፥ የኢትዮጵያን ታቦታት "እሳተ መለኮት" ሲሉ አለ መፍራታቸው አስደንጋጭ ነው፡፡ ታቦቱን መለኮታዊ አድርገው የሚያቀርቡት በዚህ ክፍል ብቻ አይደለም፡፡ በዘጠነኛው ነጥብ ውስጥም ሁለት ጊዜ ያህል ታቦት መለኮታዊ ነው ብለዋል፡፡

በዐዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት አለ መኖሩ እየታወቀ የታቦት አገልግሎት ቀጥሏል ብሎ ማመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ ስሕተቱ ግን በዚህ ሳያበቃ ታቦት መለኮታዊ ነው እስከሚለው ጥግ ድረስ ሄዷል፡፡ ለመሆኑ የስሕተት ትምህርት ገደብ የለውም ወይ? ጥጉስ የት ድረስ ነው? ታቦት እሳተ መለኮት ነው ሲባል "እንዲህስ አይባልም! ይህ ስሕተት ነው!" የሚል ሰውስ የለም ወይ?

[71] (1988፣ 86)፡፡





## 3.6. ታቦታት አሪታውያን ያሰኛሉ?

"እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በታቦቱ ፊት አከብረን ስንዘምር፣ ስንሰግድ፣ እልል ስንል አንዳንዶች ቢነቅፉን፥ 'እነዚህ አሪታውያን ትክክል አይደሉም፤ ተሳስተዋል፤' ቢሉን አልተሳሳትንም፤ እነርሱ ግን ተሳስተዋል፡፡ ዐልፈውም ደግሞ ነቀፉ አላቆም ካሉ የእግዚአብሔር ቍጣ በእነርሱ ላይ ይገለጣል ይላል መጽሐፍ ቅዱስ (2ሳሙ. 6፥20)፡፡" ስለ ተባለው፤

አሪታዊነትን በወንጌል ውስጥ ይዛ በመገኘቷ ቤተ ክርስቲያን ትክክል ነች ተብላ የምትመሰገንበት፤ ወይም ተሳስታለች ተብላ የምትነቀፍበት መለኪያ ሊኖር ይገባል፡፡ መለኪያውም ሌላ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ይልቁንም አሪት ፍጻሜ ማግኘቱንና ስፍራውን ለወንጌል መልቀቁን የሚመሰክሩት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚያስተምሩት ትምህርት ዋና መለኪያ ነው፡፡

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በዋናነት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት የሚያብራሩ ሲሆኑ፥ የብሉይ ኪዳን ትንቢትና ምሳሌ፥ የአሪት መሥዋዕት፤ ሥርዐትና የተቀደሱ ዕቃዎች የሚገልጡትና የሚያሳዩት እማናዊው ነገርና አካሉ በሐዲስ ኪዳን ምን እንደ ሆነ ይናገራሉ (ቈላ. 2፥16-17፤ ዕብ. 8፥5፤ 9፥24፤ 10፥1)፡፡

ከብሉይ ኪዳን የተቀደሱ ዕቃዎች አንዱ ስለ ሆነው ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት፥ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምን እንደሚሉ "በዐዲስ ኪዳን ታቦት አለን?" በሚለው ርእስ ሥር አንዳንድ ነጥቦችን ማንሣታችን ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ በስድስተኛው ጥያቄ የተነሣው ሐሳብ፥ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ስለ ታቦት ከተጻፈውና ከተገለጠው ነገር ጋር ፈጽሞ የማይመሳሰል ሆኖ ይታያል፡፡ መምህር ምሕረተ አብ ግን በኢትዮጵያ የሚደረገውን የታቦት ንግሥ ሥርዐት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለማስመሰል፥ በሌላ ዐውድ የተጻፈውን ቃል ኢትዮጵያዊ ዐውድ ሰጥተው ይተረጕሙታል፡፡

በቃል ኪዳኑ ታቦት ዘንድ የሌለና ያልተደረገ፥ በኢትዮጵያ ታቦታት ዘንድ ግን የሚታዩና የሚደረጉ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በእግዚአብሔርና በተለያዩ ቅዱሳን ስም ለተሰየሙት ታቦታት የበዓላት ቀናት ተለይተው፥ [የጥምቀትን በዓል ሳይጨምር] ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የንግሥ በዓል የሚደረግላቸው መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ በዚህ ሥነ

ሥርዐት ላይ ለታቦታቱ ዝማሬ፣ ስግደት፣ እልልታና ሆታ ይቀርባሉ:: ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ዝማሬዎች መኖራቸው ባይካድም፥ አንዳንዶችም ቢታቦቱ ላይ ለተጻፈው ስመ አምላክ ነው የሚሰገደው ብለው ለማስተባበል ቢሞክሩም፥ ስግደቱ፣ እልልታውና ሆታው ግን በአብዛኛው በቀጥታ ለታቦታቱ የሚቀርብ ነው:: ይህ ሁኔታ በቃል ኪዳኑ ታቦት ያልተደረገና ከአሪታዊነት ወጣ ያለ በመሆኑ አሪታዊነት ሊባል፥ እንዲህ የሚያደርጉትም አሪታውያን ተብለው ሊገለጹ የሚቻል አይደለም::

መምህሩ በዚህ ክፍል ላነሡት ሐሳባቸው ድጋፍ ይሆነኛል በሚል የጠቀሱት 2ሳሙ. 6፥20ን ነው:: የዚህን ጥቅስ ሙሉ ሐሳብ ለማግኘት ቢያንስ ከቍጥር 12 ጀምሮ መመልከት ያስፈልጋል:: ክፍሉ ንጉሥ ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት የጌት ሰው ከሆነው ከአቢዳራ ቤት ወደ ከተማው ለማምጣት ስለ ተደረገው በዓል ይናገራል:: በዓሉ ለአንድ ጊዜ በዚሁ ወቅት ብቻ የተደረገ እንጂ፥ ከዚህ ቀደም ሲከበር የኖረ፥ ለወደ ፊቱም ዓመታዊ በዓል ሆኖ እንዲቀጥል የተወሰነ አልነበረም:: በዚህ ሥነ ሥርዐት ላይ ዳዊት "በሙሉ ኀይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘፍን ነበር" (ቍጥር 14):: ታቦቱ ወደ ዳዊት ከተማ በገባ ጊዜም የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ትመለከት ነበርና፥ "... ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘፍን አየች፤ በልብዋም ናቀችው" (ቍጥር 16)::

ሜልኮል ዳዊትን ለምን ናቀችው? ሜልኮል በዳዊት ላይ ንቀት ያደረባት፥ መምህር እንዳሉት ቢቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ለምን ተዘመረ በሚል መንፈስ አልነበረም:: ነገር ግን ንጉሥ ዳዊት ባሏ እንደ መሆኑ መጠን፥ የንጉሥነቱን ክብር ባልጠበቀ አኳኋን እንደ ተራ ሰው ሲዘልና ሲዘፍን በማየቷ ክብሩን አልጠበቀም ብላ ነው የናቀችው:: ጉዳዩ ባለቤቴ ክብሩን አዋረደ የሚል እንጂ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር የሚገናኝ አይደለም ማለት ነው:: ታዲያ ሜልኮል ባሏ ንጉሥ ዳዊት ራሱን አዋርዶ ስላየችው ንቀት ማሳየቷ፥ ከኢትዮጵያ ታቦታት ጋር ምን አገናኘው? ደግሞስ 'የኢትዮጵያ ታቦታት ከእግዚአብሔር ታቦት ጋር አንድ አይደሉምና፥ ለቃል ኪዳኑ ታቦት እንኳ ያልተደረገውን ቋሚና ዓመታዊ የንግሥ በዓላትን አዘጋጅቶ አምልኮት ማቅረብ አገራዊ ልማድ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ቢባል እንደ ነቀፌታ ለምን ተቈጠረ?

ከላይ ማስረጃ ይሆናል ተብሎ የተጠቀሰው፥ የኢትዮጵያን ታቦታት ሊገልጽ የሚችልበት አንድም ነጥብ አይታይም:: ይሁን እንጂ ይህ ግድ





ያልሰጣቸው መምህር ምሕረተ አብ፥ ለጥቅሱ ኢትዮጵያዊ ዐውድ አጕናጽፈው፥ ዳዊትና ሕዝቡ ያላደረጉትንና ያላሉትን፥ አድርገዋል፤ ብለዋል ይላሉ:: "... ዳዊት ሕዝቡን አሰናብቶ 'እወዳችኋለሁ፤ የዛሬ ዓመት በሰላም ያገናኘን፤ ጸበል፣ ጸዲቅ ቅመሱ፤ እኔም የእናንተ ነኝ፤ እናንተም የእኔ ናችሁ' ብሎ፥ [ከ]ሕዝቡ ጋ[ር] ተቃቅፎ 'ዳዊት እንወድሃለን ሺህ ዓመት ንገሥ' እያሉ ሕዝቡ ፍቅሩን ገልጾለት በሰላም ተበተነ::" በዚህ ገለጻ ውስጥ መምህሩ ስብከት ለማሳመር ብለው፥ ቃሉን በኢትዮጵያ ዐውድ ሲተረጕሙት ከተጻፈው ዐልፈዋል::

እንደ ገለጻቸው ከሆነ በዓሉ ዳዊትና ሕዝቡ የቃል ኪዳኑን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ ለማምጣት የተደረገ ሳይሆን፥ በኢትዮጵያ እንደሚታየው ዓመታዊ የታቦት የንግሥ በዓል ለማክበር የተዘጋጀ ነው የሚመስለው:: በተለይ፥ "... የዛሬ ዓመት በሰላም ያገናኘን፤ ጸበል፣ ጸዲቅ ቅመሱ፤" የሚለው ገለጻቸው ፍጹም ኢትዮጵያዊ ቅብ የተቀባ ነው::

ለመሆኑ ዳዊት የዛሬ ዓመት ያገናኘን ያለው የቱ ጋ ነው? እንዲህ ለማለት የሚያበቃውስ ምን ነገር አለ? ምክንያቱም የቃል ኪዳኑ ታቦት ከአባዲራ ቤት ወጥቶ ወደ ዳዊት ከተማ መግባቱ አንድ ጊዜ የተከናወነ እንጂ ተደጋጋሚ ክሥተት አይደለም:: ስለዚህ በኢትዮጵያ እንደሚደረገው በየዓመቱ የሚከበር የታቦት የንግሥ በዓል ስለሌለ፥ ሕዝቡን ለቀጣዩ ዓመት በሰላም ያገናኘን የሚልበት አንድም ምክንያት አይኖርም:: ዳዊት አለ እንዳሉት በቀጣዩ ዓመት ተመሳሳይ በዓል ማድረጉን የሚናገር አንድም ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሊያቀርቡም አይችሉም? ቀድሞም ቢሆን ዳዊት ታቦቱን በአቢዳራ ቤት እንዲቀመጥ ያደረገው በዖዛ መቀሠፍ ዐዝኖ ነው:: በኋላ አቢዳራ መባረኩን ሲሰማ በዓል አድርጎ ታቦቱን ወሰደው:: ድርጊቱ አንድ ጊዜ የተፈጸመ እንጂ የሚደጋገም ስላልሆነ፥ ዳዊት የዛሬ ዓመት ያገናኘን የሚያሰኘው አንድም ምክንያት የለም ማለት ነው::

ሌላው አስገራሚ ነገር የ"ጠበል-ጠዲቅ" ጉዳይ መነሣቱ ነው:: በዚህ ክፍል ዳዊት መሥዋዕት አሳርጎ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ስም ከመረቀ በኋላ፥ በበዓሉ ላይ ለታደመው ሕዝብ በነፍስ-ወከፍ አንዳንድ እንጀራ፣ ቍራጭ ሥጋና የዘቢብ ጥፍጥፍ ማከፋፈሉ ተጽፏል (ቍጥር 18-19):: ይህም ከአገራችን "ጠበል-ጠዲቅ" ጋር ተገናኝቶ የተነገረ ከሆነ፥ አሁንም ታሪኩን ኢትዮጵያዊ ቅብ ለመቀባት ተፈልጎ የተደረገ መሆኑ ግልጽ ነው::

በሌላም በኩል መምህሩ በተደጋጋሚ ዳዊት የዘመረው በታቦቱ ፊት እንደ ሆነ አድርገው ነው ያቀረቡት:: ርግጥ ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት በተሸከሙ ካህናት ፊት ሲዘልና ሲዘፍን ቢታይም፥ እርሱ ግን ክብሩን ሁሉ ጥሎ እንዲያ የሆነው በእግዚአብሔር ፊት ነው::

- "ዳዊትም በሙሉ ኀይሉ <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> ይዘፍን ነበር" (ቍጥር 14)::
- "ንጉሡም ዳዊት፥ <u>በእግዚአብሔር ፊት</u>" ይዘልና ይዘፍን ነበር (ቍጥር 16)::
- "ዳዊትም ሜልኮልን፦ <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> ዘፍኛለሁ፤ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን:: ስለዚህም <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> እጫወታለሁ::" (ቍጥር 21)::

ዳዊት እንዲያ ሲዘልና ሲዘፍን የነበረው በእግዚአብሔር ፊት መሆኑ ተጽፎ ሳለ፥ መምህር ምሕረተ አብ ግን በታቦተ ጽዮን ፊት ነው እየዘለለ የዘመረው ማለታቸው ፍጹም ሐሰት ነው:: ዐላማቸው በኢትዮጵያ ታቦታት ፊት መዘመርን፣ መስገድንና እልል ማለትን ማጽደቅ ነውና፥ በዚህ ሁኔታ "ታቦታችን ከብሯል፤ ዳዊትን ሆነናል" ሲሉ አለማፈራቸው ብዙ አያስገርምም::

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ለጥፋታቸው ማጣመማቸውና ሰዎችን ማሳሳታቸው ሳያንስ (2ጴጥ. 3፥16)፥ የሌላውን ጩኸት በመቀማት፥ "ዐልፈውም ደግሞ ነቀፋ አላቆም ካሉ የእግዚአብሔር ቍጣ በእነርሱ ላይ ይገለጣል ይላል መጽሐፍ ቅዱስ" ማለታቸው መጽሐፍ ቅዱስን እንደማያውቁት አሳብቆባቸዋል:: ምክንያቱም፥ "ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን በትዕቢት ተነፍቶአል፤ አንዳችም አያውቅም" (1ጢሞ. 6፥3-4) ይላልና መጽሐፍ ቅዱስ:: ስለዚህ 'የኢትዮጵያ ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፤ በቃል ኪዳኑ ታቦት ስም ለኢትዮጵያ ታቦታት የሚደረገው አምልኮት ሁሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው' ብሎ መናገርና ማስተማር ሊያስቈጣ የሚችለው ሰይጣንን እንጂ እግዚአብሔርን ሊሆን አይችልም::





እስኪ መምህር ይጠየቁ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአንድ ጊዜ ተግባር ብቻ የሰጠውን የናሱን እባብ እስራኤል በሂደት እያጠኑለት በመገኘታቸው በእነርሱ ደስ ብሎታልን? ሕዝቅያስ "ነሑሽታን" ብሎ ሲሰባብረውስ ተቈጥቶታልን? ይልቁንም እግዚአብሔር ያላዘዘውንና እጁ ፈጽሞ የሌለባቸውን የኢትዮጵያን ታቦታት አስመልክቶ እየሆነ ባለው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል ብለው ያስባሉ? በፍጹም!!! ስለዚህ እግዚአብሔርን ሊያስቈጣው የሚችል ነገር እየተናገሩና እየሠሩ ያሉት እርስዎ ነዎትና፥ በሌላው ላይ ከመፍረድዎ በፊት ራስዎን ቢመረምሩ መልካም ነው::

ከሁሉም የሚገርመው የመምህር ምሕረተ አብ ገለጻ፥ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት የሆነውን ነገር አትሌቶቻችን አሸንፈው ሲገቡ በማማተብ ከሚያሳዩት ሁኔታ ጋር ማነጻጸራቸው ነው:: "አትሌቶቻችን አይታችኋል? አንዳንዴ ዳዊትን ይመስሉኛል" በማለት ሮጠው 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ ሲወጡ፥ ዓለም በቴሌቪዥን እየተከታተላቸው ባለበት ሰዓት በማማተብ ተዋሕዶ እምነታቸውን ለዓለም እንደሚሰብኩ ተናግረዋል፤ አድማጮቻቸውንም እልል አሰኝተዋል:: አክለውም እንዲህ ብለዋል፤ "በዚያ ቦታ ላይ ማድረግ ያለብን ሃይማኖታችንን መግለጥ ነው:: ታክሲ ውስጥ መዝሙር ከከፈትህ ሃይማኖትህን እየሰበክህ ነው:: አለባበስህ፣ አነጋገርህ፣ ሕይወትህ ሉቅ ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚገልጥ ሃይማኖታዊ ነገር ካደረግህ እምነታችንን እያንጸባረቅን ነው::"

መምህሩ፥ ዳዊትንና አትሌቶቻችንን እንዴት ማነጻጸር እንደ ቻሉ ግልጽ አይደለም:: ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ያዋረደውና በሚስቱ እስከ መናቅ የደረሰው ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ብሎ ነው:: አትሌቶቻችን የሚሮጡት ግን ዝናን ለማትረፍ፣ ለአገራቸው ክብርን ለማምጣትና ገንዘብን ለማግኘት ብለው ነው:: ስለዚህ ዳዊትና እነርሱ ለተለያየ ዐላማ ያከናወኑትን ተግባር ማነጻጸርና ማመሳሰል እንዴት ይቻላል? ማነጻጸሪያ ያደረጉት የእነርሱ ከድል በኋላ የማማተባቸው ጕዳይም፥ በምን ምክንያት እንደ ተደረገ መጤን አለበት:: በብዙ ስፖርታዊ ክንውኖችና በሌሎችም መሰል ተግባራት ላይ፥ በተለይ በወጣቱ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው የኅብረተ ሰብ ክፍል፥ እንደ ወረት (ፋሽን) የያዘውን ማማተብን፥ ከሃይማኖታዊ ጕዳይ ጋር ብቻ ማገናኘት የሚቻል አይደለም:: አትሌቶቻችንም ቢሆኑ መምህሩ እንዳሉት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውን ለዓለም ለመመስከር ብለው ሳይሆን፥ ድል ለሰጣቸው አምላክ ምስጋና ለማቅረብ ሊሆን ይችላልና

የሚያማትቡት፥ ነገሩን ሃይማኖትን ከመመስከር ጋር ማያያዝ የማይመስል ነገር ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሌሎችም ኦርቶዶክሳውያን ሃይማኖታቸውን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንዲመሰክሩ አስተምረዋል። ሆኖም ሃይማኖት ብለው ያቀረቡት በአብዛኛው ከባህል ጋር ግንኙነት ያለውን ነገር ሁሉ ነው። ለምሳሌ፦ በታክሲ ውስጥ መዝሙርን መክፈት ተጠቅሷል። ይህ ለብዙ ኦርቶዶክሳያውን መልካም ሊሆን ይችላል። ለሌሎች ደግሞ መብትን የመጋፋት ጉዳይ ተደርጎ መቈጠሩ አይቀርም። ቁም ነገሩ ያለው የታክሲ ሾፌሮች ኦርቶዶክሳዊነትን ማንጸባረቅ ያለባቸው በዚህ መንገድ ነው ወይ በሚለው ነጥብ ላይ ነው።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ብዙዎች የታክሲ ሾፌሮች የተባሉትን ይህን ነገር ሲፈጽሙ ይታያል። ለእነርሱ ኦርቶዶክሳዊነት ማለት እንደ ተሰበከላቸው በኦርቶዶክስ ዘማርያን የወጡ የመዝሙር ካሴቶችን በታክሲ ውስጥ መክፈት ነው። ነገር ግን በታክሲ ውስጥ በወገኖቻቸው ላይ የሚፈጽሟቸው በደሎችና ግፎች አሳዛኝ ናቸው። ለምሳሌ፦ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት፥ ወይም የታክሲ ተጠቃሚዎች ቍጥር በሚጨምርባቸውና የታክሲዎች ቍጥር በሚያንስባቸው ጊዜያት፥ ዐጭር መንገድ የሚጓዘውን ተጠቃሚ በረጅም መንገድ ሒሳብ ማስከፈል፣ ወይም መንገዱን በመቈራረጥ ትርፍ ለማጋበስ መሞከር፣ እንደዚያም ሆኖ በከፈለው ገንዘብ ዘና ብሎ እንዳይሄድ ከተፈቀደው ሰው በላይ ደራርቦ መጫን፣ በታክሲ ረዳቶች በኩል ገንዘብ ተቀብሎ መልስ አለ መስጠትና ማረሳሳት፣ ተሳፋሪውን ግማሽ መንገድ ላይ አድርሶ ማራገፍና በሌላ ታክሲ እንዲሄዱ በማድረግ የተጠቃሚዎችን ጊዜና ጕልበት ማባከን ጥቂቶቹ ናቸው።

ይህ ሁሉ እንግዲህ በዐመፅ ትርፍን ለማግኘት የሚደረግ ጥረት ነው። ይሁን እንጂ በግፍና በዐመፅ የሚሰበሰብ ገንዘብ ነውና ብዙዎች የታክሲ ሾፌሮችና ረዳቶቻቸው በሚያገኙት ገንዘብ ኑሮአቸውን ሲለውጡና በኑሮአቸው ሲባረኩ አይታይም። ስለዚህ መምህር፥ የታክሲ ሾፌሮችንና ረዳቶቻቸውን በታክሲ ውስጥ መዝሙር ከፈቱ ከማለት በላይ የሆነውን የጸና እምነትና የቀና ምግባር ሊያስተምሯቸው፥ መልካም ሥራቸውንም አይተው ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያከብሩት፥ እነርሱም በሥራቸውና በኑሯቸው እንዲባረኩ ሊረዷቸው ይገባል። አስቀድመው እርስዎ እውነቱን ከተረዱ ማለት ነው።





ስለዚህ መምህር፥ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተጻፈውን ቃል፥ ለኢትዮጵያ ታቦታት ሰጥተውና ጠቅሰው፥ "ዳዊትን ሆነን በመዘመራችን፥ በታቦቱ ፊት በመዝለላችን በታቦቱ ፊት እልል በማለታችን ከአባቶች ጋር የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘን ክብር በመስጠታችን ... እኛ አልተሳሳትንም" በማለትዎ ትልቅ ስሕተት ፈጽመዋልና ይታረሙ!!

## 3.7. ታቦታት የሚሰጧቸው ጥቅሞች አሉን?

**"እናንተ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ታቦት ምንም ጥቅም ስለሌለው ጥቅም የሌለውን ነገር ይዛችሁ በመገኘታችሁ ተሳስታችኋል የሚሉን ወገኖችን ይመለከታል። እኛ ግን ካህናት ከደብራቸው፥ ታቦታቱ ከመንበራቸው በመኖራቸው የምናገኘው ጥቅም ቋንቋ ሊገልጠው ከሚችለው በላይ እጅግ ብዙ ነው። የማይቻለው እንዲቻል፣ የማይሆነው እንዲሆን፣ የከበደው እንዲቀል፣ እንቆቅልሻችን እንዲፈታ የግድ ታቦት ያስፈልገናል ይላል የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ" ስለ ተባለው፤**

ይህ ˙መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌለውና የቤተ ክርስቲያናችንም ትምህርት ያልሆነ፥ መምህሩ ከልባቸው ያነቁት ፍጹም ኑፋቄና የእግዚአብሔርን ስፍራ ለኢትዮጵያ ታቦታት የሚሰጥ አምልኮ ባዕዳዊ ትምህርት ነው። መምህር፥ እስኪ "የማይቻለው እንዲቻል፣ የማይሆነው እንዲሆን፣ የከበደው እንዲቀል፣ እንቈቅልሻችን እንዲፈታ የግድ ታቦት ያስፈልገናል" የሚል ቀርቶ፥ ከዚህ ሐሳብዎ ጋር የሚቀራረብ ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያሳዩን? ፈጽሞ አያገኙም። ታዲያ፥ "ይላል የእግዚአብሔር ቃል፥ መጽሐፍ ቅዱስ" ሲሉ ለምን በሐሰት ተናገሩ? ይህ ሌላ ሳይሆን የሐሰት ምስክርነትዎን በ"መጽሐፍ ቅዱስ ይላል" ስም ሸፍነውና እውነተኛ አስመስለው ለማሳየት የሚያደርጉት ጥረት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበው ሁሉ ይረዳዋል።

የኢትዮጵያው ታቦት በኢኦተቤክ ውስጥ በየቤተ ክርስቲያኑ እንዲኖር ቢደረግም፥ የእግዚአብሔር ስፍራ ለታቦት የተሰጠበት ሰነድም ሆነ ትምህርት ግን ፈጽሞ የለም። እርስዎ ለታቦቱ የሰጡትን ተገቢ ያልሆነ ስፍራ ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ የምትሰጠው ለእግዚአብሔር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት "የማይቻለው እንዲቻል፣ የማይሆነው እንዲሆን፣ የከበደው እንዲቀል፣

እንቆቅልሻችን እንዲፈታ" የግድ የሚያስፈልገን እግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ ታቦት አይደለም።

መምህር፥ እርስዎ ከላይ ለተገለጸው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢኦርቶዶክሳዊ ትምህርትዎ ድጋፍ ብለው የጠቀሱት በኢያ. 3፥14-17 ያለውን ክፍል ነው። ክፍሉ ታቦቱን የተሸከሙ የአሪት ካህናት እግሮች ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠልቁ ከላይ የሚመጣው ውሃ መቆሙንና ሕዝቡ በደረቅ ምድር መሻገሩን ይናገራል። በዚህ ስፍራ ላይ ለተሠራው ተኣምራት ባለቤቱ እግዚአብሔር እንጂ የቃል ኪዳኑ ታቦት አይደለም። እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ ዋና ዐላማው የታቦቱን ሁሉን ቻይነት ማሳየት ሳይሆን የራሱን ክብርና ታላቅነት መግለጥ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡ ሁሉ ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ፥ በእስራኤል ነገዶች ቍጥር ልክ ከዮርዳኖስ ወንዝ ዐሥራ ሁለት ድንጋዮችን እንዲወስዱ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር (ኢያ. 4፥1-3)። በዚሁ መሠረት ስለ ወሰዷቸውና በጌልጌላ ስላቆሟቸው ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ምንነት የሚመጣው ትውልድ ቢጠይቃቸው እንዲህ ሲሉ እንዲመልሱ ተነገራቸው።

> እስራኤል ይህን ዮርዳኖስን በደረቅ ተሻገረ፤ እስከንሻገር ድረስ አምላካችሁ የኤርትራን ባሕር ከፊታችን እንዳደረቀ እንዲሁ እስከትሻገሩ ድረስ አምላካችሁ እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውሃ ከፊታችሁ አደረቀ። ይኸውም የእግዚአብሔር እጅ ጠንካራ እንደ ሆነች የምድር አሕዛብ ሁሉ እንዲያውቁ፥ አምላካችሁንም እግዚአብሔርን ለዘላለሙ እንድትፈሩ ነው። (ኢያ. 4፥22-24)።

ከዚህ ጥቅስ የሚከተሉትን ነጥቦች መጨበጥ ይቻላል፤

- ምንም እንኳ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት እግሮች ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲገቡ ውሃው ቢቆምና ሕዝቡ ሁሉ በደረቅ ምድር ቢሻገሩም፥ ይህን ተኣምራት ያደረገው ታቦቱ ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። ስለ ሆነም "እግዚአብሔር የዮርዳኖስን ውሃ ከፊታችሁ አደረቀ" (ቍጥር 23) ተብሏል።

- እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገውም፥ እጁ ጠንካራ እንደ ሆነች አሕዛብ ሁሉ እንዲያውቁ፥ እስራኤላውያንም አምላካቸውን እግዚአብሔርን ለዘላለም እንዲፈሩት ለማድረግ ነው እንጂ፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት ሁሉን አድራጊነት ለማስመስከር አይደለም።



አልተሳሳትንምን?

በዚህ ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር ለሚያደርገው ተኣምራት መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል። ይሁን እንጂ በራሱ ያደረገው አንዳች ነገር ስለሌለ፥ "ወንዙን ከፈለ፤ ውሃውን አቆመ፤ ሕዝቡን አሻገረ" ተብሎ ሊነገርለት የሚገባው፥ ብቻውን ተኣምራትን የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ነው (ኢዮ. 5፥9፤ መዝ. 72፥18)። መምህሩ ግን ታሪኩን በሙሉ ሳያነቡትና ጥቅሱንም በአግባቡ ጠቅሰው ሳይተረጒሙት፥ "መጽሐፍ ቅዱስ ይላል" ብለው ብቻ ቅዱስ ቃሉን እንደ ሽፋን በመጠቀም፥ የልባቸውን ሐሳብ የእግዚአብሔር ቃል አስመስለው አቅርበዋልና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ደባ ፈጽመዋል። ሰሚዎቻቸውንም ከቀናው መንገድ አስወጥተው ወደ ተሳሳተ ትምህርት ወሰደዋቸዋል።

ከላይ እንደ ተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱስ ዮርዳኖስን የከፈለውና ሕዝቡን በደረቅ መሬት ያሻገረው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራል። ይህን ያደረገውም በአሕዛብ እንዲታወቅ፥ በእስራኤልም እንዲፈራ ነው በማለት ምክንያቱን ጭምር ቃሉ ያስረዳል። እርሳቸው ግን፥ "እግራቸው [የካህናቱ] የዮርዳኖስን ውሃ ሲነካ ከታቦቱ ኀይል ወጣ ይላል። ኀይል ወጣና ገባር ወንዞች በያሉበት እንዲቆሙ ዮርዳኖስም እንዲደርቅ እንዲከፈል አደረገች ታቦተ ጽዮን" ሲሉ ያልተጻፈ አንብበዋል። ለመሆኑ ይህን ከየት አገኙት? አልተጻፈም እንጂ እግዚአብሔር ከቃል ኪዳኑ ታቦት ኀይልን ሊያወጣ ይችላል። ነገር ግን ያልተጻፈውን "ከታቦቱ ኀይል ወጣ" ብለው ለመናገር እንዴት ደፈሩ? እንዲህ ማለትዎ የኢትዮጵያ ታቦታት ኀይል ይወጣቸዋል ለሚለው ትምህርትዎ፥ መንገድ ጠራጊ አድርገው መላክዎ ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ ዮርዳኖስን ያደረቀው እግዚአብሔር ነው እያለ፥ ያደረቀችው ታቦተ ጽዮን ናት ለማለት ያነሣሣዎስ ምን ይሆን? ቃሉ እንደሚመሰክረው "ጽዮን" የሚለው ስም ኢያቡሳውያን የመሸጓትና በኋላ ላይ ዳዊት የያዛት፥ ከተማውም ያደረጋት አምባ ናት (2ሳሙ. 5፥6-10)። ከዚህ ጊዜ በፊት በእስራኤል ልጆች ይዞታ ሥር ስላልነበረችና የታወቀችው ከዳዊት ዘመን ወዲህ ስለ ሆነ፥ በኢያሱ ዘመን ውስጥ ሆኖ "ጽዮን" በሚለው ዘርፍ (ታቦተ ጽዮን ብሎ) የእግዚአብሔርን ታቦት መጥራት አላዋቂነት ነው። እነዚህ ሁሉ የተሳሳቱ መረጃዎች ናቸው።

መምህር፥ የእግዚአብሔር ቃል የማይለውን ይላል ብለው፥ ወደ የት ለመሄድ እንደ ፈለጉ ግልጽ ነው። የሄዱበት መንገድ የኢትዮጵያ ታቦታት ተአምራትን ይሠራሉ ወደሚለው ሰፈር ነው ያደረሰዎ። ለዚህም በዐድዋ ጦርነት ላይ አባቶቻችን "የጊዮርጊስን ታቦት ይዘው ዐድዋ ድረስ ዘምተው፤ ጊዮርጊስ ታቦቱ ስለ እኛ ተዋግቶ ሉዓላዊነታችንንና ነጻነታችንን ዐውጆ፣ ነጮችን በሠለጠነ ዘመናዊ መሣሪያ ቢመጡ አሳፍሮ መልሶልን ነጻ እንድንሆን አድርጎናል" ብለዋል።

ነገር ግን ይህን ያውቁ ኖሯል? ከዐድዋ ድል በኋላ ጣሊያን ራሷን አጠናክራና በዘመናዊ ጦር ተደራጅታ ኢትዮጵያን ዳግም በወረረች ጊዜ፥ አባቶቻችን ታቦት ይዘው ነበር ወደ ማይ ጨው የዘመቱት። ነገር ግን ድል አላገኙም። ይህም ሁኔታ ከዚያ በኋላ አነጋጋሪ ሆኖ፥ "በማይ ጨው ዘመቻ ጊዜ ተአምራትን እንዲያደርግ ያዘመታችሁት ታቦት ምን አደረገላችሁ" የሚል ትውልድ ተነሥቶ ነበር።[72] ለተነሣው ጥያቄ ከቤተ ክህነት በኩል የተሰጠው ምላሽ፥ ታቦታችን ተአምር መሥራት አቅቶት ሳይሆን ኀጢአታችን ያመጣብን ጣጣ ነው የሚል ነበር። በዐድዋውም ሆነ በማይጨዉ ጦርነት ጊዜ እኛ ተወረርን እንጂ አልወረርንም። በሁለቱም ጊዜ ራሳችንን ለመከላከልና ወራሪውን ጠላት ለማባረር አባቶቻችን ጦርነት ገጥመው በመጀመሪያው አሸነፉ። በኋለኛው ግን ለጊዜውም ቢሆን ተሸነፉ። ስለዚህ በዐድዋው ጦርነት ላይ ያሸነፉት ኀጢአት ሳይሠሩ ታቦት ይዘው ስለ ዘመቱ ነው ብሎ መናገር የሚቻል አይመስልም። በማይ ጨዉ ጊዜ ደግሞ የተሸነፉት ታቦት ይዘው ቢዘምቱም በኀጢአታቸው ምክንያት ረድኤት ስላላገኙ ነው ሊባል የሚችልበት አንድም ምክንያት አይኖርም። ምናልባት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና እርሱ ሳያውቀው የሚሆን አንዳች ነገር የለምና፥ እርሱ የሰጣቸውን የዐድዋውን ድል ለጊዮርጊስ አሳልፈው በመስጠታቸው ነው ቢባል ሊያስኬድ ይችል እንደ ሆነ አይታወቅም።

በብሉይ ኪዳን ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ የነበረ ቢሆንም፥ ልብን ከእግዚአብሔር ላይ አንሥቶ በታቦቱ ላይ ማሳረፍ ለሽንፈት እንጂ ለድል ሲያበቃ አልታየም። በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በዔሊ ዘመን የሆነውም ይኸው ነው። የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ እግዚአብሔርን ማስቈጣታቸው ሳያንስ፥ ወደ ጦርነት እግዚአብሔርን ጥለው ታቦቱን ግን

[72] መርሐ ምእመናን (1946፣ 51)።





ይዘው በዘመቱ ጊዜ ድል ተመቱ፤ አፍኒንና ፊንሐስ ሞቱ፤ ታቦቱም በፍልስጥኤማውያን ተማረከ (1ሳሙ. 2፥12-17፤ 4፥1-22)።

በአገራችን ታቦታት ተሠራ ብለው የጠቀሷቸውን የ2001 ዓ.ም. የበዓለ ጥምቀትን "ተአምራት" እናንሣ። አንደኛው ተአምር፥ ሁሉ አንድ ልብ ሆኖ ታቦታትን እያከበረ ስለ ሄደ ታቦታቱ ጥምቀተ ባሕር ሲደርሱ በሁሉም ሰፍራ ዝናቡን እንደ ጠበል አርከፈከፈው። "በበነጋውም ሰው በሙቀት እንዳይደከም፥ ሚካኤል በደመና እየጋረደ፥ ታቦታቱን ሕዝቡ አጅቦ ወደ መንበረ ክብራቸው እስኪገቡ ድረስ ደመና አደረገው፤ የማይቻለው ተቻለ፤ በበጋ ዝናብ ዘነበ።" ይህ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የመዝነቡ ጉዳይ ተአምር መባሉ፥ "ሥጋ ቈጠር ቢሉት ጣፊያን አንድ አለ" የሚለውን ተረት ያስታውሳል። መምህር፥ እስኪ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይስጡ! በሌላ ዝናብ ባልዘነበባቸው የጥምቀት በዓላት ፀሐይ ወጥቶ ሕዝቡ ለምን ሲቃጠል ዋለ? አምና ተአምር ሠሩ የተባሉት ታቦታት የት ሄደው ነበር? እርስዎ ተአምር ያሉትን እኮ ሌላው፥ በተለይም በወቅቱ አዝመራውን ሰብስቦ ያላስገባው ዐርሶ አደርና እህል ሸማቹ ከተሜ፥ ያለ ወቅቱ ሲዘንብ እንደ ተአምር ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቍጣ ተመልክቶ "እግዚኦ!" ሊል እንደሚችል መዘንጋት የለብዎትም። ስለዚህ ምናልባት ነገሩ በተአምር ጎራ የሚመደብ ሳይሆን፥ ከአየር መዛባት ችግር ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ቢዘንብም እንኳ ዝናቡን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሚካኤል አይደለም።

ሌላው ተአምርዎ ደግሞ በየካ ሚካኤል የቃና ዘገሊላ በዓል ላይ ታየ ያሉት ነው። በጊዜው በበዓሉ ላይ ወጣቶች ከለቀቋቸው ርግቦች መካከል፥ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ያደረጓት አንዷ ነጭ ርግብ ተነጥላ በመቅረትና ሌሎቹን ርግቦች ተሳስታችኋል፥ እኔ ግን ታቦቱን ሳላስገባ አልሄድም ብላ በዚያ መቅረቷንና ማረፊያ ያደረገችውም ታቦቱን መሆኑን ተናግረዋል። መምህር፥ በአገላለጽዎ ርግቧ ሁሉን ነገር ያጫወተችዎ ነው የሚመስለው። ይህን ተረትዎን ለዐዋቂዎች ሳይሆን ለሕፃናት ቢነግሯቸው ሳይመጥናቸው አይቀርም። መቼም ይህ እርስዎ የፈጠሩት ተረት እንጂ በእውን የተፈጸመ ተአምር እንዳልሆነ፥ በቪሲዲዎ የሚታየውን ምስል ከንግግርዎ ጋር አለ መግጠሙን በማነጻጸር እንኳ ማረጋገጥ ይቻላል። ሌላ ሌላውን እንቶ-ፈንቶ ነገር ሁሉ ትተን፥

- ነጭና ጥቁር የሆነችውን ርግብ፥ "ነጭ ርግብ" ማለትዎ፥

- ፈጽሞ ሊባል የማይገባውን ርግቧን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናት ማለትዎ፥[73]
- በቪሲዲው ላይ እንደሚታየውም ርግቧ ያረፈችው ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በተዘረጋው ጃንጥላ ላይ መሆኑ በግልጽ እየታየ፥ እርስዎ ግን በቅዱስ ሚካኤል ታቦት ላይ ነው ያረፈችው ማለትዎ ነገሩ ተረት እንጂ ተኣምር አለ መሆኑን ያስረዳል።

ይህች በስሟ ተረት የፈጠሩላት ርግብ "መጥታ በታቦቱ ላይ ዐርፋ አለ መሳሳታችንን ስለ ገለጸችልን አልተሳሳትንም" ብለዋል። እውነትም አልተሳሳቱም!

በመጨረሻም፥ "ረኃባችን በጥጋብ፣ ማጣታችን በማግኘት፣ ችግራችን ሁሉ በረድኤት እንዲቀየር ሁላችን ለታቦት ክብር እንስጥ። ይኼ ነው ትልቁ ነገር" ብለዋል። ርግጥ ነው እርስዎ ባይጠቅሱትም፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ አቢዳራ ቤት ገብቶ ለሦስት ወራት በተቀመጠ ጊዜ፥ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ሲል እግዚአብሔር አቢዳራንና ቤቱን ባርኮለት ነበር (2ሳሙ. 6፥11-12)። ልብ ይበሉ መምህር፥ የባረከው ታቦቱ ሳይሆን ስለ ታቦቱ ብሎ እግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም፥ "ፍጹም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ፥ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌሉ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ. 1፥17) ተብሎ ተጽፏል።

ዛሬም ቢሆን ከእግዚአብሔር በቀር (ታቦትም ቢሆን) ሕዝቡን ሊባርከና በበረከቱ ሊያትረፈርፍ የሚችል አንዳችም ነገር የለም። በብሉይ ኪዳን አቢዳራን ወደ ቤቱ በገባው በቃል ኪዳኑ ታቦት ምክንያት የባረከው እግዚአብሔር፥ በሐዲስ ኪዳን ሕዝቡን የባረከውና የሚባርከው ለዚሁ ዐላማ በላከው (የሐዋ. 3፥26) በአማናዊው ታቦት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌ. 1፥3)።

እንዲህ አይደለም! እግዚአብሔር ይባርከን ዘንድ ታቦት የግድ ያስፈልገናል ካሉ ግን፥ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ታቦታት ሞልተውን ምነው ታዲያ "ረኃባችን በጥጋብ፣ ማጣታችን በማግኘት፣ ችግራችን ሁሉ

[73] ጌታ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ መውረዱ ተጽፏል (ማቴ. 3፥16)፤ ርግብ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ግን ፍጹም ኑፋቄ ነው።





በረድኤት" አልቀየር አለ? በተቃራኒው ታሪካችን የረኃብ፣ የበሽታ፣ የድኽነት፣ ለምን ሆነ? ታቦታቱን የሚያከብር ጠፍቶ ነው እንዳይሉ፥ ብዙዎች ዘወትር ይሰግዱላቸው፣ ይዘምሩላቸውና እልል ይሉላቸው የለምን? ነገር ግን በረከትና ረድኤት ለምን ጠፉ?

እውነቱ ይህ ነው። ዳዊት የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ አቢዳራ ሲያገባው (2ሳሙ. 6፥10)፥ አቢዳራ ፈቃደኛ ነበር እንጂ አይገባም ብሎ አልተቃወመም። ስለዚህ በቤቱ የእግዚአብሔር በረከት ገባ። እኛስ እግዚአብሔር እንዲባርከን የላከውን አማናዊ ታቦት፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ተቀብለነውና የልባችንን በር ከፍተንለት መቅደሱ ወደ ሆነው ሕይወታችን እንዲገባ፥ በእኛ ውስጥ እንዲኖር በትክክል ፈቅደንለታል? የብዙዎቻችን ልብ የተከፈተው ለሌሎች እንጂ ለጌታ እንዳይደለ ግልጽ ነው። ታዲያ በየት በኩል ይባርከን? መምህር የበረከቱን መገኛ መንገድ ስተዋል። ሕዝቡንም ወደ ባሰ ርግማን እየመሩት እንደ ሆነ ልብ ይበሉ። ስለዚህ ወደ በረከቱ ምንጭ ወደ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለሱ ይመከራሉ።

## 3.8. ለታቦት ይሰገዳልን?

**"ለታቦት ስንሰግድ ግንባራችንን መሬት አስነክተን ስንታይ 'ተሳስታችኋል፤ ለታቦት ስግደት አይገባም' ለሚሉ ወገኖችም ቅዱስ ከሆነው የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሐሳብ ይዞ ወደሚገኘው መረጃችን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መሄድ ግድ ይለናል።"**

በዚህ ክፍል ደግሞ ለታቦት ስግደት ይገባል የሚል ትምህርት ቀርቧል። ስግደት የሚቀርበው ለአምላክ ብቻ እንደ ሆነና ከእርሱ በቀር ለማንም፥ ለምንም መስገድ የተከለከለ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በአጽንዖት ይናገራል። የቃል ኪዳኑ ታቦት በውስጡ የያዛቸው ሁለቱ ጽላት ካሰፈሯቸው ዐሥር ቃላት ውስጥ፥ "በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውም" የሚለውም ዋናው ትእዛዝ ነው (ዘፀ. 20፥4-5)። ጽላቱ ላይ እንዲህ ተጽፎ እያለ ለታቦት ይሰገድ ማለት፥ እርስ በርሱ የሚጣረስ ነው።

ምናልባት ይህ ትእዛዝ የተቀረጹ ጣዖታትን ማምለክና ለእነርሱ መስገድ የተከለከለ መሆኑን ለመግለጽ የተጻፈ ነውና ታቦትን አይወክልም ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለቃል ኪዳኑ ታቦት በተለይ ስግደት እንዲቀርብ የታዘዘበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም፡፡ ለቃል ኪዳኑ ታቦት የሰገደ ወገንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈጽሞ አይገኝም፡፡ ስግዶ ቢገኝ ኖሮ እንኳ ይወቀሥ ነበር እንጂ አይመሰገንም፡፡ ታዲያ መምህር ምሕረተ አብ "መረጃችን" ብለው የጠቀሱት ከየትኛው መጽሐፍ ቅዱስ ይሆን?

ማስረጃ ይሆነኛል ብለው የጠቀሱት ኢያ. 7፥6 ላይ ያለውንና "ኢያሱም ልብሱን ቀደደ፥ እርሱና የእስራኤልም ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ" የሚለውን ጥቅስ ነው፡፡ "በግምባራቸው ተደፉ" ተብሎ የተጻፈውን፥ "ግንባራቸውን መሬት አስነክተው ሰገዱ ይላል" ብለው ነው ያነበቡት፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን እንዲህ አላለም፡፡ ግእዙም፥ "ወሠጠጠ አልባሲሁ" ኢያሱ ወወድቀ በገጹ ውስተ ምድር ቅድመ ታቦቱ ለእግዚአብሔር እስከ ሠርከ"[74] ነው የሚለው፡፡ ጥቅሱ በግንባራቸው መደፋታቸውን እንጂ መስገዳቸውን አያመለክትም፡፡ ያም ቢሆን ምሕረት ለመለመን እንጂ ለታቦት ለመስገድ ፈልገው ያደረጉት አይደለም፡፡ ታዲያ ከየት አምጥተው ነው "ሰገዱ ይላል" ያሉት? ምናልባት ሕዝቡ እኛ ያነበብንለትን ብቻ ይቀበላል እንጂ፥ የሰጠነውን ጥቅስ ከቤቱ ገብቶ እያነበበ አያረጋግጥም ብለው ይሆናል፥ እንደ ተጻፈው ሳይሆን እንደ ፈለጉት ያነበቡት፡፡

እዚህ ላይ "ተደፉ" የሚለው "ሰገዱ" ሊሆን አይችልም ወይ? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል፡፡ ይህ ግን እነ ኢያሱ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ለምን በግምባራቸው መደፋት አስፈለጋቸው? ዐላማቸው ለታቦቱ መስገድ ነበር? ወይስ ሌላ? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ይቀሰቅሳል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስም ቢያንስ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ምዕራፍ ሰባትን ከቍጥር አንድ ጀምሮ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡

ቀደም ብሎ እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች የኢያሪኮ ቅጥር ከፈረሰላቸው በኋላ ሊያደርጓቸው ስለሚገቡ ነገሮች መመሪያ ሲሰጥ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ "እናንተ ግን እርም ካደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ፤ እርም ከሆነው አንዳች የወሰዳችሁ እንደ

[74] ብሉይ ኪዳን (1955፣ 356)፡፡





ሆነ የእስራኤልን ሰፈር የተረገመ ታደርጉታላችሁ፥ ታስጨንቁታላችሁ" (ኢያ. 6፥19)፡፡ "እስራኤልም እርም በሆነው ነገር በደሉ፤ ... የእግዚአብሔርም ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ" (ኢያ. 7፥1)፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ በጋይ ሰዎች ላይ ሲዘምቱ ድል በማድረግ ፈንታ ድል ሆኑ፡፡ "የሕዝቡም ልብ ቀለጠ፥ እንደ ውሃም ሆነ" (ቍጥር 5)፡፡ ኢያሱ ልብሱን ቀዶ ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር በመሆን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በግንባራቸው ተደፍተው የዋሉት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የመሆኑ ምልክት ነውና፥ በፊቱ በግንባራቸው የተደፉት ንስሓ ለመግባትና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ጤናማ ግንኙነት ለመመለስ እንጂ በቀጥታ ለታቦቱ ለመስገድ አይደለም፡፡ ቃሉም በታቦቱ ፊት እንጂ ለታቦቱ ተደፉ አይልም፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፥ መምህር ምሕረተ አብ ለቃል ኪዳኑ ታቦት ያልሰገደውን ኢያሱን በሐሰት 'ሰገደ፤ በመስገዱም አልተሳሳተም፤ እኛም የእርሱን አርአያ ተከትለን በመስገዳችን አልተሳሳትንም' ይላሉ፡፡ "ኢያሱ ሰግዷል" የሚለው ውሸታቸው እንዲይዝላቸውም፥ ከሕዝቡ ጋር የተመላለሱትን ልቦለዳዊ ምልልስ ቀጥሎ እንመልከት፡፡
"ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆነ ኢያሱ፥ በገባዖን ፀሓይን ያቆመ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ ያሻገረ፣ ቅጽር እፍርሶ ርስት ያወረሰ፣ ከሙሴ ቀጥሎ እስራኤልን ወደ ተሰፋዪቱ ምድር የመራ ኢያሱ በታቦቱ ፊት ምን አለ [አደረገ]?"
"ሰገደ፡፡"
"ምን አለ?"
"ሰገደ፡፡"
"እኛም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ለእግዚአብሔር በጣም ቅርብ የሆነ ኢያሱ እንደ ሰገደ በመስገዳችን ምን አላልንም?"
"አልተሳሳትንም!"
"ምን አላልንም?"
"አልተሳሳትንም!"
"አይሰማም!"
"አልተሳሳትንም!"
"ስለዚህ ማንም ተሳስተሃል ቢልህ ኢያሱን ጠይቀው፤ ኢያሱ ተሳስቷል እያልከኝ ነው ወይ በለው፡፡ ኢያሱ ተሳስቷል የምንል ደግሞ እኛ ማነን? እነርሱስ ማናቸው? ኢያሱም አልተሳሳተ፤ ኢያሱን የመሰልን እኛም አልተሳሳትንም፡፡"

"ኢያሱን መሰላቸኋል፤ ትክክል አይደላችሁም ያሉን እነርሱ ግን"
"ተሳስተዋል"
"እኛ ግን"
"አልተሳሳትንም"

በዚህ ምልልስ ውስጥ ሊስተዋሉ የሚገባቸው አንዳንድ መሠረታውያን ነጥቦች አሉ፡፡ በመጀመሪያው ላይ እንደ ተገለጸው ኢያሱ ታላቅ የእስራኤል መሪ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው እርሱና የእስራኤል ሽማግሌዎች እርም በሆነው ነገር በተፈጸመው በደል ምክንያት፥ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ለመግባት "በእግዚአብሔር ታቦት ፊት እስከ ማታ ድረስ በግምባራቸው ተደፉ፤ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነሰነሱ" ይላል እንጂ ለቃል ኪዳኑ ታቦት ሰገዱ አይልም፡፡ ስለዚህ ያልተጻፈውን፥ "ኢያሱ ለቃል ኪዳኑ ታቦት ሰገደ" በማለት የተሳሳተ ሐሳብ አስቀምጦ፥ በዚህ የተሳሳተ ሐሳብ መሠረት ለኢትዮጵያ ታቦታት የሚሰግዱ ትክክለኞች፥ የማይሰግዱ ደግሞ ስሕተተኞች ናቸው ማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ኢያሱ ለእግዚአብሔር ታቦት አልሰገደም እንጂ፥ ቢሰግድ ኖሮ እርሱ ሰግዷል ተብሎ አርአያነቱን መከተል ባልተቻለም ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢያሱ ታላቅ መሪና የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም ፍጹምና የማይሳሳት ሰው ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ስለዚህ ከእርሱ በጎ የሆነውን ነገር ተምሮ አርአያነቱን መከተል ይገባል፡፡ ጥሩ ያልሆነ ነገር አድርጎ ከተገኘ ግን፥ የእርሱን ስሕተት ላለመድገም ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ፦ ከተጻፈው በመነሣት ኢያሱ በገባዖን ሰዎች ተታሏል (ኢያ. 9፥1-27)፡፡ ይህም ሰው በመሆኑ የፈጸመው ስሕተት ነው፡፡ ታዲያ፥ "ለእግዚአብሔር ቅርብ የሆነ ኢያሱ፥ በገባዖን ፀሐይን ያቆመ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ ያሻገረ፣ ቅጽር አፍርሶ ርስት ያወረሰ፣ ከሙሴ ቀጥሎ እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር የመራ ኢያሱ" በገባዖን ሰዎች ተታሏልና፥ እኛም አርአያውን ተከትለንና መታለልን እንደ ጽድቅ ቈጥረን ተላላ ልንሆን ነው ማለት ነው?

መምህር፥ ኢያሱ ለታቦት ሳይሰግድ ሰግዷል በሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነውን ትምህርት እውነተኛ አስመስለው ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ በማስከተልም ለኢትዮጵያ ታቦታት መስገድ ኢያሱን መምሰል ነው ሲሉ፥ የታላቁን መስፍን የኢያሱን ስም አጥፍተዋል፡፡ ስለዚህ እርሱ





ያላደረገውን፥ ለታቦት በመስገድ ኢያሱን እንምሰለው በማለትዎ ፍጹም ተሳስተዋልና መሳሳትዎን ይመኑ፡፡

## 3.9. ታቦት ለምን ይሰረቃል?

"ብዙ ጊዜ መናፍቃን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ለማስኰብለል ከሚጠቀሙባቸው ነገሮች መካከል አንዱና ዋነኛው፥ 'የሚካኤል፣ የገብርኤል፣ የማርያምና የመድኀኔ ዓለም ታቦት ጠፋ፤ ተሰረቀ ይባላል፡፡ ታዲያ በሌቦች የሚሰረቅና የሚጠፋ፥ ራሱን እንኳ መከላከል የማይችል ጽላት እንዴት ይዛችሁ ትከተላላችሁ? ተሳስታችኋል እኮ' ይሉናል፡፡ ለዚህ ትችት ዐዘል ጥያቄ መልሳችን ምን ይሆን?"

ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት በቃልም በጽሑፍም የሚተላለፉ ትምህርቶች፥ ብዙ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት ከተጻፈውና ከሚታመነው ትምህርት ጋር ልዩነቶች አሏቸው፡፡ በኢትዮጵያ ታቦታት ላይ ከሚታዩትና ከሚሰሙት ነገሮች መካከል አንዱ ታቦታቱ የመሰረቃቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ አልታየም፤ አልተሰማም፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ታቦታት የመሰረቃቸውን ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስደግፎ ማቅረብ የማይቻል ቢሆንም፥ መምህር ምሕረተ አብ ግን ታቦት ሊሰረቅ እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አለኝ ይላሉ፡፡

ክርክራቸውን ሲጀምሩም፥

> ለምን ታቦት ይጠፋል? ለምን ታቦት ይሰረቃል? ... የሚሰረቅ ራሱን መጠበቅ የማይችል፥ መለኮታዊነቱ የሚያጠራጥር ነገር ነወይ የያዛችሁት? ይሉናል እ..ህ.. አይ አለማስተዋል፤ አይ አለማወቅ፤ እንዲህ ነው የሚለው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ታቦት እንደማይጠፋ፥ ታቦት እንደማይሰረቅ ሲናገር፤ በመጀመሪያ ማወቅ ያለብን ነገር አለ፡፡ በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 4 ላይ ታቦት የሚሰረቅበትን ምክንያት ሲናገር እንዲህ ይላል፡፡

ብለው፥ በዘመነ መሳፍንት የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በፈጸሙት ኀጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር ታቦት መማረኩን ይጠቅሳሉ፡፡ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በሚፈጸሙ ኀጢአቶች ምክንያት የኢትዮጵያ ታቦታት ሊሰረቁ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ "ተማረከ" የሚለውን "ተሰረቀ" ብለው ተርጉመዉታል ማለት ነው፡፡

መምህሩ በሥላቅ መልክ "አይ አለማስተዋል፥ አይ አለማወቅ፥" በሚል ራሳቸውን አስተዋይና ዐዋቂ፥ ሌላውን የማያስተውልና የማያውቅ አድርገው ሲያቀርቡ፥ ታቦት እንደማይሰረቅና እንደማይጠፋ ማስረጃ ይሆነኛል ብለውም ፲ሳሙ. 4ን ጠቅሰዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ሲሠራበት ባይታይም፥ አንዳንድ ጊዜ ሌላውን ስሕተተኛ፥ ራስን ግን ትክክለኛ አስመስሎ ለማቅረብ የሚጠቀስ አንድ መርሕ አለ፤ እንዲህ የሚል፥ "እንብብዋ ለመልእክት እምጥንታ እስከ ተፍጻሜታ - መልእክቷን ከመጀመሪያዋ እስከ መጨረሻዋ አንብቧት፡፡"[75] መርሑ የአንድን መጽሐፍ ሐሳብ በትክክል ለመረዳት ቈንጽሎ መውሰድ ሳይሆን፥ መጽሐፉን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ማንበብ እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ እስካሁን ለማሳየት እንደ ተሞከረው፥ መምህር ምሕረተ አብ ይህን መርሕ የሚያውቁት አይመስልም፡፡ በዚህ መርሕ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን ስለማያነቡትም፥ ቃሉን የሚተረጉሙት በተጻፈበት ዐውድ መሠረት ሳይሆን፥ ለእርሳቸው በሚስማማቸውና ከቃሉ ውጪ ያመጡትን ዐዲስ ሐሳብ እንዲደግፍላቸው አድርገው ነው፡፡ እውን ፲ሳሙ. 4 እርሳቸው እንዳሉት ታቦት የሚሰረቅበትን ምክንያት ነው የሚናገረው?

በተጠቀሰው ምዕራፍ ውስጥም ሆነ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት መሰረቅ የተጻፈ አንዳች ነገር አይገኝም፡፡ ካሁን በፊት ለማንሣት እንደ ተሞከረው በ፲ሳሙ. 4 የተጻፈው ታሪክ፥ በዔሊ ዘመን የእስራኤል ልጆች ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ገጥመው ድል በተመቱ ጊዜ፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘው እንደ ገና ለጦርነት መሰልፋቸውን ነው የሚናገረው፡፡ በዚህም ጦርነት ላይ ሠላሳ ሺህ እስራኤላውያን ዐለቁ፤ የተረፉትም ሸሹ፡፡ ታቦቱ ተማረከ፡፡ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስም ሞቱ፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የቃል ኪዳኑ ታቦት በጦርነት ላይ በይፋ ተማርኮ መወሰዱን እንጂ፥ በኢትዮጵያ ታቦታት እንደሚደረገው በድብቅ መሰረቁን አይደለም፡፡

ሌላው የመምህር ምሕረተ አብ የተሳሳተ መነሻ ሐሳብ፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት ኀጢአት ስለ በዛ በእስራኤል መካከል ላለመቀመጥ ወስኖ፥ በራሱ ተነሣሽነትና ፍላጎት በፍስጥኤማውያን እጅ እንደ ገባ ተደርጎ የተነገረው ነው፤ እንዲህ በማለት፥ "ከዚያ ታቦቷ እንዴት ብላ ትቀመጥ? ታቦተ ጽዮን፥ በቃ ልሰደድ አለች፡፡ ከእነዚህ ጋር ከምኖር ልሰደድ፤ ዐውቃ

[75] ሃይማኖተ አበው (1986፤ 457)፡፡





በፍልስጥኤማውያን፣ በማያምኑ፣ ሃይማኖት በሌላቸው ሰዎች ተማርካ ውሰዱኝ ብላ ሄደች፡፡ ሰው የለማ እዚህ፡፡ ከአሕዛብ ያልተሻለ ሰው እዚህ ስለ በዛ ሄደች፡፡"

ርግጥ ነው፤ የዔሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ብዙ ኀጢአትና ግፍ ሲፈጽሙ ነበር (፲ሳሙ. 2፥12-25)፡፡ እነርሱ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ፥ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ገጥመው ተሸነፉ፡፡ "የእስራኤል ሽማግሌዎችም፡- ዛሬ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለ ምን መታን? በመካከላችን እንዲሄድ ከጠላቶቻችንም እጅ እንዲያድነን፥ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እናምጣ አሉ" (፲ሳሙ. 4፥3)፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህሩ እንዳሉት ታቦቱ በራሱ ፈቃድ እንደ ሄደ ሳይሆን፥ የእስራኤል ልጆች ያጡትን ድል በታቦቱ አማካይነት መልሰው ለማግኘት በማሰብ ይዘዉት እንደ ሄዱ ነው፡፡ ድል የሚገኘው ግን በታቦቱ መኖርና አለመኖር ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶ በመኖርና ባለ መኖር ነው፡፡ በመሆኑም አፍኒንና ፊንሐስ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ፈጸሙት ኀጢአት ንስሓ ሳይገቡና ሕይወታቸውን ሳያስተካከሉ፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዘው ቢዘምቱም የእስራኤል ልጆች ዳግም ተሸነፉ፡፡ ታቦቱንም አስማረኩ፡፡ እነርሱም ሞቱ፡፡ እውነቱ ይህ ነው እንጂ መምህሩ እንዳሉት፥ የቃል ኪዳኑ ታቦት፥ "የሚያከብረኝ የለም" ውሰዱኝ ብሎ የሄደበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም፡፡

የቃል ኪዳኑ ታቦት ካላይ በተገለጸው ምክንያት ተማረከ፡፡ የኢትዮጵያ ታቦታት የሚሰረቁበት ምክንያቱ ግን ምን ይሆን? መምህሩ ግን ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በተሳሳተ አተረጓጐም ላይ ተመሥርተው የተናገሩትን ለኢትዮጵያ ታቦታት ከመስጠት ወደ ኋላ አላሉም፡፡ "አንድ ማወቅ ያለብን ታቦት፥ ውስጥ ባለነው ሰዎች ችግር ይሰደዳል፤ ካልተመቸነው ግድ ነው፤ ይሄዳል" ያሉትም ይህንኑ የሚጠቍም ነው፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ታቦታት ስርቆት ካልሆነ በቀር ስደትና ምርኮ ብዙም አልገጠማቸውም፡፡ የሚሰረቁትም በውስጥ ዐዋቂዎች እንደ ሆነ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ ጕዳዩን መንፈሳዊ ቅብ ቀብቶ ማቅረቡ ለጊዜው ለማሳሳት ካልሆነ በቀር ብዙ አያሳምንም፡፡

እርሳቸው ባሉት መንገድ ነገሩን እንረዳው ቢባል እንኳ፥ የኢትዮጵያ ታቦታት የሚሰረቁት በኀጢአት ብዛት ነው ማለት አይቻልም፡፡ እንዲህ ሲባል ግን ኀጢአት አልበዛም ማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የኀጢአት

መብዛት ታቦታቱን አሰረቃቸው ለማለት የሚያስችል ምንም መነሻ ምክንያት የለም ለማለት ነው:: በአንጻሩ ያልተሰረቁትንም ታቦታት በመንበራቸው እንዲቆዩ ያደረገው የጥበቃ መጠናከር እንጂ የኀጢአት እለ መብዛት አይደለም::

መምህር ምሕረተ አብ፥

> ታቦት መጀመሪያ ይሄዳል:: ከዚያ ቀጥሎ ምን ይሆናል? የሚሆነው ነገርማ፥ በአንደኛ ሳሙኤል ምዕራፍ ፀምስት ላይ ከቍጥር አንድ ስትመለከቱ ታቦት ይሄድና ሥራ ይሠራል:: መጀመሪያ ሲሰደድ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ያጸዳል:: ... ውስጥ ያለን ሰዎች ካልተመቸነው ያጸዳናል:: ሳይመቹት ሲቀሩ መጀመሪያ ታቦቷ ሄደች:: ከዚያ ቀጣዩ ርምጃ አፍኒን ፊንሓስ አባታቸው ዔሊ ተገዱ፤ ጸዱ:: የማይመቹት ሲጸዱ ታቦተ ጽዮን መጽዳቱን አረጋገጠች:: እና መመለስ አለብኝ ልትል ነዋ!

ብለው፥ በእግዚአብሔር ታቦት ምክንያት በፍልስጥኤማውን ዘንድ የሆነውን መቅሠፍትና በዔሊና በልጆቹ ላይ የደረሰውን ሞት በመጥቀስ፥ ታቦት ቢማረክም የሚሠራው ሥራ አለ ይላሉ:: ሁኔታው እንዲህ ባይሆንም ይሁን ብለን እንቀበል:: በኢትዮጵያ ታቦታት ላይ ግን ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው እንዴት ነው?

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ታቦታት መጀመሪያውኑ ከጥበቃ መላላት የተነሣ እንጂ በኀጢአት ምክንያት የሚሰረቁ አለ መሆናቸው ግልጽ ነው:: ከተሰረቁ በኋላም ፖሊስ በሚያደርገው ጠንካራ ምርመራና ክትትል፥ ብዙዎቹ ታቦታት በቍጥጥር ሥር እንደሚውሉ ዘወትር በየዜና ማሠራጫው የምንሰማው እውነት ነው:: ታቦታቱን የሰረቁት ወገኖችም ክስ ተመሥርቶባቸው ለፍርድ ይቀርባሉ እንጂ ሌላ መቅሠፍት ሲወርድባቸው አይታይም:: ርግጥ ይህም ቢሆን የሌብነታቸው ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው:: ከዚህ ውጪ የተሰረቁት ታቦታት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ መምህሩ የዘረዘሯቸውን:- ዝርፊያን፣ ጥንቆላን፣ ሟርትን፣ ድግምትንና ሌሎችንም ኀጢአቶችና ርኩሰቶች የሚሠሩትን ሲያጸዱ አይታይም:: ታቦታቱ ወደየመንበራቸው የሚመለሱትም በፖሊስ ጠንካራ ክትትልና ሥራ እንጂ፥ ቤተ መቅደሱ ከኀጢአተኞች መጽዳቱን አረጋግጠው አይደለም:: በመሆኑም፥ "ባልተመቹት ሰዓት ታቦት ተሰደደ፤





የማይመቹት ሲወገዱ ታቦት ወደ ከብሩ ተመለሰ:: እውነቱ ይሄና ይሄ ብቻ ነው:: ስለዚህ ማንም ተነሥቶ ታቦት ተሰረቀ ቢልህ አትገረም::" የሚለው አነጋገራቸው የ"ማስተዛዘኛ" ሐሳብ እንጂ አንድም የእውነት ሽታ የለውም::

የእግዚአብሔርን ታቦት በማረኩት ላይ እግዚአብሔር ኀይሉን አሳይቷል:: የኢትዮጵያ ታቦታት ግን በሚሰርቋቸው ላይ ምንም ሲያደርጉ አይታይም:: ይህም መምህሩ ይሉናል ያሉትንና "ታዲያ በሌቦች የሚሰረቅና የሚጠፋ፥ ራሱን እንኳ መከላከል የማይችል ጽላት እንዴት ይዛችሁ ትከተላላችሁ? ተሳስታችኋል እኮ" የሚለውን ትችት ለማስተባበል አዳጋች መሆኑን ያስረዳል:: ስለዚህ መምህር፥ የኢትዮጵያን ታቦታት ከቃል ኪዳኑ ታቦት ጋር ለማመሳሰል ቃሉን ያለ ንባቡ፥ ወይም ተማረከ የሚለውን ተሰረቀ ብለው በማንበብና በመተርጐም የሄዱበት መንገድ አንድም ውጤት አላመጣምና፥ ተሳስተዋል፤ ቢመለሱ ይሻላል:: የኢትዮጵያ ታቦታት ሲሰረቁ በፖሊስ ክትትል ከሌቦች እጅ እየተመለሱ እያየንና እየሰማን፥ "ይመለሳል፤ የት ይሄዳል ታቦት? የት ይሄዳል? የትም ቢሆን ቅርሳችን? የት ይሄዳል? እንደ ወጣ የሚቀር የለም:: መለኮታዊ ነገር የት ይጠፋል? ይሂድ ተወው? ይመለሳል" በሚል ራስዎን ባይሸንግሉና ሰሚዎችዎን በያሳስቱ መልካም ነው::

## 3.10. ስለ ታቦት ዐዲስ ኪዳን ምን ይላል?

"'የተባለው ሁሉ ተብሎ የሰጣችሁን ማስረጃ ከብሉይ ኪዳን እንጂ ከዐዲስ ኪዳን ስላልሆነ፥ በዐዲስ ኪዳን በዘመነ ሥጋዌ ተቀባይነቱ የቀረና የተረሳ ነገር ስለ ሆነ ተሳስታችኋል' ይሉናል:: እኛ ግን የታቦትን ተቀባይነት ከብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በዐዲስ ኪዳንም በማያሻማ ሁኔታ እንዳለ ልናረጋግጥ እንወዳለን:: እስኪ ስለ ታቦት ዐዲስ ኪዳን ምን ይላል?"

ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈው ሁሉ ለኢትዮጵያ ታቦታት እንደ ተነገረ አድርጎ በማቅረብ፥ የኢትዮጵያ ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳውያን ናቸው ማለት ፈጽሞ አይቻልም:: ከዚህ አንጻር መምህር ምሕረተ አብ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ጠቅሰው ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ለማሳየት የሞከሩበት ትንታኔ ሁሉ ስሕተት ነው:: የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ጥቅሶች ለኢትዮጵያ ታቦታት የሰጡበት አግባብና ያብራሩበት መንገድም ጥራዝ ነጠቅና የተዛባ በመሆኑ፥ ራሳቸው

መምህር ምሕረተ አብ ካልሆኑ በቀር 'እስካሁን የሰጣችሁን ማስረጃ ከብሉይ ኪዳን ነው' ሊል ማንም አይደፍርም።

ስለ እግዚአብሔር ታቦት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የተጻፈውን ያነበበ ሰው፥ በዐዲስ ኪዳን ዘመን ውስጥ ሆኖ የታቦቱ አገልግሎት የቀጠለ ስለ መሆኑ ጥያቄ ሊያነሣ አይችልም። የታቦቱ የአገልግሎት ዘመን ያበቃበትን ሁኔታና ጊዜ ስለሚገነዘብም፥ በዐዲስ ኪዳን ስለ ታቦቱ መረጃ ማግኘት እፈልጋለሁ ሊልም ከቶ አይችልም። ምናልባት ያ ቀድሞ የነበረው የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ የት ደረሰ? ብሎ ይጠይቅ ይሆናል። ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት ግን በብሉይም ሆነ በዐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ቢፈልግ እንኳ አንድም መረጃ ሊያገኝ አይችልም።

መምህር ምሕረተ አብ ለእግዚአብሔር ታቦት የተቈረቈሩ በመመሰልና ለኢትዮጵያ ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሽፋን ለማስገኘት በማሰብ፥ ታቦትን ይቃወማሉ ያሏቸውን ወገኖች እንዲህ በማለት ይከሳሉ።

> በብሉይ ኪዳን በርግጥ ታቦት ነበር። ግን በዐዲስ ኪዳን ቀርቷል ይላሉ። የሚገርመው አልቀረም። ኢየሱስም፥ አምላካችንም ታቦትን አልሻረም። ቢሽረው ምን አስጮኸኝ፤ ጉረሮዬ እስኪሰነጠቅ ምን አስጮኸኝ? ጌታ ቀርቷል እያለ አልቀረም ብዬ ከእርሱ ጋር ሙግት? ያመኛል? ጤና አለኝ እኮ! እብድ ነኝ እንዴ? እውነት ስለ ሆነ እርግጠኛ ስለ ሆንኩ እናገራለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመነ ሥጋዌው በዐዲስ ኪዳን ታቦት አንድም ቦታ ላይ ታቦት አያስፈልግም፤ ታቦት ቀርቷል፤ ታቦት ውሸት ነው፤ ትክክል አይደለም፤ ተሳስታችኋል አላለም። እንዲያውም ብሎ ቢሆን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ታቦት ቀርቷል ብሎ ይጽፍ ነበር። ግን እነርሱም አልጻፉ፤ እኛም ተጽፎ አይተን ያነበብነው ነገር አንድም ቦታ ላይ የለም።

እስኪ ርግጠኛ ሆነው በድፍረት ያቀረቧቸውን ሐሳቦች በእግዚአብሔር ቃልና በሚያመዛዝን ኅሊና እንመርምራቸው። በቅድሚያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦትን እንዳልሻረ ተናግረዋል። ነገር ግን ከአራት ዓዦች መካከል አንዱ የሆነውን ታቦትን ነጥሎ በማውጣት ብቻ ሳይሆን፥ ሕግና ነቢያትን በጥቅሉ ማየት ያስፈልጋል። ሕግና ነቢያት የሚናገሩት ስለሚመጣው መሲሕ ስለ ኢየሱስ ነው። በውስጣቸው የያዟቸውም ነገሮች





ምሳሌነታቸው ለእርሱ ነው (ሉቃ. 24፥25-27፡44፤ ዮሐ. 5፥39 ቈላ. 2፥17፤ ዕብ. 8፥5፤ 10፥1)። ስለዚህ የጥላው አካልና የምሳሌው እማናዊ የሆነው እርሱ ሲመጣና ጊዜያዊ አገልግሎታቸውን በፍጹም አገልግሎቱ ሲተካ፥ ጌታ ለሕግና ለነቢያት ፍጻሜን ሰጣቸው፤ አልሻራቸውም።

ጌታ ሕግንና ነቢያትን ሻራቸው ብሎ መናገር ይቻል የነበረው፥ ለሚመጣው እውነተኛና እማናዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የነበሩትን ነገሮች ከተመደበላቸው የአገልግሎት ዘመን በፊት፥ ወይም የአገልግሎት ጊዜያቸውን ሳያጠናቅቁ ከአገልግሎት ውጪ ቢያደርጋቸው ነበር። ወይም ደግሞ ስለ እርሱ በሕግና በነቢያት የተነገሩትን ትንቢቶች ሳይፈጽማቸው ቢቀር ነበር ሕግንና ነቢያትን ሻራቸው የሚባለው። ጌታ የመጣበትን ዐላማ ባለ ማስተዋል የሕግና የነቢያት ቃል እንዳይፈጸም በመንገዱ ላይ የቆሙትን ሁሉ፥ ጌታ በመቃወም ቃሉ እንዳይሻርና እንዲፈጸም ያለውን ጽኑ ዐቋም አሳይቷል (ማቴ. 16፥21-23፤ 26፥52-54)።

ወደ ታቦቱ ጉዳይ ስንመለስ፥ ጌታ ታቦት ስለ መሻሩ ብቻ ሳይሆን በዐዲስ ኪዳን ስለ መጽናቱም አልተናገረም። 'ታቦት ተሽሯል? ወይስ አልተሻረም?' የሚለው ጉዳይም፥ በኢትዮጵያ ካልሆነ በቀር ታቦትን በቅድሚያ ተቀብለውት በነበሩት በአይሁድም ሆነ፥ ታቦትን በታሪክ ካልሆነ በቀር በማያውቁት በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አከራካሪ ነጥብ አይደለም። በዚሁ መጽሐፍ በክፍል አንድ ውስጥ "ታቦት በዐዲስ ኪዳን አለን?» በሚለው ርእስ ሥር ለማሳየት እንደ ተሞከረው፥ አይሁድ ታቦት አስቀድሞ ለምን ዐላማ እንደ ተሰጣቸውና በኋላም በነቢያት በኩል የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ ስለ ተረዱ (ኤር. 3፥16፤ 31፥31-34)፥ በተለይ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ታቦት አላስፈለጋቸውም። ስለ ታቦቱም ጥያቄ አላነሡም። ስለዚህ ጌታም ስለ ታቦት መሻር ማንሣት አላስፈለገውም።

መምህር ምሕረተ አብ ግን፥

> ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ዐምስት ቍጥር ዐሥራ ሰባት ላይ እንዲህ ብሏል፤ እንኳን ሊሽረው፥ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ። በእርግጥ የተሻረ ሕግ አለ ... የተሻሩ ነገሮች አሉ፤ ፍጹም የሆኑ ሕጎች አሉ፤ ... ታቦት አልተሻረም። ይህ ከታቦት መሻር ጋር አንድም የተነገረ ነገር የለም። ታቦት አልተሻረም።

ይላሉ፡፡ እውነት ነው! ጌታችን ሕግንና ነቢያትን ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣም፡፡ ነገር ግን በመምጣቱ ፍጻሜ ያገኙና ቀጣይነታቸው ያበቃ ነገሮች አሉ፡፡ የጸኑና ጠንክረው የቀረቡ ሕገጋትም አሉ፡፡ እንዲህ በመሆኑም ጌታ ሕግንና ነቢያትን ፈጻማቸው እንጂ ሻራቸው አይባልም፡፡ መምህሩም ቢሆኑ ይህን እውነታ አልካዱም፡፡ የተሻሩትንና የጸኑትን ነገሮች በመለየቱ ላይ ግን ሲቸገሩ ይታያል፡፡ ይህም ጥቅሱን ታቦት አልተሻረም በማለት ለያዙት ዐቋም ድጋፍ አድርገው በማቅረባቸው ይበልጥ ተንጸባርቋል፡፡ ሆኖም ማቴ. 5፥17ን ስለ ታቦት አለ መሻር ለመጥቀስ የሚያበቃ ምን ምክንያት ይኖር ይሆን?

መምህሩ፥ ጌታ ታቦትን አልሻረውም ከማለት በቀር፥ ያልሻረበትን በቂ ምክንያት በጥቅሱ መሠረት አላስረዱም፡፡ ይልቁንም ማቴ. 5፥17ን ስለ ታቦት አለ መሻር እንደ ተናገረው አድርገው ብቻ ነው ያቀረቡት፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ ከዚህ በላይ ለመናገር የሚያስችልና ሐሳባቸውን የሚደግፍ ነጥብ ስለሌላቸውም ይመስላል፥ ጌታ ታቦት ተሽሯል ብሎ ቢያስተምር ኖሮ፥ "ምን አስጮኸኝ፤ ጉረሮዬ እስኪሰነጠቅ ምን አስጮኸኝ? ጌታ ቀርቷል እያለ አልቀረም ብዬ ከእርሱ ጋር ሙግት? ያመኛል? ጤና አለኝ እኮ! እብድ ነኝ እንዴ? እውነት ስለ ሆነ እርግጠኛ ስለ ሆንኩ እናገራለሁ፡፡" በማለት ማስረጃ ሳያቀርቡ እኔ ያልሁትን በእምነት ተቀበሉ ዐይነት ተማፅኖ ያቀርባሉ፡፡ አክለውም፥ "ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ታቦት ቀርቷል ብሎ ይጽፍ ነበር፡፡ ግን እነርሱም አልጻፉ፥ እኛም ተጽፎ አይተን ያነበብነው ነገር አንድም ቦታ ላይ የለም" ወደሚል ሌላ "ማስረጃ" ያልፋሉ፡፡ ነገር ግን ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱ የታቦት አገልግሎት ማብቃቱን ስለ ማስተማራቸው ማስረጃ ቢቀርብ፥ እርሳቸው እንዳሉት ጤነኛነታቸውን እንጠራጠር?

ከላይ ለማሳየት እንደ ተሞከረው ጌታችን ታቦትን በተመለከተ ተሽሯል ወይም አልተሻረም በማለት በግልጽ ያስተማረው ትምህርት በቅዱስ ወንጌል አልተመዘገበም፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥመን፥ "በጐደለ ሙላ" እንደ ተባለን ሁሉ፥ የምንፈልገውን ሐሳብ እንሞላበታለን? ወይስ ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚለውን አገናዝበን ኅሊናዊ ብይን እንሰጣለን? ምናልባት እርሳቸው አላነበቡ፥ ወይም ማንበብና መጥቀስ አልፈለጉ ይሆናል እንጂ፥ የታቦት አገልግሎት ማብቃቱን የጌታ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጽፈዋል፡፡





ማስረጃ 1. 2ቆሮ. 3፥3-18፡፡

በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ላይ የምናገኘው ዋና መልእክት፥ የሐዲስ ኪዳን አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን አገልግሎት ብልጫ ያለውና እጅግ የከበረ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከዚህ በቀር ሳይባል ሁሉንም የብሉይ ኪዳን አገልግሎት የሚመለከት ነው፡፡ አንዳንዶች ግን በተለይ ይህ ክፍል ታቦትን እንደማይጨምርና ስለ ሌላው አገልግሎት ብቻ እንደሚናገር አድርገው ጽፈዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ እንመልከት፤ "ከላይ የተጠቀሰው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክትም ፈጽሞ ስለ ታቦት መሻር የተነገረ አይደለም፡፡ ሕገ ኦሪት በሕገ ወንጌል መምጣት ምክንያት ስለ ማነሷና ሕገ ወንጌል ስለ መጽናቷ እንጂ፡፡"[76] መቼም ይህ "ካፈርኩ አይመልሰኝ" ካልሆነ በቀር፥ ምዕራፉ ሕገ ኦሪት ከሕገ ወንጌል ማነሷን እንደሚናገር ያስተዋለ ሰው፥ ከኦሪት ንዋያተ ቅድሳት አንዱ የሆነው ታቦት ዐብሮ ክብሩ ዝቅ አላለም ለማለት የሚያስደፍረው አንድም ምክንያት አይኖርም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ የመልእክቱ መንደርደሪያ አድርጎ ያቀረበው፥ በድንጋዩ ጽላትና በልብ ጽላት መካከል ያለውን የክብር መጠን በማነጻጸር ነው፡፡ "እናንተም፥ በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው" (ቍጥር 3)፡፡ የኦሪት አገልግሎት ክብሩን ከማጣቱ የተነሣ ታቦትም ክብሩን እንዳጣ ምንም አያጠራጥርም፤ "ያ የከበረ እንኳ፥ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን ዐጥቶአልና" (ቍጥር 10) በተባለው መሠረት፥ እጅግ በበለጠው የሐዲስ ኪዳን አገልግሎት ክብር ምክንያት የብሉይ ኪዳን አገልግሎት ክብሩን ማጣቱ የታመነ እውነት ነውና፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የኦሪት አገልግሎት አንዱ ንዋይ ቅዱስ የሆነው ታቦት የአገልግሎት ዘመኑ አላከተመም ማለት፥ ሰውዬው ከሞተና ነፍሱ ከወጣ በኋላ እጁ ብቻ ተለይቶ ሊንቀሳቀስ ይችላል እንደ ማለት ይቈጠራል፡፡

እነዚሁ ለእውነት አልረረታ ባዮች፥ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 3 ውስጥ "ተሻረ" የሚለው በሙሴ ፊት ላይ የወጣው ብርሃን እንጂ ታቦት አይደለም ብለው ነገሩን ተራ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ርግጥ ነው! ስለ ቀደመው አገልግሎት ክብር ሲባል፥ ሙሴ ጽላትን ተቀብሎ ከሲና ተራራ

[76] ሄኖክ (ዲ/ን) (2001፣ 106)፡፡

በወረደ ጊዜ፥ የእስራኤል ልጆች ፊቱን ማየት እስኪፈሩና መሸፈኛ እስኪያደርግበት ድረስ አንጸባርቆ ነበር (ዘፀ. 34፥29-35)። በኋላ ግን ማንጸባረቁ ቀርቷል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል እየተናገረ ያለው ዋና ነገር በሙሴ የፊት ማንጸባረቅ ስለ ተገለጸው የአሪት አገልግሎት ክብር እንጂ፥ ክብሩን ማሳያ ስላደረገው ስለ ሙሴ ፊት አይደለም።

> እንግዲህ እስራኤላውያን ከፊቱ ክብር የተነሣ የሙሴን ፊት ትኵር ብለው ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፣ ያ ከጊዜ በኋላ የሚያልፈውና በድንጋይ ላይ የተቀረጸው የሞት አገልግሎት በክብር ከመጣ፣ ታዲያ፣ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ከዚያ የላቀ ክብር አይኖረውም? ሰዎችን የሚኰንነው አገልግሎት የከበረ ከሆነ፣ የሚያጸድቀው አገልግሎት የቱን ያህል ይበልጥ የከበረ ይሆን! (ቍጥር 7-9 ዐ.መ.ት.)።

**ማስረጃ 2. ዕብ. 9፥4-5**

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ በምዕራፍ 9 ቍጥር 1 ላይ፥ "ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ሥርዐትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት" በማለት ይጀምራል። እየተናገረ ያለው ስለ አሪት አገልግሎት፣ አገልግሎቱ ይፈጸምበት ስለ ነበረው የማደሪያው ድንኳንና በድንኳኑ በሚገኙት ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት ይሰጥባቸው ስለ ነበሩት ንዋያተ ቅድሳት ነው። ከንዋያተ ቅድሳቱ መካከልም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ "ሁለንተናዋ በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት" ከነጓዟ እንደ ነበረች ጠቅሷል (ቍጥር 4)። ይሁን እንጂ ስለ ኪዳኑ ታቦትም ሆነ ስለ ሌሎቹ የማደሪያው ድንኳን የተቀደሱ ዕቃዎች፥ "ስለ እያንዳንዳቸው ልንናገር አሁን አንችልም" (ቍጥር 5) ይላል። ይህም ብሉይ ኪዳን ፍጻሜ በማግኘቱና በማለፉ፥ ስለ እርሱ በምንናገርበት ዘመን ላይ አለ መሆናችንን ያስረዳል። በዚህ ክፍል የተገለጹትን የማደሪያውን ድንኳን፣ የተቀደሱትን ዕቃዎችና አገልግሎቱን ሁሉ በኀላፊ አንቀጽ (Past Tense)፦ "ነበራት"፤ "ነበረባት"፤ "ነበረች"፤ "ነበረ"፤ "ነበሩ" ብሎ መግለጹም፥ ታቦትን ጨምሮ የተጠቀሱት አሪታውያን ነገሮች ሁሉ ማለፋቸውንና በሐዲስ ኪዳን አገልግሎት መተካታቸውን ያመለክታል።

መምህር ምሕረተ አብ ግን ቢያንስ እነዚህን በክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ስለ ታቦት የአገልግሎት ዘመን ማብቃት የተጻፉትን ማስረጃዎች መጥቀስ አልፈለጉም። እንዲያውም ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንኳ ስለ ታቦት





መሻር እንዳልጻፈና እርሳቸውም የተጻፈ ነገር በአንድም ስፍራ እንዳላነበቡ ርግጠኛ ሆነው ነው የተናገሩት። ይህ ግን ፍጹም ውሸት ነው። መቼም ከላይ በ2ቆሮ 3፥3-18 እና በዕብ 9፥1-5 ላይ የተጠቀሱትን ሐሳቦች ሳያነቡ አልቀሩም። ነገር ግን በግልጽ ተጽፎ ሳለ፥ በአንድም ቦታ ላይ አልተጻፈም፤ እኛም አላነበብንም ያሉበት ምክንያት ግልጽ ነው። ምእመኑ መጽሐፍ ቅዱስን አያነብም ብለው የተሳሳተ አመለካከት ስለ ያዙ ይሆናል እንዲህ ለማለት የደፈሩት። የማይደግፏቸው የሚመስሏቸውን ጥቅሶች እየተዉ ለሐሳባቸው የሚስማሙ የመሰላቸውን ብቻ እየመረጡ ስለሚያነቡና በተጻፈበት መንፈስ ሳይሆን በሚስማማቸው መንገድ ስለሚተረጕሙም ሊሆን ይችላል እንዲህ ያሉት። ከላይ የቀረቡት ጥቅሶችም ሐሳባቸውን የማይደግፉላቸውና የሚያፈርሱባቸው ስለ ሆኑ ነው እንደሌሉ የቈጠሯቸው።

መምህሩ በ2ቆሮ. 3፥3-18 ላይ የተጻፈውን ዘለው፥ በ2ቆሮ. 6፥16 ላይ የተጻፈውን ቃል ግን ጠቅሰው ጳውሎስ ታቦት እንዳልተሻረ ይናገራል ይላሉ፤ እንዲህ በማለት፥

> [ታቦት] እንኳን ሊሻር፥ እንኳን ሊሻር ቅዱስ ጳውሎስ ምን አለ? በ2ቆሮ. 6፥16 ላይ ታቦትን እንደ ጣዖት ለሚመለከቱ ሰዎች ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፥ የእግዚአብሔርን ታቦት አለ፤ ቅዱስ ጳውሎስ እኮ ነው፤ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው? ታቦት ሌላ ነው፤ ጣዖትም ሌላ ነው። ጣዖት የሰይጣን ነው፤ ታቦት የእግዚአብሔር ነው።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ፥ "የእግዚአብሔርን ታቦትስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው?" የሚለው የተወሰደው ከሰባ ሊቃናት ቅጂ ከተተረጐመው ከግእዙ ዐዲስ ኪዳን ላይ ነው (2ቆሮ. 6፥16 የ2000 ዓ.ም. ዕትም)። የግሪኩ ቅጂ ከሆነውና በ1953 ዓ.ም. ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን፥ "ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው?" ነው የሚለው።

በመጀመሪያው፥ "የእግዚአብሔር ታቦት"፤ በሁለተኛው ደግሞ፥ "የእግዚአብሔር መቅደስ" የሚሉት ሐረጋት የሚገልጹት በቁሙ ታቦትን ወይም ቤተ መቅደስን አይደለም፤ ክርስቲያኖችን ነው እንጂ። የ2000 ዓ.ም. ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሲያረጋግጥ፥ "የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደለንምን?" ይላል። የ1953 ዓ.ም. ዕትም መጽሐፍ

ቅዱስ ደግሞ፥ "እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና" ይላል። ከዚህ አንጻር ይህ ጥቅስ ስለ ታቦት የሚናገር አይደለም። መምህር ምሕረተ አብ ግን በዚህ ጥቅስ መሠረት የታቦትን አለ መሻር ከማስረዳት ይልቅ፥ የቃል ኪዳኑን ታቦት ጣዖት ነው ብሎ የተናገረ ሰው ያለ ይመስል፥ ስለ ታቦትና ስለ ጣዖት ልዩነት ወደ ማስረዳት ነው የዞሩት። ይህም የሚያሳየው ጥቅሱ ታቦት ከአገልግሎት ውጪ አለ መሆኑን ሊናገርላቸው እንዳልቻለና እርሳቸውም ለማስረዳት ዐቅም እንዳነሳቸው ነው። በዚህ ስላልተሳካላቸው እንደ ገና ወደ ራእየ ዮሐንስ ይሸጋገራሉ። "ዮሐንስ በራእዩ ምን ብሎ አረጋገጠ መሰላችሁ! ... ራእይ 11፥19 ላይ እነሆ አለ፤ ... በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፤ የቃል ኪዳኑም ታቦት፥ የእግዚአብሔርም ታቦት፥ በየት ታየ? .. በሰማይ ታየ። እንኳን በምድር በሰማይ የማን ታቦት አለ? የእግዚአብሔር የአምላካችን ታቦት አለ።"

ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይህን የራእየ ዮሐንስ ክፍል አልቀበለውም ሊል አይችልም። በአተረጓጐም ላይ ግን ልዩነት ይታያል። ለራእ. 11፥19 ጥቅስ በተለያዩ የክርስትና ክፍሎች ከሚሰጡት ትርጕሞች መካከል ሁለቱን፥ በዚሁ መጽሐፍ በክፍል አንድ ውስጥ "በዐዲስ ኪዳን ታቦት አለን?" በሚለው ርእሰ ሥር ለማሳየት ተሞክሯል። በኢኦተቤክ ሊቃውንት ዘንድ ለዚህ ጥቅስ የተሰጠው ትርጕም፥ "ሕጉን ጠብቃ የምትኖር ምእመን መንግሥተ ሰማይን ወርሳ ከብራ ታየች"[77] የሚል ነው። መምህር ምሕረተ አብ ግን፥ "መምህር" እንደ መባላቸው ቤተ ክርስቲያን የሰጠችውን ፍቺ እንኳ ተከትለው ሳይሆን፥ በንባቡ ብቻ ሄደው በዐዲስ ኪዳን ታቦት አለ ለማለት ጥቅሱን ተጠቅመውበታል። ጥቅሱ ግን የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰማይ መታየቱን እንጂ በዐዲስ ኪዳን ዘመን የታቦት አገልግሎት መቀጠሉን አያረጋግጥም።

ጥቅሱን እኔ ባልሁት መንገድ፥ "ታቦት በዐዲስ ኪዳን ዘመን አለ ይላል" ብላችሁ ተቀበሉ ማለታቸው ሳያንስ፥

> አይ እኛ ዐዲስ ኪዳንም ቢል ብሉይ ኪዳንም ቢል ታቦትን እንሰድባለን ካሉ ይችላሉ። ግን ታቦቱን የሚሳደብ ሰው የሰይጣን መልእክተኛ ነው። የዮሐንስ ራእይ 13፥7 666 የክርስቶስ ተቃዋሚ አውሬው በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን

[77] መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ (1989፣ 423) የራእየ ዮሐንስ 11፥19ን ትርጓሜ ተመልከት።





> ማደሪያ ታቦቱን ይሳደባል። የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦቱን የሚሳደብ የሰይጣን መልእክተኛ ነው።

በማለት ከሰሚዎቻቸው ጋር ምልልስ ያደርጋሉ።
"ስለዚህ ታቦትን የሚሰድብ የማን መልእክተኛ ነው?"
"የሰይጣን።"
"ታቦትን የሚያከብር የማነው?"
"የእግዚአብሔር።" ...
"የእግዚአብሔርን ሐሳብ መፈጸም ይሻላል ወይስ መቃወም ይሻላል?"
"መፈጸም" ...
"የሰይጣንን ሐሳብ መቃወም ይሻላል? መደገፍ ይሻላል?"
"መቃወም።"
"ስለዚህ ቅርሳችንን ታቦታችንን እንጠብቅ።"

የትኛውም ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ የቃል ኪዳኑን ታቦት ሊሰድብ አይችልም። ስለ ኢትዮጵያ ታቦታትም ቢሆን እስካሁን ለማሳየት እንደ ተሞከረው መጽሐፍ ቅዱሳውያን አይደሉም ነው የተባለው። ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተጻፈውን ለእነርሱ በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱሳውያን አስመስሎ ማቅረብም ትክክል አይደለም ነው የተባለው። የመምህር ምሕረተ አብ ክርክር ግን እነዚህን እውነቶች ሊያስተባብል የሚችል ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ አንጻር ማን የእግዚአብሔር መልእክተኛ፥ ማን ደግሞ የሰይጣን መልእክተኛ እንደ ሆነ በፉከራ ሳይሆን በትምህርቱ ፍሬ ሊታወቅ ይችላል።

"የ ... ቄስ ቅኔ ቢጐድልበት ቀረርቶ አለበት" እንዲሉ፥ የጠቀሱትን ጥቅስ ማስረዳት የማይሆንላቸው ቢሆን፥ ብዙዎች የሚናገሩት ሲያልቅባቸው "ዘንዶው፣ አውሬው" እያሉ እንደሚያስፈራሩ፥ እርሳቸውም ማስፈራሪያቸውን "አውሬው" ይሉ ገቡ። በራእ. 13፥7 አውሬው የሚሰድበው የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦት ነውን? በፍጹም! የቃል ኪዳኑ ታቦት ማደሪያነቱ ለጽላት ነበር። እግዚአብሔር ለእስራኤል መሪዎች የሚገለጥበት መሆኑ ቢታወቅም፥ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ ተብሎ ግን በአንድም ስፍራ አልተጠራም። አውሬው፥ "እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ" ነው የሚለው። ይህም ቃሉ በሰማይ ስላለው የእግዚአብሔር ማደሪያ እንጂ ስለ ታቦት እንዳልተነገረ ያስረዳል። ታዲያ እርስዎ ከየት አምጥተው ነው አውሬው ታቦቱን ይሳደባል የሚሉት?

በመጨረሻም መምህር፥ ባልደረባዎ፥ "የእግዚአብሔር መገለጫ ዙፋኑ የሆነውን ታቦተ ሕጉን ከመንበራችን ያኖርነው ተሳስተን፣ ሳይገባንና ሳንረዳው ቀርተን ሳይሆን፥ እውነትና እውነት ስለ ሆነ ነው፡፡ ይህንን እኛ ያየነውን እውነት ያላያችሁና ባለ ማስተዋል የምትጓዙ ወገኖች ወደዚህ እውነት እንድትመጡ እግዚአብሔር ይርዳችሁ» ብለዋል፡፡ "የማያዳግም ምላሽ" ተብለው ለቀረቡት ምላሾቻችሁ፥ በዚህ መጽሐፍ የተሰጡት የምላሽ ምላሽ እውነቶች፥ ለእርስዎም ለባልደረባዎም መሳሳታችሁን አሳይተዋል ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ወደ ሌለው ትምህርታችሁ፥ ሌላውን ከመጋበዝ ይልቅ ወደዚህ እውነት እንደምትመጡ ተስፋ እናደርጋለን፡፡





ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ታቦታት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መታወቂያዎቿ ናቸው፡፡ በየበዓላቱ ከሚደረገው የታቦታት ንግሥ ጋር በተገናኘ እየተከናወነ ያለው ተግባር፥ ታቦት በሃይማኖት ቅጥር ብቻ ሳይወሰን ወደ ማኅበረ ሰቡ ባህል እየሠረጸ፥ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፥ ብሎም ለአገር የቱሪስት መስሕብ እየሆነና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን እያስገኘ መምጣቱን መገንዘብ አያስቸግርም፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ የቃል ኪዳኑ ታቦት በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ይገኛል የሚለው እምነት የብዙዎችን ትኩረት የሚስብ ሆኗል፡፡ እዚህ ላይ ግን፥ በብሉይ ኪዳን የነበረው የታቦት አገልግሎት፥ በዐዲስ ኪዳንም ቀጥሏል ወይ የሚለው ነጥብ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሊፈተሽ ይገባል፡፡

ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው የቃል ኪዳኑ ታቦትና የኢትዮጵያ ታቦታት በስም የተመሳሰሉ ቢሆንም፥ በአገልግሎት ግን የተለያዩ መሆናቸውን በዚህ መጽሐፍ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከታቦት ጋር በተገናኘ በብሉይ ኪዳን የነበረውና በአገራችን እየታየ ያለው ሁኔታም ልዩነት እንጂ ተመሳሳይነት እንደማይታይባቸው ተጠቍሟል፡፡

በአገራችን ታቦት እንደ አንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ቅዱስ ንዋይ የሚታይ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ከመታየት ዐልፎ፥ በየሥርዐተ ንግሡ እንደ እግዚአብሔር የሚዘመርለት፣ የሚሰገድለትና የሚመለክ እየሆነ መምጣቱ የእግዚአብሔርን ስፍራ መውሰዱ ነውና፥ ድርጊቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲመዘን ትልቅ ስሕተት ነው፡፡ ይህ ተግባር ለሰዎች ውጫዊ ወይም ሥርዐታዊ ርካታን የሚሰጣቸው ቢመስልም፥ ውስጣዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚለውጥ ሆኖ አይታይም፡፡ ከዚህ የተነሣ ብዙው ሰው ሕይወቱ የተለወጠና በመጽሐፍ ቅዱስ የማይመራ ሆኗል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲስተካከል፥ ምእመናን ወደ እማናዊው ታቦት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉና በእርሱ በኩል ትክክለኛውን አምልኮተ እግዚአብሔርም ዘወትር እየፈጸሙ በተለወጠ ሕይወት እንዲኖሩ መርዳት ከቤተ ክርስቲያን አባቶችና መምህራን ብዙ ይጠበቃል፡፡

በዚህ ዘመን የተለያዩ ሰዎች ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት በተጻፈው ቃል ስለ ኢትዮጵያ ታቦታት የሚሰጧቸው ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ውጪ ናቸው፤ ዛሬ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀርም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ታቦት የለም፡፡ ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈንና በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት

የሌለን ነገር ከየት አምጥተው ነው የሚያስተምሩት? ቢባል፥ አንዳንዶች ካለ ማወቅ የተነሣ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት የተነገረውን ለኢትዮጵያ ታቦታት ጠቅሰው ያስተምራሉ። ሌሎች ደግሞ ልዩነቱ ቢገባቸውም፥ የኖረውን ባህል ማስቀረት አይቻልም፤ ለማስቀረት ቢሞከርም ተቃውሞ ይነሣል በሚል፥ ሊመጣ የሚችለውን ተቃውሞና ስደት በመፍራት ስለ ታቦት ማስተማራቸው ይታወቃል። አንዳንዶቹም ዐውቀውም ሆነ ባለ ማወቅ የካሴት ገበያቸውን ለማድራትና በስብከት ንግድ ለማትረፍ ሲሉ ወተቱን አጥቍረው፥ ማሩን አምርረው እንደሚሰብኩ ግልጽ ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከሆነ ግን ታቦትን ጨምሮ የተቀሩትም የብሉይ ኪዳን ጓዞች ሁሉ፥ በዐዲስ ኪዳን ይመጣል ለተባለው ለአካሉና ለአማናዊው ጥላና ምሳሌ ነበሩ። አካልና አማናዊ የተባለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሐዋርያው አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶችን ጠቅሶ ይህን ሲያስረዳ፥ "እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው" ብሏል (ቈላ. 2፥17)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት እግዚአብሔር ለሕዝቡ መሪዎች የሚገለጥበትና ከእነርሱ ጋር የሚነጋገርበት የክብር ዙፋኑ ነበር (ዘፀ. 25፥21-22፤ 30፥6፤ ዘኊ. 7፥89)። የቃል ኪዳኑ ታቦት ብቻም ሳይሆን እግዚአብሔር በነቢያት የተናገረባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል (ዕብ. 1፥1)።

በዐዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ራሱን የገለጠውና ለሰዎች የተናገረው ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው (ማቴ. 11፥27፤ ዮሐ. 1፥18፤ ዕብ. 1፥1-3)። በዚህም የቃል ኪዳኑ ታቦት ይሰጠው የነበረው የጥላ አገልግሎት በአማናዊው ታቦት በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጻሜን አግኝቷል ማለት ነው። ዛሬ በዚሁ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ እግዚአብሔር መቅረብም ሆነ እርሱን ማነጋገር አይቻልም (ዮሐ. 10፥9፤ 14፥6፤ ኤፌ. 2፥13፡18፤ ዕብ. 13፥15)። ስለዚህ ዛሬ በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን ማግኘትና ማነጋገር እንጂ፥ እግዚአብሔርን ለማነጋገር ወደ ታቦት መሄድ አያስፈልግም።

መጽሐፍ ቅዱሳውያን ባይሆኑም፥ በአገራችን ታቦታት የተባሉ ንዋያተ ቅድሳት አሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጥንታውያን ጽሑፎች፥ የብሉይ ኪዳኑ የቃል ኪዳን ታቦት አገልግሎቱን መቀጠሉን ሳይሆን፥ ወይም በኢትዮጵያ ታቦታት መተካቱን ሳይሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የዐዲስ ኪዳን





ታቦት መሆኑን ይመሰክራሉ። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

- "ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ ዘግቡር እምዕፀ ዘኢይኔቅዝ ይትሜሰል ለነ ዘእግዚአብሔር ቃለ ዘኮነ ሰብአ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ። - ከማይነቅዝ ዕንጨት ተሠርቶ ሁለንተናው በወርቅ የተለበጠው ታቦት፥ ያለ መለያየትና ያለ መለወጥ ሰው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል (ኢየሱስ ክርስቶስን) ይመስልልናል"[78]
- "ወእምድኅረዝ ኮነ ሰብአ ተሰምየ ብእሴ ወመሲሐ ወኢየሱስሃ ወታቦተ ወዐራቄ ወበኵረ ለዘሰከቡ ወበኵረ ለዘይትነሣእ እሙታን ወርእሰ ሥጋሃ ለቤተ ክርስቲያን። - ሰው ከሆነ በኋላም ብእሲ (ሰው)፣ የተቀባ፣ ኢየሱስ፣ ታቦት፣ አስታራቂ፣ ለሙታን በኵር፣ ከሙታን ወገን ለሚነሣም በኵር፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ ተባለ።"[79]

ከእነዚህ ምስክርነቶች እንደምንረዳው፥ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚያረጋግጥልን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ዐዲስ መንገድ ተጠርጓልና የቀድሞው የታቦት አገልግሎት አብቅቷል። ለታቦታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ስፍራውን ከመልቀቅ በቀር፥ ታቦት በዐዲስ ኪዳን ሌላ ስያሜና ተግባር ተሰጥቶት አገልግሎት ላይ የሚውልበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም።

ታቦታተ ኢትዮጵያን በሚመለከት የኖረው ሃይማኖታዊ ሥርዐት ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር ግንኙነት ባይኖረውም፥ እንዲቀጥል እንጂ በእግዚአብሔር ቃል እንዲስተካከል ሲደረግ አይስተዋልም። ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ ለቃል ኪዳኑ ታቦት በተጻፈው ቃል የኢትዮጵያን ታቦታት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስመስሎ ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት ነው። እንዲህ ማድረግ የእግዚአብሔርን ቃል ላልተጻፈበትና ለራስ ፍላጎት በሚስማማ መንገድ መጥቀስ ነውና በእግዚአብሔር ቃል ላይ መዋሸት ይሆናል። በተጨማሪም እግዚአብሔር በዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት በዚህ ዘመን ለእኛ የተናገረበትን መንገድ አለ መቀበልና ማቃለል ነው።

መምህር ምሕረተ አብ የሄዱበት መንገድም ወደነዚሁ ስሕተቶች የሚያደርስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ለማይታወቁት የኢትዮጵያ ታቦታት

[78] ውዳሴ ማርያም ዘእሑድ።

[79] ሃይማኖተ አበው (1986፤ 339)።

የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ፥ እነርሱን መጽሐፍ ቅዱሳውያን ለማስመሰል በመሞከራቸው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስሕተት ፈጽመዋል። የዐዲስ ኪዳኑን አማናዊ ታቦት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰዎች እንዳያስተውሉትና በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርቡ በኢትዮጵያ ታቦታት ሸፍነዉታል። መቼም ቢሆን ከዚህ የበለጠ ጉልሕ ስሕተት አይኖርምና መምህሩ ተሳስተው ማሳሳታቸውን ሊያምኑ ይገባል። የሰሟቸውና የበለጠው እውነት እስኪገለጥላቸው ድረስ የተሳሳተውን ስብከት ለጊዜው የሰሟቸው ወይም የተቀበሏቸው ምእመናንም ሁሉ እውነቱን ከሐሰት እንዲለዩና ከታቦት ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲሉ ይመከራሉ።

ምስጢርን የሚገልጥ አምላክ እውነቱን ያብራልዎ!!





## ዋቢ ጽሑፎች


ሃይማኖተ አበው (1986) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ሄኖክ ኀይሌ (ዲ/ን) (2001) ታቦት በሐዲስ ኪዳን። አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)።

ሐንኮክ ግርሃም (1995) ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ። (ተርጓሚ ጌታቸው ተስፋዬ) አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

መሠረት ስብሐት ለአብ (1988) ሥላሴ በተዋሕዶ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

__________ (ዓ.ም. ያልተገለጸ)" የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥነ ሥርዐት ትምህርት" ቦታው ያልተገለጸ።

መርሐ ምእመናን። (1946) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

መጻሕፍተ ሠለስቱ ሐዲሳት። (1989) አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ።

ብሉይ ኪዳን (ግእዝ) (1955)፣ አሥመራ፣ ኮከበ ጽባሕ ቤተ ማኅተም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1951) የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ-አክሱም-ዛጉዌ። አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

__________ (1966) የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ኀ.ሥ. ማተሚያ ቤት።

አምሳሉ አክሊሉ (ዶ/ር) (1976) "ዐጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ"። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር) (ዓ.ም. ያልተገለጸ) የአገው ሕዝቦችና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ታሪክ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1993) መጽሐፍ ቅዱስ ዐዲሱ መደበኛ ትርጉም። (የታተመበት ቦታውና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948) መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ክብረ ነገሥት ግእዝና አማርኛ (1994)። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ኮርኮክ ሮበርት (1999) ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ናትን፡፡ (ተርጓሚ ሣህለ ጥላሁን) አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ፡፡

ውዳሴ ማርያም (1987)። አዲስ አበባ፣ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ዑቁ ኢያሰሕቱከሙ፡፡ (1996) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1953) መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

__________ (1992) የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

__________ (1980) መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

__________ (2000) መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡ (የታተመበት ቦታውና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዐተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፡፡ (1988) አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ (1962) ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዲበኩሉ ዘውዴ (ዶ/ር) (1986) ፍትሐ ነገሥት ብሔረ ሕግ ወቀኖና ሰያሜው ፅንሰ ሐሣቡ ምንጮቹ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ፡፡ (1987) አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ገድለ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (1998) (ቦታው ያልተገለጸ) ጢስ ዐባይ ማተሚያ ቤት፡፡

ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፡፡ (1996) (የታተመበት ቦታውና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፡፡

ጎርጎርዮስ (ሊቀ ጳጳስ) (1974) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፡፡

ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት (ዓመተ ምሕረቱ እና ወሩ ያልተገለጸ)፡፡

ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፡፡ (1990) አዲስ አበባ፣ (የታተመበት ቦታውና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)፡፡

Kenneth Barker (1995) The NIV Study Bible. Zondervan Publishing House, USA.